# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 001 መስከረም 1 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!








አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትሪያርክ | ሼህ ሐጂ ኢብራሒም ቱፋ | ብፁእ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ | ፓስተር ጻድቁ አብዶ | ቄስ ዶ/ር ዮናስ ይገዙ

## አለመግባባቶች ተወግደው ሰላም እንዲሰፍን የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ ዓመት በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ያሉ ግጭቶችና አለመግባባቶች ተወግደው ሰላም እንዲሰፍንና ሀገራዊ አንድነት እንዲጠናከር የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ፡፡ አዲሱ ዓመት ሲከበር በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን በመደገፍ ሊሆን እንደሚገባም አሳሰበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለኃይማኖት የአዲስ ዓመት በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የእርስ በርስ ግጭት፣ ረሃብ፣ ጦርነት፣ ድህነት፣ ኋላ ቀርነት

አለመግባባቶች ተወግደው... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





## በአዲሱ ዓመት ግጭትና የዘመናት ስብራትን በምክክርና በሽግግር ፍትሕ መጠገን ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ ዓመት ግጭቶችንና የዘመናት ስብራትን በምክክርና በሽግግር ፍትሕ ለመጠገን መነሳሳት ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ትናንት ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት፤ አዲሱን ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ የሚጠቀስ ዘመን ለማድረግ እንዘጋጅ ብለዋል፡፡

የዘመናት ዕዳዎቻችን የምናወራርድበት፣ የኖሩ ቁስሎቻችን የምናክምበትና የዘመናት ሕልሞቻችንን ሥር መሠረት የምናስይዝበት ዓመት ለማድረግ እንነሳ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

2017 ዓ.ም እቅዶቻችንን ተግብረን፣ ፕሮጀክቶቻችንን በጊዜና በጥራት አጠናቅቀን፣ ግጭቶቻችንን በውይይትና በድርድር የምንፈታበት ዓመት ይሁንልን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የዘመናት ስብራቶቻችንን በምክክርና በሽግግር ፍትሕ ጠግነን፣ በብዙ ነገሮች ራሳችንን ችለንና ሪፎርሞቻችንን

በአዲሱ ዓመት... ወደ ገጽ 6ዞሯል











## " ከኢትዮጵያ ሥልጣኔ ማሳያዎች መካከል የዘመን አቆጣጠር አንዱ ነው"

- መጋቢ ሀዲስ ሮዳስ ታደሰ (ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ለዘመናት ከዘለቁ የሥልጣኔዋ ማሳያዎች መካከል አንዱ የዘመን አቆጣጠሯ ነው ሲሉ መጋቢ ሀዲስ ሮዳስ ታደሰ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

መጋቢ ሀዲስ ሮዳስ ታደሰ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለብዙ ሺ ዓመታት የዘለቁ የሥልጣኔዋ ማሳያ

"በኢትዮጵያ ለዘመናት... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## «በዓላትን ለሰላምና ለይቅርታ ልንጠቀምባቸው ይገባል»

- ሊቀ ማዕምራን የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ



**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በዓላትን ለሰላም እና ለይቅርታ ልንጠቀምባቸው እንደሚገባ እና ወደ ዓዲስ ዓመት የሚደረገው ሽግግር ይቅር በመባባል መሆን እንዳለበት የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ማዕምራን የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ ገለጹ፡፡

ሊቀ ማዕምራን የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ራሳችንን መርምረን የተሻለ ማንነትን መላበስ፣ ትናንት እንቅፋት እንዳይሆንብን መጣር፣ እልህንም መተው፣ በዓላትን ለሰላም እና ለይቅርታ ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡

የተቸገሩ ጎረቤቶቻችንን በማገዝ ማሳለፍ ይኖርብናል። መደጋገፍና መተባበራችን ቀደም ሲልም የሚገለጽ ነበር። 2017 ዓ.ም የተሻለ አስተሳሰብ የምንላበስበት ዓመት ብናደርገው ጥሩ ነው ብለዋል፡፡

«በትናንት ጉዳይ ላይ ተቸንክረናል፡፡ ትናንት ትልቅ እንቅፋት ሆኖብናል» ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ትናንትን ለመቀባባት መሞከር የለብንም ብለዋል፡፡ ብዙ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ሲከራከሩ፣ ጉዳዩ የመረረ ጥላቻና ግጭት ሲፈጥር ተመልክቻለሁ፡፡ ትናንት የተሠሩ ነገሮች ታሪክ ናቸውና በታሪካቸው ብናውቃቸው የተሻለ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በዓላትን ለሰላምና... ወደ ገጽ 6ዞሯል




# 2017 ዓመተ ምሕረት

## - የሠብዓዊነት፣ የሰላም፣የልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሥራን የምንገልጥበት

## - ከአዋራጁ የተረጂነት አስተሳሰብ የምንላቀቅበት ሊሆን ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የ2017 ዓመተ ምሕረት እንደ ሕዝብ ለሠብዓዊነት፣ ለሰላም፣ ለዘላቂ ልማት እና አካባቢ ጥበቃ ተግባራት፤ እንደ ሀገርም ከአዋራጁ የተረጂነት እሳቤ ለመውጣት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ያለፈው ዓመት(2016) ብዙ ትዝታዎችን አኑሮ ያለፈ ቢሆንም፤ አዲሱ ዓመት ከእነዚህ ትውስታዎች ባሻገር የሚታይ አዲስ ሕልምና ራዕይ የሚታሰብበትም፣ የሚፈጸምበትም ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ እንደ ሕዝብም እንደ ሀገርም ከፍ አድርገው ከሕልምና ራዕዮቻችን ትይዩ ሊገልጡን በሚችሉ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ መሥራትን ይጠይቃል፡፡

አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የስኬት፣ የመተሳሰብ፣ ሠብዓዊነት ቦታ የሚያገኝበት እንዲሁም ችግር ከኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያውያን የሚርቅበት እንዲሆን ምኞቴ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ይሄ ግን ከምኞት ያለፈ ሥራ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መንግሥትም ሆነ መላው ሕዝብ ለሀገር ሰላምና ዘላቂ ልማት፣ ለሠብዓዊነትና እርስ በእርስ መረዳዳት ብሎም ለአከባቢ ጥበቃ ተግባራት ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን ሠብዓዊነትን ለሌሎች የሚያስተምሩት እንጂ ከሌሎች የሚማሩት አለመሆኑን በተግባር ሲገልጡ ኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ በ2017ትም ሠብዓዊነትን ከፍ አድርገው መግለጥ፤ የመተጋገዝና የመረዳዳት እሴታቸውን አውጥቶ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ዘላቂ ልማትን እና የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን ከፍ አድርጎ በመከወን፤ ኢትዮጵያውያን የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር፣ የምግብ ሉዓላዊነትን የማረጋገጥ አቅም እንዳላቸውም ማሳየት ይገባቸዋል፡፡



**አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር)**

በመሆኑም አዲሱ ዓመት፣ ሠብዓዊነትን የምንገልጥበት፣ ሰላማችንን የምናጸናበት፣ ዘላቂ ልማትን የምናሰፍንበት እና አካባቢያችንን የምንንከባከብበት፣ ለዚህም ሁለንተናዊ እይታን የምንላበስበት መሆን አለበት ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በተመሳሳይም አዋራጅ የሆነውን ተረጂነት ከውስጣችን የምናስወጣበትና ለምግብ ሉዓላዊነታችንን እውን መሆን መስፈንጠሪያ አቅም ለመፍጠር የምንተጋበት ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ የሰላም ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሠብዓዊ ድጋፍን ለማቅረብ ችግር መሆኑን በተጨባጭ ስለታየ እና ተቸገርኩ ደግፉኝ ለማለት እንኳን ሰላም አስፈላጊ እንደመሆኑ፤ ለሁሉም መሠረት የሆነውን ሰላም ማጽናት የአዲሱ ዓመት ተግባር ሊሆን ይገባል። ለዚህ ደግሞ የምንቸገርባቸውን ጉዳዮች አደምጦና ተመካክሮ መሄድ እንጂ፤ ለማንኛቸውምና በማንኛቸውም ምክንያት ሰላምን በሚያሳንስ መንገድ ነገሮችን ለማስኬድ መሞከር ጥቅም የለውም፡፡

ከሠብዓዊነት፣ ከዘላቂ ልማትና ከሰላም ጉዳዮች በተጓዳኝ በ2017 ከስጋችንም፣ ከነፍስና አጥንታችንም ማውጣት ያለብን ነገር ተረጂነትን ነው ያሉት ኮሚሽኑ፤ ተረጂነት ክፉ ልምምድ ብቻ ሳይሆን የዜግነት እና የሀገር ክብርን የሚያዋርድ፣ ሌሎች ጋር ያለንን አቻነትም የሚያኮስስ ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡

በመሆኑም በ2017 ተረጂነት የተጣበቀብን ትልቅ ችግርና ፈተና መሆኑን ተገንዝበን ከተረጂነት ለመውጣት ሁላችንም ሀብታችንን፣ እውቀታችንን፣ ጉልበትና ሃሳባችንን ጭምር ደምረንና አሰባስበን የምንረባረብበትና እጅ ለእጅ ተያይዘን የምንወጣበት ዘመን ሊሆን ይገባል፡፡

እንደ አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው ገለጻ፤ በመሆኑም 2017ን የምንፈልገው ደረጃ ላይ ለመድረስ እንደ መስፈንጠሪያ ጊዜ ልንጠቀመው፤ ለአህጉራችንም ሌጋሲ የምናስተምርበት ሊሆን ይገባል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የአረንጓዴ ዐሻራ ሌጋሲ ደግሞ ለዚህ ትልቅ የማቀድና የመፈጸም አቅማችን አብነት ነው። ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያውያን ከተነሳን ማድረግ እንደምንችል፤ በአንድ ጀንበር ከ615 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ተክለን ዓለም ያልቻለውን ችለን አሳይተናል፡፡

ይሄ ደግሞ የትኛውም ትልምና ጅምራችን ለፍጻሜም፣ ለስኬትም የሚበቃ ስለመሆኑ ማንጸሪያችን ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ፣ 2017 ለዘላቂ ልማታችንም፣ ለአካባቢ ጥበቃችንም፣ ለምግም ዋስትና ሥራችንም አቅም የሚሆኑ ችግኞችን የምንተክልበት፣ የተተከሉትንም ለዛፍነትና ለፍሬነት እንዲበቁ የምንንከባከብበት፤ የምግብ ዋስትናችን አካል፣ የምግብ ሉዓላዊነታችንም አቅም አድርገን የምንጠቀምበት ዘመን ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም፣ 2017 በብዙ መንገድ ሰላማችን፣ ዘላቂ ልማታችን፣ የአካባቢ ጥበቃችንን እና ሠብዓዊነታችንን አጥብቀን የምንይዝበት፤ ተረጂነትንም በእጅጉ የምንጸየፍበት እና ከምግብ ዋስትና ወደ ምግብ ሉዓላዊነት ለምናደርገው ጉዞ የመስፈንጠሪያ አቅም የሚሆኑ ተግባራትን የምንፈጽምበት ሊሆነን ይገባል፡፡



**መስፍን አርዓያ (ፕ/ር)**



**ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር)**



**ዮናስ አያሌው (ኢ/ር)**

# አዲሱ ዓመት የተሻለ ሠላም የሚገኝበት እንዲሆን የተቋማት ኃላፊዎች ምኞታቸውን ገለጹ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አዲሱ ዓመት ከሁሉም በላይ የተሻለ የሠላም ዓመት እንዲሆን ምኞታቸው መሆኑን የተለያዩ የተቋማት ኃላፊዎች ገለጹ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ር) የአዲስ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በኩል ባስተላለፉበት ወቅት እንደተናገሩት፤ አሮጌው ዓመት በርካታ ድብልቅ ስሜቶች ያሳለፍንበት ዓመት ነበር፤ 2017 ዓ.ም የተሻለ፣ መልካምና ከሁሉም በላይ የሰላም ዓመት ይሁንልን ብለዋል።

ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኃላፊዎች ባለፉት ሁለት ዓመት ከአምስት ወራት የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወናቸውን አስታውሰው፤ በቀጣይ እስከ አዲሱ ዓመት አጋማሽ ድረስ የተያዙ ሥራዎች የሚጠናቀቁበት ዘመን እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

መሠረታዊ የሆኑና ማግባባት ያልቻሉ ምክንያቶችን ነቅሶ በማውጣት በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ የሚወያዩበትን መድረክ አመቻች እንደመሆናችን መጠን ሁሉንም ክልሎችና በተዋረድ ያሉትን ባለድርሻ አካላት በመለየት አጀንዳዎቻቸውን ሰብስበው የሚሰጡበት ሂደት ላይ እንገኛለን ሲሉ አስረድተዋል።

ዓመቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሠላም፣ የጤናና ከሁሉ በላይ ያለፉትን ችግሮቻችንን በሚገባ ተገንዝበን በመሰባሰብ እርስ በርሳችን ታርቀን ወደ ሀገራዊ ምክክር የምንሄድበት ጊዜ መሆን አለበት ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺህ በላይ ወረዳዎች ላይ አጀንዳ እየተሰበሰበ መሆኑን አመላክተው፤ በቀጣይም የተሳካ የምክክር ሂደት እንዲፈጠር በአዲሱ ዓመት ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበትም አመላክተዋል።

የሠላም ሚኒስትር ዴኤታ ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በአዲሱ ዓመት የኢትዮጵያ የሰላም እጦት ችግሮች የሚቀረፍበት ዓመት እንደሚሆን ተስፋ አኝ ሲሉ ተናግረዋል። ለሰላም እንቀፋት የሆኑ ችግሮች እንዲወገዱ ሚኒስቴሩ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

በ2017 ዓ.ም ለአዎንታዊ የሰላም ግንባታ ትኩረት ተሠጥቶ እንደሚሠራ የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተለይም ከኃይማኖት ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የተሻለ ሰላም ሀገሪቷ ላይ እንዲሰፍን በርካታ ሥራዎች መጀመራቸውን አንስተዋል፡፡ ለዚህ ስኬት ደግሞ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ዓመቱ እንደ ሀገር የተያዙ እቅዶቻችን የሚሳኩበት፤ ወደ ብልጽግና የሚደረገው ጉዞ በተሳካ ሁኔታ የሚከናወንበት ይሆናል ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዮናስ አያሌው (ኢ/ር) ናቸው፡፡ የሕዝቡ ዕድገት ጎልቶ የሚወጣበት የሰላም ዓመት እንደሆንም ተመኝተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው፤ አዲሱ ዓመት ለመላው ኢትዮጵያውያን የሰላም፣ የጤና፣ የደስታ የስኬትና እንዲሁም የዕድገትና ብልጽግና ዓመት እንዲሆን ተመኝተዋል፡፡

ኮሚሽኑ በ2016 ዓ.ም የተሰጡትን ተልዕኮዎች በአግባቡ መፈጸም እንደቻለ ገልጸው፤ ይህንኑ በ2017ዓ.ም አጠናክሮ እንደሚያስቀጥል ነው ያስታወቁት፡፡

# በዕርድ ወቅት ለቆዳና ሌጦ ጥራት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በበዓላት እርድ ወቅት ለቆዳና ሌጦ ጥራት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአምራች ኢንዱስትሪ የቆዳ ቴክኖሎጂ ዘርፍ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ቢሻው ዋካሶ እንደገለፁት፤ ለሀገራችን ቆዳና ሌጦ ትልቅ ሀብት በመሆኑ በዕርድ ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ሀገራዊ ምርት ማሳደግ ይገባል፡፡

በዓልን ምክንያት በሚጸፈም ዕርድ የሚገኙ የቆዳ ምርቶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንደሚያስገኙ ጠቁመው፤ ለሀገር ጥቅም ሲባል ህብረተሰቡ ቆዳና ሌጦን በባለሙያ በጥንቃቄ በማስገፈፍ ወደቆዳ መሰብሰብያ ቦታ የማድረስ ኃላፊነት አለበት ብለዋል፡፡

ዘርፉ ከፍተኛ የሥራ ዕድልና የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ በመሆኑ፤ በኮንደሚኒየም አካባቢ የሚደረጉ ዕርዶች ላይ ቆዳን ቆፍሮ መሬት ውስጥ መቅበር የአካባቢ ብክለት የሚያስከትልና የሀብት ብክነት በመሆኑ ከዚህ አይነት ድርጊት መታቀብ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ኢንዱስትሪው ያልተጠቀመውን ከፍተኛ አቅም ለመጠቀም ስትራቴጂ መነደፉን ጠቅሰው፤ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች በፋይናንስ ለማሳደግ የአፍሪካ ገበያ ላይ በማተኮር ከጂቡቲ፣ ኬንያ እና ሌሎች ሀገራት ጋር በመሆን በተለይ የተማሪዎች ጫማ የማምረት ሥራ እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በዘርፉ በ2017 ዓ.ም ትልቅ ዕቅድ መቀመጡን አመላክተው፤ የአካባቢ ብክለት ለመከላከል የተፅእኖ መጠናቸው ቀላል የሆኑ ኬሚካሎች በመጠቀም ብክለትን የመከላከል ሥራ ይሠራል ብለዋል፡፡

ዘርፉ ከውጭ ይገቡ የነበሩ የቆዳ ምርቶች ሙሉ በሙሉ ማስቀሩቱን የጠቀሱት ኃላፊው፤ የሚሊተሪ እና የተማሪዎች ጫማ በሀገር ውስጥ መመረቱ ትልቅ እምርታ በመሆኑ ዕውቅና ሊሰጠው እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ተወካይ አቶ ኤርሚያስ ወሰኑ በበኩላቸው፤ ለቆዳ ጥቅም ያለን አመለካከት ትኩረት ሰጥተን የሀገራችን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጥራቱን የጠበቀ ቆዳ ወደ ተገቢው ቦታ በማድረስ ኢንዱስትሪውን ማገዝ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ዜና



ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደሰ

## “ህብረተሰቡ በአዲሱ ዓመት ይቅር በመባባል መንፈስ ሁለንተናዊ ሰላምን ሊያጸና ይገባል”

**- ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደሰ**
**የኢትዮጵያ ሃይማኖት ጉባዔ ጠቅላይ ፀሐፊ**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ ዓመት አዲስ ምዕራፍ በመሆኑ ህብረተሰቡ ይቅር በመባባል መንፈስ የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላም ሊያጸና ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ጉባዔ ጠቅላይ ፀሐፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ጉባዔ ጠቅላይ ጸሐፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ህብረተሰቡ በአዲሱ ዓመት ይቅር በመባባል መንፈስ የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላም ሊያጸና ይገባል፡፡

ሁሉም ሰው ይህንን ምዕራፍ እንደ አዲስ ጅማሮ በመውሰድ ለመረዳዳት፣ ለመቻቻል እርስ በእርስ ለመግባባት እቅድ መያዝ አለበት ያሉት ጠቅላይ ጸሐፊው፤ በ2017 ዓ.ም በጎ ተግባሩ በማስቀጠልና ከባለፈው ችግር ለመላቀቅ ጥረት ማድረግ እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በአእምሮ መታደስና መለወጥ ከፈጣሪ የተሰጠ ትዕዛዝ በመሆኑ የሰው ልጅ አዲስ ዓመት ሲቀበል በአዲስ ልብስ ከማጌጥና የተለያዩ መብሎች ከማዘጋጀት ባሻገር በሃሳብ መታደስና ለአዲስ እቅድ፣ ሕይወት፣ ተስፋና ትጋት መዘጋጀት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፤ የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ተወስኖ ተለክቶና ተቀምሮ የተሰጠው እድሜው በአግባቡ ካልተጠቀመበት በሕይወቱ አንዳች ውድቀት እንዳስመዘገበ የሚቆጠር መሆኑን ጠቅሰው፤ በሚያልፍ ጊዜ የማያልፍና ለትውልድ የሚሸጋገር ዐሻራ አኑሮ ማለፍ ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ አክለውም ፤ ሰው ያለፈው ዘመኑ በክፋት፣ በምቀኝነት፣ በሰላም እጦት፣ በቂምና በበቀል አሳልፎ ሊሆን ይችላል ነገር ግን አዲስ ዓመትን ሲያከብር በአዲስ ተስፋ በይቅር ባይነት ከባለፈው ውስብስብ ችግር በመሻገር መንፈስ መሆን አለበት ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በተጨማሪም በእርቅ በሰላም በፍቅር በአንድነት በምህረት በቸርነት በይቃርታ እንዲሁም በመረዳዳትና በመተጋገዝ በኢትዮጵያዊነት እሴት መቀበል አለበትም ብለዋል፡፡

እንደ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ገለጻ፤ ካለፉት ጊዜያት ምን ተማርኩ ምንስ አወቅኩ ምን አሳካው ምንስ ጎደለኝ የሚሉትን ጉዳዮች ማሰናሰልና ከግምት ውስጥ ማስገባትም ያስፈልጋል፡፡

አዲስ ዘመን በሚያረጁና በሚጠፉ ጊዜያቶች የማይደበዝዝ ትልቅ ሥራ ሠርቶ ለማለፍ እድል እንደተሰጠ የሚያስገነዝብ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ሰው አዲስ ዓመት ሲመጣ አዲስ እድል ተሰጥቶኛል በማለት ለመልካም ሥራ መትጋት አለበት ያሉት ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፤ በተሰጠን እድል መጠቀም አለመቻል በራሱ ለቁጭትና ለሃዘን የሚዳርግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አዲስ ዓመት ክረምቱ፣ ጅረቱ፣ ዝናቡና ነጎድጓዱ ሁሉ አልፎ በአበቦች ፍካት እንዲሁም በተስፋ የተሞላ ሰማይ የሚታይበት በመሆኑ ተፈጥሮ በራሱ የሚያስተምርበት ጊዜ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የሃይማኖት ተቋማትም በዚህ ረገድ ለተከታዮቻቸው ተገቢውን ትምህርትና ግሳጼ መስጠት እንዲሁም ምዕመናንም ከየቤተ እምነቱ የሚሰጡ ትምህርቶች በአግባቡ መተግበር አለባቸው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ቤተ እምነቶች በሰላም ዙሪያ ላይ ያላሳኳቸውና ያልሰሯቸውን ነገሮች መለስ ብለው ለማየት አዲሱ ዓመት እንደ አዲስ የተሰጠ እድል መሆኑን በመገንዘብ በትጋት እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮችና ከንቲባዎች ለአዲሱ ዓመት መልካም ምኞታቸውን ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮችና የከተማ አስተዳደሮች ለአዲሱ ዓመት መልካም ምኞታቸውን ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ በ2017 ዓ.ም የሕዝቦችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የተለያዩ የልማት ሥራዎች እንደሚከናወኑ ጠቅሰው፤ የከተማዋ ነዋሪዎችም ትጋት፣ አንድነትና ትብብራቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

መጪው ዓመት ተባብረን ራዕያችንን እውን የምናደርግበት፣ እቅዳችንን የምንፈጽምበት ይሁንልን ሲሉም መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ፤ በአዲሱ ዓመት በተለያዩ መስኮች ስኬትና ሰላምን የምናረጋግጥበት እንዲሆን እመኛለሁ ብለዋል፡፡ ዘመኑን በተሻለ ጥረትና አንድነታችን በማጠናከር የበለጠ ስኬትና ልማት የምናስመዘግብበት እንዲሆን ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ፤ በሕዝባችን ሰላም ፈላጊነት፤ በአመራራችን ቁርጠኝነት ባሳለፍነው ዓመት የገጠሙንን አይነተ ብዙ እና ተለዋዋጭ ፈተናዎች በጽናትና በትዕግስት አልፈናል ብለዋል፡፡

በአዲሱ ዓመት ሁላችንም በአንድነትና በሕብረት በመቆም ለመጪው ትውልድ መልካም ነገር በመሥራት ከእዳ ወደ ምንዳ የምንሸጋገርበት የስኬት እና የብልጽግና ዓመት ይሆን ዘንድ ከልብ እመኛለሁ ብለዋል፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ጥላሁን ከበደ በበኩላቸው፤ አዲሱ ዓመት የክልሉ ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ወደላቀ ደረጃ የሚሸጋገርበት እንዲሁም ህብረ ብሄራዊ አንድነት የሚያብብበት የስኬት ዘመን እንዲሆንም ተመኝተዋል፡፡

በአዲሱ ዓመት ይበልጥ በማገልገል የሰላም፣ የመቻቻልና የብልፅግና ተምሳሌት የሆነ ክልል ለመንባት የተጣለውን ግብ ለማሳካት እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ-መስተዳድር አሻድሊ ሀሰን፤ በ2017 አዲሱ ዓመት የክልሉን ሠላም በማጽናት የህብረተሰቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በሙሉ አቅም እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

የተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመት የተለያዩ ጫናዎችን በመቋቋም በሀገራችን ኢትዮጵያ የተጀመረውን የብልጽግና



ጉዞ ወደፊት የሚያራምዱ ስኬቶች የተመዘገቡበት ነው ብለዋል፡፡

ወደ አዲሱ ዓመት ስንሸጋገር አዲስ ተስፋ ሰንቀን፣ አዳዲስ ዕቅዶችን ይዘን፣ ለአዳዲስ ውጤቶች ለመብቃት ብርታታችንን፣ ፅናታችንን፣ ትጋታችንን ከፍ በማድረግ ነው ያሉት ደግሞ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር እንዳሻው ጣሰው ናቸው፡፡

አዲሱ ዓመት አቅሞቻችንንና ፀጋዎቻችንን አስተባብረን በማንቀሳቀስ አዳዲስ ውጤቶችን እውን ለማድረግ በጋራ የምንተጋበት ዓመት ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ደስታ ሌዳሞ በበኩላቸው፤ በአዲሱ ዓመት ኢትዮጵያውያን አንድነታችንን አጠናክረን፣ ሰላማችንን ጠብቀን፣ ሙሉ አቅማችንና ጊዜያችን ለልማትና ለእድገት የምናውልበት ዓመት ይሁንልን ብለዋል፡፡

ባለፉት የለውጥ ዓመታት ሉዓላዊነትን የሚፈታተኑ የውጭ ፖለቲካ ጫናዎችን በጥበብና በበሳል ዲፕሎማሲያዊ መንገዶች አልፈናል፤ አዲሱ ዓመትም ውጥናችንን የምናሳካበት የደስታ ዘመን እንዲሆንልን እመኛለሁ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ (ዶ/ር)፤ አዲሱ ዓመት የሠላም፣ የአብሮነትና አንድነት ይበልጥ እንዲጎለብት ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

ለመጪው ትውልድ ዐሻራ ያሳረፍንበት ግድብ አብዛኛው ሥራ የተጠናቀቀበት እና ተጨማሪ ተርባይኖች ሥራ የጀመሩበት ለሕዝቡ ታላቅ ብስራት የተበሰረበት ዓመት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የተጀመሩ መልካም ሥራዎችን በማጠናከር አዳዲስ አስተሳሰቦችን እና የልማት ውጥኖችን በመያዝ ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች እንደሚሠሩ አስታውቀዋል፡፡

አዲሱ ዓመት የሰላም የብልጽግና የመተሳሰብና በህብረት የምናድግበት እንዲሆንልን እመኛለሁ ያሉት ደግሞ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሐጂ አወል አርባ ናቸው፡፡

ሁሌም ቢሆን ዕድገትና ብልጽግና ሁለንተናዊ መሆን ስለሚገባው በተለያዩ አካባቢዎችና ዘርፎች የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ እጅ ለእጅ ተያይዘን አዲሱ ዓመትን ለነገው ትውልድ ዐሻራ አስቀምጠን ማለፍ የምንችልበት እንዲሆን ጥሪዬን አቀርባለሁ ብለዋል፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ከድር ጁሃር በበኩላቸው፤ በአዲሱ ዓመት የአስተዳደሩን ሰላምና ፀጥታ በአስተማማኝ ከመጠበቅ ጎን ለጎን የሕዝብን የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በፍጥነት እና በጥራት ለመፍታት በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

በአዲሱ ዓመት የሚፈለገው ለውጥ እንዲመጣ ሁሉም በየተሰማራበት መስክ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ መትጋት ይጠበቅብናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሐመድ ባስተላለፉት መልእክት፤ የክልሉን ሕዝብ ከተረጂነት ለማላቀቅና በምግብ ራስን ለመቻል የተጀመሩ የስንዴና ሩዝ ልማት ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል፡፡

በክልሉ የተገኘውን ሰላምና መረጋጋት በማጠናከር በአሸባሪ ሃይሎች ሊፈጸሙ የሚችሉ ትንኮሳዎችን አስቀድሞ ለመከላከል የፀጥታ መዋቀሩ ከሕዝብ ጋር የሚያደርገው ትብብርም በትኩረት እንደሚሠራ ርዕሰ መስተዳድሩ ተናግረዋል፡፡

አዲሱ ዓመት በአዲስ መነሳሳትና አስተሳሰብ የተጀመሩ ልማቶች ተጠናክረው የሚቀጥሉበት ሊሆን እንደሚገባ የሀረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ ገልጸዋል፡፡

መጪው አዲስ ዓመት ለኢትዮጵያውያን ሰላም፣ መቻቻል፣ መከባበርና መፈቃቀድ የሰፈነበት እንዲሆንም ተመኝተዋል፡፡

ርዕሳነ መስተዳድሮቹ በዓሉን አቅመ ደካሞችና ጠያቂ የሌላቸውን ወገኖች በመደገፍ ማክበር ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ሚኒስቴሩ ከዲፕሎማሲያዊ ሥራው በተጨማሪ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ አስታወቀ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ሚኒስቴሩ ከዲፕሎማሲ ሥራው በተጨማሪ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በትኩረት እየሠራ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴ ገለጹ፡፡

ተቋሙ አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ለሚያሳድጋቸው 33 ህፃናትና አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሠራተኞቹ የበዓል ስጦታና የማዕድ ማጋራት ሥነ-ሥርዓት አከናውኗል፡፡

በወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴ፤ ሚኒስቴሩ ከዲፕሎማሲያዊ ሥራ በተጨማር ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ በትኩረት እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡ ይህም ዲፕሎማሲያችን በሠብዓዊ ተግባራት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ማመላከቻ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደሀገር የማህበረሰቡን አንገብጋቢ ችግሮች ለመፍታት እየተከናወነ በሚገኘው ሥራ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነቱን ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በዚህም የተቀናጀ የክረምት ሠብዓዊና ማህበረሰባዊ አገልግሎት ተነሳሽነትን በመወጠን የ2016 ዓ.ም የበጎ አድራጎት መርሀ-ግብር መጀመሩን አስታውሰዋል፡፡

እንደ ሚኒስቴሩ ገለጻ፤ ተቋም የአቅም ደካሞችን ቤት የማደስና ማዕድ የማጋራት ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በተጨማሪ በአርባ ምንጭና ወላይታ ሶዶ ከተሞች ድጋፍ ለሚሹ ከ400 በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍና ለአራት አቅመ ደካማ ቤተሰቦች ደረጃውን የጠበቀ የቤት

ፎቶ ገበበ ገብሬ



ግንባታ ማስጀመሪያ ሥራ አከናውኗል፡፡

በሁለቱ ከተሞች የተቋሙ ሠራተኞችን በማስተባበር በሺዎች የሚቆጠሩ ችግኞችን ማስተከል ችሏል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ተቋሙ 33 ሕፃናትን ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ በማሳደግ ላይ ይገኛል፡፡ ህፃናትን ማሳደጉና መደገፉ ለእኛ ትልቅ ፀጋ በመሆኑ እንደመታደል እንወስወደዋለን ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህም ተቋሙ ለማህበራዊ ደህንነት ያለውን ቁርጠኝነት ከማጉላት ባሻገር የኢትዮጵያውያንን አንድነትና ርህራሄ ማሳያ የሆነው የአብሮነትና የመደመር መርህ የሚገልጽ ነው ብለዋል፡፡

ድጋፍ የሚደረግላቸው ህፃናት ደህንነት ከሀገራችን ደህንነት ጋር በቀጥታ የተሳሰረና የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የመቅረፅ ዓላማ ያለው መሆኑን ሚኒስትሩ ጠቁመዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ መሳተፍ የዜግነት ግዴታ መሆኑን አምባሳደር ታዬ ጠቁመው፤ የተቋሙ ሠራተኞች እያከናወኑ ያሉትን የበጎ አድራጎት ተግባር አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በመርሀ-ግብሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴን ጨምሮ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ የተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ተገኝተዋል፡፡

# አለመግባባቶች ተወግደው ሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመልካም አስተዳደር እጦት በዓለም ፊት ልዩ መለያችን ሆኗል ብለዋል፡፡

ዛሬም ከዚህ ችግራችን ሳንላቀቅ አጠናክረን ለማስቀጠል ውል የገባን እስክንመስል ድረስ እየቀጠልንበት እንገኛለን ያሉት ፓትሪያሪኩ፤ በእንዲህ የመሰለ ልምድ ልናፍርበትና ንስሐ ልንገባበት እንጂ ልናስቀጥለው አይገባም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለዓለም የሚተርፍ ሀብትና ጸጋ አላትና ችግሮቻችንን በመፍታት የሕዝባችንን ሰቆቃ ሳናስረዝም በእኩልነትና በአንድነት ሀገራችንን በማደስ በራሳችን እሴቶች እንመራ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በአዲሱ ዘመን ግጭትን በውይይት፣ መለያየትን በአንድነት እንዲሁም አለመግባባትን በዕርቅ በመፍታት በመታደስ ማማ ላይ የቆመ ማኅበረሰብ ለመገንባት ሁሉም የድርሻውን ሃላፊነት እንዲወጣ አሳስበዋል፡፡

አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የዕርቅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ያድርግልን ሲሉም አባታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሼህ ሀጂ ኢብራሂም ቱፋ ኢትዮጵያ የተለያዩ የሃይማኖቶች ተከታዮች በሰላምና በፍቅር ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖሩባት አገር መሆኗን በመጥቀስ ሁሉም ይህንን ተቻችሎ የመኖር ልምዱን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ተናግረዋል ።

ሁሉም አዲሱን አመት እርቅና ሰላም በማውረድ ለአገር ልማትና ዕድገት መስራት እንደሚገባም ገልፀዋል።

አዲሱ አመት የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት ዘመን እንዲሆን በዓሉን በመተባበርና በመረዳዳት ማሳለፍ አለብን ብለዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ብጹዕ አቡነ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል በበኩላቸው፤ አዲስ ዓመት የተሰጠን በጎ ነገሮችን እንድናስብና ለጋራ ጥቅም የሚሆኑ ተግባራትን እንድንፈጽም ነውና ለዚህ እንነሳሳ ብለዋል፡፡

ባለፈው ዓመት የተፈታተኑንን ችግሮች ዛሬ በአዲሱ ዓመት መፍታት እንድንችል እግዚአብሔር የመፍትሄውን መንገድ እንዲያሳየን የምንጸልይበት ጊዜ ነው ብለዋል፡፡

አዲሱ ዓመት ለተራቡት፣ ለተጠሙት፣ ለታረዙት፣ ለተፈናቀሉት፣ ለታሰሩት፣ ለታመሙትና ላዘኑት የምንደርስበት ጊዜ ይሁንልን ሲሉ አባታዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ በበኩላቸው፤ ባለፉት ዓመታት የተፈጸሙ ያልተገቡ ተግባራትና እኛነታችንን የማይመጥኑ ችግሮች የመነጩት ከስግብግብነት፣ ከጠበኝነት፣ ከቂም በቀልና ከግዴለሽነት እንጂ በተፈጥሮ ያገኘናቸውም ሆነ ፈጣሪ ያሸከመን እዳዎች አለመሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

በራሳችን ቸልተኝነትና ትዕቢት ያመጣናቸውን መዘዞች በማስተዋልና በጥበብ በመራቅ መከባበርን፣ ይቅር መባባልን እና ከአድሎ ነጻ የሆነ ግንኙነት ማጠናከር እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

አዲሱ ዓመት የበረከትና የሰላም፣ አብዝተን ስለምድራችን የምንጸልይበትና ለእውነት የምንቆምበት ዓመት ይሁንልን ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል። የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ቄስ ዮናስ ይገዙ (ዶ/ር) ባስተላለፉት የበዓል መልዕክታቸው፤ ወደ አዲሱ ዓመት መሸጋገር የቻልነው በእግዚአብሔር ቸርነት በመሆኑ ባለፈው ዓመት የታዩ ድክመቶችን በማረምና ጥንካሬዎችን በማስቀጠል ለዜጎች ኑሮ መሻሻል ሁሉም ሊተጋ ይገባል ብለዋል፡፡

እግዚአብሔርን መፍራትና መልካም ስብዕናን መፈለግ ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በአዲሱ ዓመት የሌሎችን ጥቅምና ማንነት የማይነኩ ተግባራትን በታማኝነትና በቅንነት ለማከናወን መነሳሳት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ሀገሪቱ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ እየተገዳደራት ያለው የተሟላ የሰላም እጦት እንዳለ ሆኖ በተለያዩ ጊዜያት የሚፈጠሩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች የዜጎችን ኑሮ እያከበዱ መሆናቸው ግልጽ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር የጠብ ጫሪነት ሳይሆን በሰላምና በመደጋገፍ የመኖር ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም ሰሞኑን ከጎረቤት ሀገራት ጋር የተያያዙና የሀገሪቱን ሰላም የሚፈታተኑ ጉዳዮች እየተስተዋሉ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

እግዚአብሔር በሁኔታዎች ሁሉ ጣልቃ ገብቶ በሀገሪቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት እንዲቻል ተግቶ መጸለይ ይገባል ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

አዲሱ ዓመት የተለያየ ችግር የደረሰባቸውን ወገኖች በተለይም ተንከባካቢና አሳዳጊ የሌላቸውን ህጻናት፣ አቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ህሙማንን፣ በድህነት የሚማቅቁና ተፈናቅለው የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ አባታዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ‹‹በዓላትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያውያን የተጋረጡብንን ችግሮች መለየት አለብን፣ መልሶ መላልሶ ግጭት ውስጥ የሚያስገቡንን መንስኤዎች ብናስብ ጥሩ ነው፣ ሌሎች ሰዎች እንዲቀየሩ፣ ሰላማዊ እንዲሆኑ ባንጠብቅ ይሻላል፡፡ ሌሎች ሰዎች እኛ የምንፈልገውን ላይሆኑ ይችላሉ፣ በቁጥጥራችን ስርም አይደሉም ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እኛ ግን በራሳችን ቁጥጥር ስር በመሆናችን መሻሻልም፣ መታረምም ስለምንችል እያንዳንዳችን ራሳችንን በመመልከት የተሻለ አስተሳሰብ ልንገነባ ይገባናል ሲሉም ነው የተናገሩት፡፡

ኢትዮጵያውያን ታሪክን አውቀን የራሳችንን ነገር ብንወስድ፣ ትናንት እንቅፋት እንዳይሆን ብንጥር፣ እልህን ብንተው ይጠቅመናል ብለዋል፡፡

በትንሽ ነገር እልህ ተጋብቶ የሰው ሕይወት ሲጠፋ፣ አካል ሲጎድል ንብረት ሲወድም ተመልክተናል፡፡ ከእልህ መውጣት አለብን፡፡ ሁሉንም ነገር በእልህ ከያዝነው ሁሉንም ነገር ሊያሳጣን እንደሚችል በማወቅ ራሳችንን ለማደስ መጣር አለብን፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩ ግጭቶች ከዚህ የተለዩ አይደሉም፡፡

የራሳችንን ነገር ማድነቅ አለብን፡፡ ስናደንቅ የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎች እና ማንነቶችን በአክብሮት ተቀብለን ሊሆን ይገባል፤ መከባበር መቻል አለብን ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

“የምሠራው ሥራ ጠቃሚ ሊሆን ጎጂነትም ሊኖረው ይችላል፡፡ እኔ ካለፍኩ በኋላ የዚህ ተቋም ታሪክ ሆኖ ያልፋል፡፡ ግን የእኔ ስም አለበት፡፡ የእኔን ስም ለመቀባባት የሚፈልጉ ሰዎች ነገን ለምን ይጣላሉ፡፡ ምን ተጽፎ ነበር፣ ምን መረጃ ነበረ በሚል ሰነድ ማገላበጥ ሊለምዱ ይገባል” ብለዋል፡፡

አንድ መድረክ ላይ ወጥቼ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብናገር የተማረውም ያልተማረውም ያደንቀኛል፡፡ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች በአንዱ ብናገር ግን ዘረኛ ተደርጌ ልፈረጅ እችላለሁ ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ልዩነት የጠብ መንስኤ መሆን የለበትም፡፡ አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ማወቅ እየፈለግን በሀገራዊ ቋንቋ መጣላት የለብንም፡፡

‹‹ኢትዮጵያ የተሠራችበት እና የተገነባችበት መንገድ ምንም ጉድለትም፤ ጥፋትም አልነበረውም ብለው የሚከራከሩ ዋና እንቅፋት ናቸው ብዬ አስባለሁ›› ብለዋል፡፡

ሊቀ ማእምራን የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ እንደተናገሩት፤ በዓላትን የአምልኮ ሥርዓታቸውን ሳንዘነጋ ማክበር አለብን፣ በትክክል የሃይማኖት ሥርዓታቸውን እንዳይለቅቁ መጠንቀቅ ይገባናል፡፡

# በአዲሱ ዓመት ግጭትና የዘመናት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በብቃት አሳክተን የምንለውጠው ዘመን ይሁንልን ሲሉ ምኞታቸውን ገልጸዋል።

ወደፊት የሚመጡት ልጆቻችን “ይሄ ታሪክ የተሠራው፣ የዛሬ ስንት ዓመት በ2017 ነው” እንዲሉን እናድርገው ሲሉ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

በወጀብና በአውሎ ውስጥ አስገራሚ ሥራዎችን እንድንሠራ የፈቀደ ፈጣሪ ዛሬም ከእኛ ጋር ነው፤ ነገም ከእኛ ጋር ነው፡፡ መሥራት የእኛ ማከናወንም የእርሱ ነው፤ እኛ ከተነሣን ዘመኑን እንድንለውጠው እርሱ ይረዳናል ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ዘመን ዕድል ነው፡፡ ዘመንን መጠቀም ግን የሥራ ውጤት ነው። ዘመንን ፈጣሪ ለሁላችንም በእኩልነት ሰጥቶናል፡፡

ልዩነት የሚፈጠረው በዘመን በመሥራትና ባለመሥራት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በታሪካችን ውስጥ የምንኮራባቸው ምእራፎች አሉ ሲሉ አስፍረዋል። በሕይወታችን ውስጥም ደስ የሚያሰኙን ጊዜያት አሉ። የተሰጠንን የዘመን ዕድል በሚገባ ተጠቅመን የሠራንባቸው ወቅቶች ናቸው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እኛ ብንፈልግም ባንፈልግም ዘመን ይለወጣል። ጊዜ ወደፊት ብቻ የሚሄድ ማሽን ነውና፡፡ ማንም አያስቆመውም፤ አቅጣጫም አያስቀይረውም፡፡ የሚቻለው በጊዜ መጠቀም ብቻ ነው ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳመላከቱት፤ “ክረምት ለሰነፍ ገበሬ መዓት፤ ለጎበዝ ገበሬ ምሕረት ነው” ይባላል። ምሕረትና መዓቱ ከዝናቡ የሚመጣ ሳይሆን ከገበሬዎቹ ዝግጅትና ሥራ የሚገኝ ነው፡፡ በሰነፍ ገበሬ ላይ ዘመን ይለወጥበታል፤ ብርቱው ገበሬ ግን ዘመንን ራሱን ይለውጠዋል።

ኢትዮጵያን ዘመን እየለወጣት ብዙ ጊዜ ኖራለች፤ አልፎ አልፎ ደግሞ በብርታትና በትጋት ዘመኑን ለውጣው ታውቃለች ሲሉ ገልጸዋል። ዘመን ሲለውጠን ከተራራ እንደተፈነቀለ ድንጋይ ወዳሰብነው ሳይሆን ወደፈለገው ነው የሚወስደን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ 2017 የሚለውጠን ሳይሆን የምንለውጠው ዓመት እንዲሆን ነው ምኞቴ ነው ብለዋል፡፡

# “ከኢትዮጵያ ሥልጣኔ ማሳያዎች መካከል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መገለጫዎች አሏት፡፡ የእራሷ ፊደል፣ የዜማ ሥልት፣ የዘመን አቆጣጠር፣ የኪነ ሕንጻ አሠራር፣ የሥዕል አሣሣል ጥበብ ለዚህ ማሳያ ናቸው፡፡

ገናና ሥርወ መንግሥት ከነበራቸውና በሥልጣኔ መጥቀው ከነበሩት ጥቂት የዓለማችን ሀገሮች ኢትዮጵያ አንዷ እንደነበረች ጠቅሰው፣ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ጥበብ መንፈሳዊና ጥበብ ሥጋዊን የያዙ ጥንታውያት የብራና መጻሕፍትንም ይዛ የኖረች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሥነ ፈለክ ታሪክ ላይ ጎልታ የምትታወቀው ለ19 ዓመታት የመራችው ንግሥት ካሲዮፕያ መሆኑዋን በመግለጽ፣ የንግሥት ካሲዮፕያ፣ የባሏ የንጉሥ ሴፌውስና የልጇ የልዕልት አንድሮሜዳ ምርምር ደግሞ የኢትዮጵያን የሥነ ፈለክ ሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ማድረሱን ተናግረዋል፡፡

ሕብራተ ከዋክብትን ከመለየት ጀምሮ በዘመናቸው በስማቸው እስከማስጠራት አድርሷቸው እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቀደምት ሊቃውንት በቀኑጥሩ ትምህርት በመራቀቃቸው ከጥቃቅን እስከ ታላላቅ ዑደታትን ጠንቅቀው ያውቁ ነበር ያሉት ሮዳስ (ዶ/ር)፣ዘመናዊው ሳይንስ የዑደታትን ነገር ከመናገሩ በፊት በጥልቀት ተረድተው ስያሜያቸውን “አዕዋዳት” ማለታቸውን አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ቀደምት የሥነ ፈለክ ሊቃውንት የሚታወቁ ሰባት አዕዋዳት መኖራቸውን በመግለጽ፣ ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኀ፣ ዐውደ ዓመት፣ ዐውደ አበቅቴ፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ ማኅተምና ዐውደ ቀመር እንደሚባሉም ገልጸዋል፡፡

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ፀሐይ ወጥቶ እስኪገባ ያለውን 12ቱን የሥራ ጊዜ “መዓልት” ብለው ሠይመውታል ያሉት መጋቢ ሀዲስ፣ ይኸውም “መዋል፣ ውሎ፣ ከጧት እስከ ማታ ሥራ ሲሠሩበት የሚውሉበት” ማለት ነው ብለዋል፡፡

ቀን “ተቀንየ” ማለት “ተገዛ፣ ተሠራ፣ አገለጋይ ሆነ” የሰዎች የሥራ መሥሪያ ጊዜ ማለት መሆኑን ጠቅሰው፣ የጨለማውን ጊዜ “ሌሊት” የሚል ሥያሜን የሰጡ ሲሆን፣ ከማታ እስከ ጧት ከኮከብና ከጨረቃ በቀር ፀሐይ የማይታይበት ዐሥራ ሁለቱ ሰዓት መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

መዓልትና ሌሊትን በአንድ ላይ የሚሰጡት 24 ሰዓት ወይም 1440 ደቂቃ ቀደምት ኢትዮጵያውያን “ዕለት” የሚል ፍቺን እንደሰጡት ገልጸው፣ በዕለት ከሚቆጠሩት ከሰባቱ አዕዋዳት ውስጥ የመጀመሪያው “ዐውደ ዕለት” ከእሑድ እስከ ቀዳሚት ያሉት ሰባቱ ዕለታት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ዐውደ ወርኀ (የወር ዑደት) በፀሐይ ዘወትር ሠላሳ፤ በጨረቃ አቆጣጠር ሃያ ዘጠኝ ዕለት እንደሆነ ለመግለጽ ያደረጉት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በኢትጵያውያኑ የዘመን ቀመር አሠራር በፀሐይና በጨረቃ አቆጣጠር ተቀምሮ ዐውደ ዓመት እንደሚባል ጠቅሰው፣ አንድ ዓመት እንደ ፀሐይ አቆጣጠር 365 ዕለት ከ6 ሰዓት ከ2 ደቂቃ፣ እንደ ጨረቃ ደግሞ 354 ዕለት ከ8 ሰዓት፤ ከ48 ደቂቃ ከ39 ሴኮንድ እንደሚሆን አስረድተዋል፡፡

ዐውደ አበቅቴ በዓመት የሚቆጠር ሲሆን በ19 ዓመት ፀሐይና ጨረቃ መንገዳቸውን ጨርሰው በተፈጠሩበት ጥኅት (ደጃፍ) እንደሚገናኙ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች ማስቀመጣቸውን ተናግረዋል፡፡

ዐውደ ፀሐይ የ28 ዓመት ዑደት ሲሆን በ28 ዓመቱ እንደገና በመጀመሪያው ጊዜ በገባበት ዕለት መልሶ ዐዲስ ዓመት ላይ እንደሚገባ ጠቅሰው፣ዐውደ ማኅተም የ76 ዓመት ዑደት ሲሆን አበቅቴና ወንጌላዊ በ76 ዓመት ዞረው እንደሚገናኙበት ተናግረዋል፡፡

ዐቢይ ቀመር በመባል የሚታወቀው ዐውደ ቀመር የዑደቱ ዘመን 532 መሆኑን በመግለጽ፣ በየ 532 ዓመቱ የዐዲሱ ዓመት መግቢያ ዕለት፣ ወንጌላዊ፣ አበቅቴ እኒህ 3ቱ እንደሚገናኙበት አስረድተዋል፡፡

በትንሣኤ በዓል አከባበር ላይ የ11 ዕለታት ልዩነት በ1582 ዓ.ም. ላይ መጀመሩን ጠቅሰው፣ በሮማ ካቶሊክ መሪ በፓፕ ጎርጎርዮስ 13ኛ ውሳኔ ማስተላለፋቸውን ተከትሎ የዘመን አቆጣጠር ጎርጎርዮሳዊ የዘመን ቀመር እንደሚባል ጠቁመዋል፡፡

የፓፕ ጎርጎርዮስ 11 ዕለታት ጭማሪ አስቀድሞ ተቀባይነት ያገኘው በካቶሊክና በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በበዙበት ሀገራት እንደነበር ጠቅሰው፣ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ግን ተቀባይነት አለማግኘቱን አስረድተዋል፡፡

የምሥራቅ አኃት አብያተ ክርስቲያናትም የተደረገውን ጭማሪ ባለመቀበል እስካሁን በጥንቱ መቀጠላቸውን ገልጸው፣ ኢራንና አፍጋኒስታንም ይህን የጎርጎርዮስን ውሳኔ ባለመቀበል የሚታወቁ ሀገራት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

የአፍሪካ ሀገራት በምዕራባውያን በቅኝ በመገዛታቸው የዘመን ቀመራቸውን በግዴታ ወደ ጎርጎርዮሳዊ መለወጣቸውን በመግለጽ፣ ኢትዮጵያ ግን በባርነት ያልኖረችና በቅኝ ገዢዎች ያልተያዘች በመሆኑ የጎርጎርዮስን ጭማሪ አለመቀበሏልን አስረድተዋል፡፡

ሕንድ፣ ባንግላዲሽ፣ ኔፓል፣ ፓኪስታን፣ እስራኤል፣ ማይናማር ደግሞ ከራሳቸው የዘመን ቀመር ጋር በትይዩ የጎርጎርዮሳዊ የዘመን ቀመርን እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል፡፡

ልዩ ዕትም

# እንኳን ለአዲሱ ዓመት
## አደረሰን፣ አደረሳችሁ!

በሽርፍራፊ ሰከንዶች ልኬት፣ በቀናት እና ወራት ስሌት፣ በዓመታት ተቀምሮ ዘመን ዘመንን ሲተካ፤ የሰው ልጆችም ሕልምና ርዕይ፣ ተስፋና መንገድ አብሮ ይታደሳል፤ ቃልን በተግባር ለውጦ ለስኬት እንዲበቃም ይተጋል። ኢትዮጵያውያን ደግሞ በዚህ ረገድ ልዩ የሚሆኑበት አያሌ ጉዳዮች አሏቸው። አንዱ ዘመንን በራሳቸው ቀመር ለክተው መለወጣቸው ሲሆን፤ የዘመን ስሌታቸው በሚሰጣቸው አዲስ ዓመት፣ በአዲስ ተስፋና መንገድን ለተሻለ ነገር መትጋታቸውም የዚሁ አንድ አካል ነው።

አዲስ ዓመት ሲመጣ፣ ከእንኳን አደረሰህ/ሽ ከመባባል ባለፈም፤ ዘመኑ የሰላም፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ፣ የመለወጥ፣ የስኬት እና የተሻለ ነገር ማግኛና ማሳኪያ እንዲሆን መልካም ምኞትን መግለጽም ሌላኛው የኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ የመተሳሰብና መተሳሰራችን አስኳል ነው። ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያውያን ለሌሎች መልካምን በመመኘት ውስጥ ለራሳችን መልካም ነገርን እንደምናገኝ እናምናለን። ቸር በማሰብ ውስጥ ቸር ማግኘትን፤ ስኬትን በማለም ውስጥ ስኬታማ መሆንን፤… በወጉ እንገነዘባለን።

እናም እንኳን አደረሳችሁ በማለት ውስጥ፣ ምስጋናን፤ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የፍቅር፣ የስኬት፣ የጤና፣ የመተሳሰብ፣… ይሁንላችሁ በማለት ውስጥ፣ መልካም ነገርን ለሌሎችም፣ ለራሳችንም እንጋብዛለን። ምክንያቱም፣ አመስጋኝ ሰው ለተሻለ ስኬት የሚንደረደርበትን ዕድልም አቅምም ያገኛል። በተመሳሳይ፣ መልካም ነገርን የሚመኝ ሰው በተመኘውና ባሰበው ልክ እንዲደርስ የሚያስችለውን የትጋትም የጽናትም ልዕልናን ይጎናጸፋል።

ከዚህ አኳያ የ2016 ዓመተ ምሕረትን የበዙ ፈተናዎች ተሻግሮ፣ የበዙ መልካም ተግባራትንም ከውኖ ወደ 2017 ዓመተ ምህረት የተሸጋገረን ሕዝብና ወገን፣ እንኳን አደረሰህ ማለቱ፤ ያለፈውን መልካምም ክፉም ነገር አሳልፎ አዲሱን ዓመት እንድናይ ላደረገ ፈጣሪ የምስጋና ቃል ማውጣት ነው። አመስጋኝነት ደግሞ መባረክን ያመጣል። በመባረክ ውስጥ ደግሞ መተሳሰብ፣ ፍቅርና አንድነት፣ ሰላምና ይቅር ባይነት፣… የመሳሰሉ ከፍ ያሉ የሰው ልጅ እሴቶች ባለቤት መሆንን ይወልዳል።

ይሄን የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ታዲያ፣ ከእንኳን አደረሰህ/ሽ የምስጋና ቃላቸው ቀጥለው፤ አዲሱ ዓመት የመልካም ነገሮች ማግኛና መፈጸሚያ እንዲሆን ይመኛሉ። ይሄ ምኞታቸው ታዲያ በአመስጋኝነት ውስጥ የሚገኝን የሰው ልጆች ከፍ ያለ የሰብዕና እሴቶች ስለሚገነዘቡ ነው። ምክንያቱም፣ የሰው ልጅ ሰላም ሲሆን ሃሳቡም መንገዱም ሰላማዊ ነው። ይሄ የግለሰቦች ሰላማዊነት ሲደመር ደግሞ እንደ ማኅበረሰብም፣ እንደ ሕዝብና ሀገርም የሚፈለገውን ሰላም ያዋልዳል።

ሰላም ሲወለድ ደግሞ፣ ፍቅር፣ አብሮነት፣ መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ ለጋራ ሕልምና ራዕይ በጋራ መቆም፣ ስለ ሀገርና ሕዝብ ሁለንተናዊ ብልጽግና መትጋት ተከትለው ይወለዳሉ። እነዚህ ሲደመሩ ሀገር እንደ ሀገር፣ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ካለፈው ዓመት የተሻለ እንዲያስብ፣ እንዲያቅድ፣ እንዲተገብር እና እቅድና ሕልሙንም እንዲያሳካ የሚችልበትን ከፍ ያለ ትጋትን፣ ቁርጠኝነትና ጽናትን ያጎናጽፉታል። እንደ ሀገር ሉዓላዊነትና ነጻነትን፤ እንደ ሕዝብም ክብርና አይበገሬነትን፤ በጥቅሉ ከፍ ያለውን የሀገርም የዜግነትም ልዕልና ለመጎናጸፍ አቅም ይሰጣሉ።

በመሆኑም፣ ዛሬ ላይ አሮጌ ያልነውን 2016 ዓ.ም ሸኝተን፣ አዲስ ያልነውን 2017 ዓ.ም ስንቀበልና አዲሱን ዓመት አንድ ብለን ስንጀምር፤ ከእንኳን አደረሳችሁ የምስጋና መግለጫ በኋላ፣ የመልካም ምኞት መግለጫዎቻችንን የምናስከትለው። ይሄ መልካም እሴት፣ መልካም መተሳሰብ ነው። ዋናው ጉዳይ ግን፤ ይሄ የምስጋና እና የመልካም ምኞት ቃላችን፤ ከቃል ያለፈ ሆኖ እንዲገለጥ በማድረግ ውስጥ የእኔ ድርሻ ምንድን ነው፣ በምን መልኩስ ልወጣ ይገባኛል፣ የሚለውን በልኩ ተገንዝቦ በመሥራት መግለጥ መቻሉ ነው።

ምክንያቱም፣ ብዙዎች የሚናገሩትን አይኖሩም፤ የሚመኙትን ለማግኘት አይተጉም፤ የሚራመዱበትን መንገድ እንኳን በቅጡ ሳይገነዘቡ ከፍጻሜ የማይደርሱበት አካሄድ ይስተዋላል። ይሄን መሰሉ አካሄድ ደግሞ እንደ ሀገርም ሆነ ሕዝብ በአዲሱ ዓመት ልንሆን ከምናቅደውም፣ ልንደርስበት ከምንጓዘውም አኳያ ጎታች ሆኖ የሚገለጥ ነው። በመሆኑም አዲሱን ዓመት በምስጋና ስንጀምር፤ ዓመቱንም በመልካም ምኞት ስንዋጅ፣ በተናገርነው ልክ ሆኖ መገኘትን ታሳቢ ማድረግ አለብን።

ለምሳሌ፣ ዓመቱ የሰላም እንዲሆን ስንመኝ፣ ለሰላም የድርሻችንን በመወጣት ሊሆን ይገባል። የመተሳሰብና የመደጋገፍ እንዲሆን ስንመኝም፣ ሠብዓዊነትን በመግለጥ ሊሆን ይገባል። የፍቅርና የይቅርታ እንዲሆን ስንመኝም፤ ፍቅርን እና ይቅርታን በተግባር እየገለጥን ሊሆን ይገባል።

ዓመቱ የብልጽግና እንዲሆን ስንመኝም፤ አንድ ሀገርና ሕዝብ ሁለንተናዊ ብልጽግናቸው እውን የሚሆንበትን መንገድ አቅዶ ለዛ እቅድ መሳካት የድርሻችንን በመወጣት ሊሆን ይገባል። በመሆኑም የአዲሱን ዓመት የእንኳን አደረሰን፣ አደረሳችሁ መልዕክት ስናስተላልፍ፤ የዓመቱንም ጉዞ የመልካም ነገር መከወኛ እንዲሆን ስንመኝ፤ ምስጋና እና ምኞታችን በተግባር የሚገለጥበት ሠብዓዊ እሴትን በመላበስ ሊሆን ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# አዲሱ ዓመት ለአዲስ ሀገራዊ ተስፋ

ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ

የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ኢትዮጵያ፣ 2017 ዓ.ምን ተቀብላለች። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሀገሪቱና ዜጎቿ መስከረም ሲጠባ መልካሙን ተመኝተውና አልመው የነበረ ቢሆንም፣ የሰላም እጦት፣ የዜጎች አሰቃቂ ሞትና መፈናቀል፣ የሀብት ዝርፊያና ውድመት … ደጋግመው ጎብኝተዋቸዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ኢትዮጵያ በሰላም እጦት በእጅጉ ተፈትናለች። ይህ የሰላም እጦት ዜጎች ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን እንዲያጡ በማድረግ ከፍተኛ ኅብረተሰባዊ ቀውስ ፈጥሯል። መንግሥት የኅብረተሰቡን ሰላም ለማስጠበቅ ልዩ ልዩ ጥረቶችን አድርጎ በጥቂት የሀገሪቱ አካባቢዎች አንፃራዊ ሰላም ቢሰፍንም፣ አሁንም አስከፊ የሕይወት መስዋዕትነት እያስከፈሉና ከፍተኛ የንብረት ውድመት እያስከተሉ ያሉ ግጭቶች አሉ። ስለሆነም በአዲሱ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ዐበይት ትኩረቶች ሊሆኑ ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል ዋናው ሰላምን ማስፈን ነው።

ሰላም ከሰላም ስብከት የተሻገረ ሃቀኛ ቁርጠኝነትን ይፈልጋል። ለሰላም ዋጋ መክፈል መሸነፍ አይደለም። በአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት የተቃኘው የፖለቲካ ባህላችን ለሰላም የሚከፈልን ዋጋ እንደሽንፈት ይቆጥረዋል። ሕዝብ ሰላምን በእጅጉ ይሻል፤ ሕዝብ ለሚፈልገው ነገር ቅድሚያ መስጠት ደግሞ ሕዝብን ማክበር ሀገርንም መውደድ ነው። የሰላም በሮችን እየዘጉና የሰላም አማራጮችን እየገፉ ‹‹ሕዝብ ይወደኛል፣ የምታገለው ለሕዝብ ነው…›› ማለት ትልቅ ስላቅ ነው። ‹‹ሰላም ወዳድ›› ለመባል ብቻ ስለሰላም መስበክም ለውጥ አያመጣም። ግጭቶች በተራዘሙ ቁጥር ሥርዓት አልበኝነት እንደሚነሰራፋ፣ የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት በእጅጉ እንደሚዳከም እንዲሁም ዜጎች በሀገራቸው ተስፋ እንደሚቆርጡ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ሰላምን ለማስፈን የሚከፈል ዋጋ ዘላቂ ትርፍ የሚያስገኝ ቅዱስ ተግባር ነው።

ሌላው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ ሀገራዊ አንድነትን ማስጠበቅ ነው። ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ-ፖለቲካዊ ቀጣና የዓለምን ትኩረት የሚስብ አካባቢ ነው። ይህ ቀጣና በየጊዜው በፍጥነት የሚለዋወጡ ክስተቶችን የሚያስተናግድ በመሆኑ ኢትዮጵያም ለዚሁ የቀጣናው ነባራዊ ሁኔታ ተጋላጭ ናት። ከሩቅም ከቅርብም ያሉት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ኢትዮጵያን በመጉዳት ‹‹ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ›› ሲታትሩ እንደኖሩ በግልፅ የሚታወቅ ሃቅ ነው። በቅርቡ እንደታዘብነው የሀገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች የሀገር ውስጥና የጎረቤት ፈረሶቻቸውን ተጠቅመው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ አደጋ ለመደቀን ደፋ ቀና እያሉ ነው።

ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ መቆየት የቻለችው በሕዝቧ አንድነት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው ከውስጥና ከውጭ የተነሱበትን ጠላቶች ድል ያደረገው አንድነቱን ጠብቆ በጋራ በመተባበሩ ነው። ታዲያ በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያንዣበቡትን የጠላት ክንፎች ለመስበር በሀገር ውስጥ ሰላምና ፍትህን ማስፈን ይገባል። በሰላም እጦትና በኢፍትሃዊነት የተማረረ ሕዝብ ለውጭ ጠላቶች መጠቀሚያ እንዳይሆን የቤት ሥራን (ሰላምና ፍትሕ የማስፈን ሥራዎችን) ቀድሞ ማጠናቀቅ ያስፈልጋል።

የምጣኔ ሀብት ጉዳይም ትኩረት የሚፈልግ ወሳኝ ሀገራዊ አጀንዳ ሊሆን ይገባል። የእቃዎችና የአገልግሎት ዋጋ በየጊዜው ማሻቀብ እንጂ ዝቅ ማለት አልሆነለትም። ይህም የኅብረተሰቡን፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል፣ ኑሮ እጅግ የከበደ እንዲሆን አድርጎታል። ለዋጋ ንረቱ የተለያዩ ምክንያቶች ዛሬም ድረስ እየተጠቀሱ ቢዘልቁም፣ እነዚህ ምክንያቶች ኑሮ ናላውን ላዞረው ኅብረተሰብ ምንም አይፈይዱም። ‹‹ኑሮውን አልቻልነውም … የዋጋ ንረቱ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል …›› የሚሉና ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሲደመጡ የቆዩ የኅብረተሰብ ድምፆች ዛሬም መስተጋባታቸውን ቀጥለዋል።

መንግሥት የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ዘርፈ ብዙ የአጭርና የረጅም ጊዜ የመፍትሄ አማራጮችን በመተግበር ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ይሁን እንጂ እነዚህ ርምጃዎች ሥር ለሰደደው ችግር አጥጋቢ መፍትሄ አስገኝተዋል ለማለት አያስደፍርም። የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እጅግ ውስብስብ በሆነ የደላሎች ወጥመድ ውስጥ በመውደቁ፣ አንዳንድ ጊዜ ችግሩ የት እንዳለ ለመለየት እንኳ ያስቸግራል። ታዲያ ችግሩን ከመለየት ጀምሮ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እንዲሁም የሀገር ፍቅርና ሙያ ያለው አመራርና ባለሙያ ያስፈልጋል።

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ወደተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ያሸጋግራል የተባለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር፣ የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ በከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ መሥራት ይገባል። በዚህ ረገድ የህብረተሰቡንና የባለሙያዎችን ሃሳብ ማዳመጥ፣ ማሻሻያው ስኬታማ እንዳይሆን ችግር በሚፈጥሩ ተቋማትና ግለሰቦች ላይ የማያዳግም ርምጃ መውሰድ እንዲሁም ማሻሻያውን በብቃት ለመተግበር የሚያግዙ ተቋማትን ማደራጀትና ማጠናከር ያስፈልጋል።

አዲሱን ዓመት ስንቀበል ከምንሰናበተው አሮጌ ዓመት ጋር አብረው የማይሰናበቱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። በአዲሱ ዓመት ሊከናወኑ የሚገባቸው ብዙ ሥራዎችም አሉ። ኢትዮጵያ ብዙ ሺ ዓመታትን ባስቆጠረው እድሜዋ ‹‹ረሃብንና ጦርነትን ደጋግማ የማስተናገዷ ምክንያት ምንድን ነው? ደጋግመው ካጋጠሟት ችግሮቿ መላቀቅ ያልቻለችውስ ለምን ይሆን?›› የሚለው ጥያቄ የሰከነ ውይይትና አጥጋቢ ምላሽ የሚፈልግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ነፃነት፣ ክብርና አንድነት ሲሉ በዓድዋና በሌሎች ሥፍራዎች ለማመን የሚከብዱ ከባድና አኩሪ ተጋድሎዎችን አድርገው ነፃ አገር ለ‹‹ተተኪው ትውልድ›› ቢያስረክቡም ‹‹ተተኪው ትውልድ›› (በተለይ ልሂቃኑ) ግን እነዚያ መስዋዕትነቶች ያስገኟቸውን በረከቶች በመመንዘር ለታላቅ ሀገር ግንባታ ግብዓትነት ሊጠቀምባቸው አልቻለም። ታዲያ ይህን የባከነ እድል በእልህና በቁጭት የመጠቀም ኃላፊነት የወደቀው በዚህ፣ በእኛ ትውልድ ላይ ነው። ይህ ትውልድ በብሔርና በሃይማኖት ተከፋፍሎ ሀገር ለማፍረስ የሚደረገውን አሳዛኝና አሳፋሪ ግብግብ የመታገልና የመመከት አደራ አለበት። የተረሳውና የባከነው የቀደምት ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ትርጉም እንዲኖረው እልህ አስጨራሽ ትግል ይጠብቀዋልና ለትግሉ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ መነሳት ይጠበቅበታል።

ታዲያ ቅንነት፣ ትጋትና ፅናት ተላብሶ የሀገሪቱን ችግሮች ለመፍታት በቅድሚያ የምክንያታዊ አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ያስፈልጋል። ምክንያታዊ አስተሳሰብ በሌለበት ቦታ፣ ትርጉም ያለውና ተጨባጭ የሆነ ለውጥን ማሳካት አይቻልም። ኢትዮጵያ ‹‹ለምን?›› እና ‹‹እንዴት?›› ብሎ ለመጠያየቅ፣ ለመከራከርና ለመወያየት የሚያስችል የሠለጠነ ባህል አላዳበረችም። ማሰብን፣ ማሰላሰልን፣ ሚዛናዊ ዕይታንና መመርመርን የሚጠይቀው እንዲሁም ‹‹ምን?››፣ ‹‹እንዴት?››፣ ‹‹ለምን?››፣ ‹‹መቼ?››፣ ‹‹የት?›› የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ መሠረታዊና አመክንዮን የተከተሉ ወሳኝ ጥያቄዎችን በማንሳት እውነትን ከሐሰት አብጠርጥሮ የማጥራት እሳቤን የያዘው ምክንያታዊነት የተባለው ጽንሰ ሃሳብ ቦታ ሊያገኝ ይገባል።

ታላቅ ሀገር ለመገንባትና የኃያል ሀገር ባለቤት ለመሆን የታላቅና በጎ አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው መንገዶቿ በጥልቀት ተፈትሸው፤ችግሮቿና ስብራቶቿ በግልጽ ውይይት ተደርጎባቸው የእስካሁኑን የኋልዮሽ ጉዞዋን በማስቆም ወደፊት እንድትራመድ ማድረግ ይገባል። ለተደጋጋሚ ረሃብና ጦርነት የዳረጓትና ከተለመደና ከተሰለቸ የ ‹‹ታላቅነት›› ወሬ ተሻግራ እውነተኛ ኃያልነትን እንዳትላበስ ያደረጓት የዘመናት ሰንኮፎቿ በግልጽ ሊነገሩና ምላሽ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል! ኢትዮጵያ ችግሮቿን በግልጽ የሚናገርላትና መፍትሄ የሚፈልግላት ልጅ/ትውልድ ትሻለች!

ምክንያታዊ አስተሳሰብን ባህሉ ያደረገ ትውልድ የመገንባት ተግባር በአንድ ጀንበር፣ በአንድ ዓመት የሚሳካ ባይሆንም ጉዞው ከአሁኑ መጀመር አለበት። ይህ ትውልድ ምክንያታዊ ትውልድ የመሆን ግዴታ ወድቆበታል። ይህን ግዴታ በብቃት አለመወጣት ግን ሀገርን የሚያሳጣ አደገኛ ዋጋ ያስከፍላል። አዲሱ ዓመት ደግሞ በአዲስ ሀገራዊ ተስፋ ስለኢትዮጵያ ችግሮች በግልጽ ተነጋግሮና ተማምኖ እውነተኛና ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የሚደረጉበት ሊሆን ይገባል! ተደጋጋሚ መከራዎች ወገቧን ያጎበጧት እናት ኢትዮጵያም ከዚህ በላይ ለመጠበቅና ጊዜ ለማባከን ዝግጁና ብቁ አይደለችም!

# የኢትዮጵያን መለያ የሆነውን የዘመን አቆጣጠራችን

**አመስወርቅ ከበደ**

ኢትዮጵያ በመንግስት የዘመን አቆጣጥር ደረጃ የምትቀበለው ከዓለም ሀገራት የተለየ የዘመን አቆጣጥር አላት። ይህንንም የራሷ መለያ አድርጋ 13 የፀጋ ወራት በሚል ስትጠቀም ኖራለች። የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር መሰረት፣ ስሌት እና ከሌሎች የዓለም ሀገራት የተለየበትን ምክንያት በተመለከተ የባህረ ሃሳብ ባለሙያ ከሆኑት መምህር ሔኖክ ያሬድ ፈንታ ጋር የዝግጅት ክፍላችን ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ!



መምህር ሔኖክ ያሬድ

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ ስለኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ይንገሩን?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ኢትዮጵያ ከተወሰነ ዓመታት ወዲህ እንደራሷ መለያ አድርጋ ከምትጠቀማቸው፣ አንዱ ምድረቀደምት የሚለው ስያሜ ነው። ምድረ ቀደምት ከሚያሰኛት አንዱ ጥንታዊ የዘመን አቆጣጠሯ ነው። ይሄም ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የኖረ ነው። ከ60 ዓመታት በላይ የቱሪዝም ማስታወቂያ የነበረው 13 የፀጋ ወራት ተብሎ የሚታወቀውም አንዱ መለያችን ሆኖ ቆይቷል።

በእርግጥ ጥንታዊያን ይሄን የ13 ወር አውድ ይጠቀሙ ነበር፤ በግዜ ሂደት ትተውታል። በአሁን ግዜ በሀገር፣ በመንግስት እና በቤተክርስትያን ደረጃ 13 ወር በማለት ኢትዮጵያ ትለያለች። ግብፅ በመንግስት ደረጃ ባይጠቀሙም የግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ግን 13 ወር በማለት ትጠቀማለች።

13 ወራት ስንል አንዳቸው 30 ቀናት ያሉት 12 ወራት አሉት፤ የመጨረሻው ደግሞ አምስት ወይም ስድስት ቀን አለች። ለዚህ ነው እንግዲህ ይችን ንውስ ወር ልዩ የሚያደርጋት እና ጳጉሜን ብለን የምንጠራት። ስለዚህ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ብለን ስናስብ መነሻ የሆኑ የተለያዩ አቆጣጠሮችን ጭምር በማሰብ ነው።

በዓለም ዙሪያ መደበኛው ካሌንደር እኛም ጋር በተጓዳኝ ያለው የጊርጎሪያን አቆጣጠር ነው። በልማት የአውሮፓውያን አቆጣጠር ተብሎ የሚታወቀው፤ በዓለም ሁሉም የራሱ ባህላዊ የዘመን አቆጣጠር ቢኖረውም በመደበኛነት የጊርጎሪያን ዘመን አቆጣጠር ይጠቀማሉ።

የጊርጎሪያን የዘመን አቆጣጠር ለመጠቀም መሰረት የሚያደርገው አቆጣጠሩ እራሱ ከቤተክርስትያን አቆጣጠር ጋር የተያያዘ ነው። ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር ተያይዞ ነው የሚቆጥረው። ልክ ለዓለም ሁሉ ጊርጎሪያን መሰረት እንደሆነው፤ ለኢትዮጵያም የዘመን አቆጣጠር መሰረት የሆነዉ የቤተክርስትያን አቆጣጠር ነው።

ስለዚህ አሁን የምንቀበለው አዲሱ ዓመት 2017 ዓ.ም ብለን እንጠቅሳለን። 2017 ስንል ከጌታችን ልደት ተነስተን የምንቆጥረው፤ ከመስከረም አንድ ጀምሮ የምናወሳው መንገድ ነው። ይህ ብቻ አይደለም የኢትዮጵያ አቆጣጠር ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ የምንቆጥርበትም መንገድ አለ። ይህ ደግሞ ዓመተ ዓለም ተብሎ የሚታወቅ ነው።

ዓመተ ዓለም ማለት ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን 5500 ዓመት ላይ 2017 ስንደምር 7517 ዓመተ ዓለም፤ በኢትዮጵያ አነጋገር ስምንተኛው ሺህ ማለት ነው። ስምንተኛው ሺህ የገባው አንድ ሺህ 501 ዓ.ም ላይ ነው ። አሁን ስምንተኛው ሺህ ከገባ 517 ዓመት ላይ እንገኛለን።

ስለዚህ የዓመተ ዓለም አቆጣጠር አለን፤ የዓ.ም አቆጣጠርም አለን። ይሄ በፀሀይ ላይ የተመሰረተው አቆጣጠራችን ነው። የቀኑን ብርሃን የቀን ቁጥር ብለን እንደምንቆጥረው ሁሉ፤ የማታው ደግሞ የራሱ የሆነ ቁጥር አለው። የማታው አቆጣጠር ሁሉንም ኢትዮጵያውያንን የሚያገናኝ ጭምር ነው። በተለይ ቤተ እስራኤሎች፣ አይሁድም በጨረቃ ነው የሚቆጥሩት፤ የሙስሊም ወንድሞችም በሂጅራ ሲቆጥሩ ጨረቃ ነው የሚጠቀሙት።

ስለዚህ በጨረቃ አቆጣጠር ደግሞ ተመሳሳይነት አለ። ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክበት የተፈጠሩት ለብርሃንነት ነው። ስለዚህ የጨረቃ አቆጣጠርም አለ። የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ስንል የፀሀዩን ብቻ እናነሳና 2017 እንላለን። ሌላው በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ውስጥ ከጨረቃ ጋር የተያያዙ በዓላትን የምንለይበት የጨረቃና የፀሀይ ጥምር አቆጣጠር አለ። ይሄ ‹‹ዩኒሶላር›› የምንለው ነው።

አምና 2016 ዓ.ም ፋሲካ ሚያዚያ፣ 27 ነው የዋለው። በጨረቃ ምክንያት ዘንድሮ 2017 ሚዚያ 12 ነው የሚውለው። መስከረም አንድ ቀን በፀሀይ

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## ልዩ ዕትም

# የኢትዮጵያን መለያ የሆነውን ...

ከገጽ 8 የዞረ

አቆጣጠር 2017 ዓ.ም ገብቷል። በፀሀይና በጨረቃ ጥምር አቆጣጠር 2025 ዓ.ም ገብቷል። ስለዚህ ሁለት ምሶሶዎች አሉ ማለት ነው።

ቤተክርስትያን ደረጃ ሁለቱንም አቆጣጠር እንጠቀማለን። በሕዝብ አቆጣጠር ግን መስከረም አንድ እንቁጣጣሽ ብለን አዲስ ዘመንን 2017 ብሎ ተቀብሏል። በተክርስትያን መሰረት ሆና ይሄንኑ መስከረም አንድ ስትቀበል ስም አላት፤ ቅዱስ ዮሐንስ ብላ ትጠራዋለች።

እያንዳድኑን ዓመት ደግሞ በቤተክርስትያን ደረጃ በወንጌላውያን ስም ትሰይመዋላች። አሁን በሸኘነው 2016 ዮሐንስ አበቃ፤ በዚህም የአራት ዓመት ዙር አብቅቷል። አሁን አዲስ አራት ዓመት ነው ምንጀምረው። መደበኛውንም አቆጣጠር ያስገኘው የቤተክርስትያኑ አቆጣጠር ነው ብለን መግለጽ እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጨረቃና በፀሀይ ጥምር አቆጣጠር 2025 መሆኑን ገልጸዋልና፤ ይሄኛው አቆጣጠር በሕዝብ በዙም አይታወቅም። እንዴት ነው ስሌቱ?**

**መምህር ሔኖክ፡-** መሰረቱ አሪት ዘፍጥረት ላይ፤ መጀመሪያ እግዚያብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ብሎ፤ ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃን ሆነ። በአራተኛው ቀን ብርሃናትን ለያቸው። ትልቁ ብርሃን ፀሀይ ቀንን እንዲገዛ፤ ትንሹ ጨረቃ ከከዋክብት ጋር ምሽትን እንዲያስተዳድር አደረገ። እነዚህን ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክበት ለአራት ነገር ነው የተፈጠሩት።

አራቱ ነገሮች ምንድናቸው፤ ምልክቶች አለ፤ ምልክቶች ሲል በዓሎች፣ ጾሞች እና ለአራቱ ወቅቶች፤ በእኛ ክረምት፣ መጸው፣ በጋ እና በልግ የሚባለው ነው። በፀሀይ ዓመት ላይ የተመሰረተው አቆጣጠር እነዚህን አራቱን ወቅቶች ያፈራርቃል። ሌላኛው ደግሞ ለእለታት አለ፤ አንድ ሳምንት ሰባት ቀን፣ አንድ ወር 30 ቀን፣ አንድ ዓመት 365 ቀን በፀሀይ፣ በጨረቃ 354 ቀን ነው። የጨረቃ ኡደት አጭር ነው ከፀሀይ በ11 ቀን ልዩነት አላት።

መሬት ፀሀይ ዞራ የምትፈጽምበት 365 ቀን ከስድስት ሰዓት ነው። ስለዚህ ይህ ስድስት ሰዓት በአራት ዓመት አንዴ ጳጉሜ ስድስት ቀን እንዲሆን ታደርጋለች፤ አራት ጊዜ ስድስት 24 ሰዓት ሆና።

ሙስሊሞች ጨረቃን አይተው ጾም ይይዛሉ። እኛም ኦርቶዶክሶች ጨረቃን አይተን ጾም እንይዛለን። የአይሁዶችን እንደዚሁ ነው። ፋሲካና የዓብይ ጾም የሚቀያየረው ከጨረቃ ጋር ተያይዞ ስለሚቆጠር ነው። ስለዚህ ይህን ለማወቅ የጨረቃና የፀሀይ ጥምር አቆጣጠር አለ። 2017 ዓ.ም ላይ ስምንት የምንደምርበት የጨረቃዋን ኡደት አምጥተን ነው።

ጨረቃ መጀመሪያ ጭረት ነች፣ ከዛን ማጭድ፣ እሩብ እየሆነች፣ ኢጋማሽ ......እየሆነች መጨረሻ ላይ ሙሉ ትሆናለች። ከዛ ደግሞ እየጎደለች ትሄዳች። ስምንትን የምንደምረው የጨረቃዋን ኡድት መሰረት አድርገን ነው። ስምንት ቋሚ ቁጥር ናት። ስምንት ሁልግዜ በየዓመቱ ትደመራለች ምክንቱም የጨረቃን ስሌት ስለምታመጣ። 2017 ብቻውን አያመጣም።

የሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ላይ "ቀንንና ወርን ዘመንን፣ ዓመትን በጥንቃቄ ትጠብቃላቹ" ይላል። ምክንያቱም ጨረቃን አይተን ነዋ። ጨረቃ ኡደቷ 29 ነጥብ አምስት ነው። 29 ነጥብ አምስት ሲባዛ በአስራ ሁለት ወራት 354 ይመጣል። ስለዚህ መስከረም አንድ ላይ 2017 እና 2025 ዓ.ም ገብቷል፤ 7517 ዓመተ ዓለም ገብቷል እንላለን።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከሌሎች የዘመን አቆጣጠር የተለየበት ምክንያት ምንድ ነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ማንም ሕብረተሰብ የራሱ የሆነ የዘመን አቆጣጠር አለው። መደበኛ የሆነው አቆጣጠር የመጣው የክርስቶስን ልደት ተከትሎ ነው። አውሮፓውያኑ መነሻ የሚደርጉት እና እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው አቆጣጠራቸው ከሮም ከተማ ጋር ተያይዞ ነው። ሮም ከተመሰረተችበት ዓመት አንድ ብለው ነው የሚጀምሩት።



መምህር ሔኖክ ያሬድ

**ማንም ሕብረተሰብ የራሱ የሆነ የዘመን አቆጣጠር አለው። መደበኛ የሆነው አቆጣጠር የመጣው የክርስቶስን ልደት ተከትሎ ነው። አውሮፓውያኑ መነሻ የሚደርጉት እና እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው አቆጣጠራቸው ከሮም ከተማ ጋር ተያይዞ ነው። ሮም ከተመሰረተችበት ዓመት አንድ ብለው ነው የሚጀምሩት።**

ጌታችን ሲወለድ ሮም በተመሰረተች 753 ዓመት ላይ ነው። ዲዮናሲዮስ ኤግስጊዮስ የሚባል እስክንድርያ በመሄድ በ532 ዓ.ም አምኖ ዶሚኒ (ኤ. ዲ) ወይም የጌታ ዓመት በማለት አቆጣጠሩ ከጌታ ልደት ጋር ተያይዞ እንዲነሳ አደረገ። በተለይ የፋሲካ ቀን አወጣጥን ተከትሎ የእስክንድሪያ ጳጳሳት ናቸው የሚያወጡት። ከእነሱ ነው ያጠናው።

በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እነ አባ ዲሜጥሮስ የተከሉት ቱፊት ቀጥሎ፤ እሱ ሄዶ ያንን ሲያጠና፤ ‹‹የሶላርን ››እና ‹‹የዩኒሶላርን›› አቆጣጠር ነው ያሳዩት። እሱ በሄደበት ወቅት በፀሀይ 524 ነው። በጨረቃ እና በፀሀይ ጥምር አቆጣጠር ደግሞ 532 ዓመት ነው። እሱ ግን ስምንት የሚደመርባት አቆጣጠር ያዘና በዛው ቀጠለ።

ከዛን ለዓለምም አስተዋወቀው፤ ሌሎች ዓለማት ‹‹ዩኒሶላሩን››፤ ‹‹ሶላር›› አድርገው ነው የቀጠሉት። እኛ ግን ሁለቱንም ጎን ለጎን አድርገን ነው የቀጠልነው። ልዩነቱ የመጣው ለዚያ ነው።

ከዛ ደግሞ የወር አመዳደባችን ይለያል፤ የዓመት መነሻችንም ይለያያል። የእነሱ ድሮ መጋቢት ላይ ነበር፣ አሁን ጥር ላይ ነው። የወራቱን ስያሜ በነገስታቱ ስም፣ ነው ያደረጉት፤ በእነ አውግስቶስ፣ በጁለሴ፤ አድርገው ከፋፈሉት፤ በተረፈ በቁጥር ስም ነው የነበረው። ‹‹ሴፕቴምበር›› ሲል ሰባት ነው፤ ‹‹ኦክቶበር›› ሲል ስምንት ....ነው። የወሩን መደብ 31፣ 28 አድርገው በመቁጠር አነስተኛ ወሯን እንድትቀር አደረጓት።

በጥንት በተለያዩ ሕብረተሰብ ውስጥ የ13 ወር አቆጣጠር አለ። ኢትዮጵያውያን ጥንታዊነቱን ይዘን ነው የቀጠልነው። ስለዚህ እኛ አንድ ወር 30 ቀን እና 12 ሲባዛ በ30 ቀናት 360 ሲደመር አምስት ቀን ከሩብ ብለን ይዘናል። እነሱ ግን በታትነውታል አንዱ ይሄ ነው ልዩነታችን።

እነሱ ሁልግዜ ጥር አንድ ቀን አዲሱ ዓመት ነው ይላሉ፤ እኛ ደግሞ መስከረም ላይ ነው አዲስ ዓመት የምንለው። ይሄ ደግሞ ልዩ ገጽታ ነው። ከክረምቱ በኋላ፤ ብራ የሚሆንበት፣ አበቦች የሚፈኩበት እና ግልጽ ያለ የጠራ ሰማይ የሚታይበት ስለሆነ የተለየ ያደርገዋል። ለጊርጎሪያን ካሌንደር መነሻው ጁሊያን ካሌንደር ነው።

በዓመተ ዓለም አቆጣጠር እኛ 7517 ዓመተ ዓለም ስንል በእነሱ 4400 እንደዛ አካባቢ ነው። አንግሊካል ደግሞ 4004 ዓመተ ዓለም ነው። 4004 ላይ 2024 ብንደምር ለእነሱ 6028 ዓመተ ዓለም ነው። እነሱ ሰባተኛው ሺህ ላይ ናቸው። እኛ ደግሞ 7517 ዓመተ ዓለም ላይ ነን። እኛ ደግሞ ስምንተኛው ሺህ ላይ ነን ያለነው።

**አዲስ ዘመን፡-ኢትዮጵያውያን የፀሀይን አቆጣጠር እና፣ የጨረቃንና የፀሀይን ጥምር አቆጣጠር ይዘን ነው የቀጠል ነው። ከዚህ በፊት የነበረው የቀን አቆጣጠር ስሌቱ ብቻ ነበር ወይስ ወቅቱኑ በማከለ መልኩ ነው ስሌቱ የተስተካከለው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** የወቅት ጉዳይ አደለም፤ ወቅቶች እራሳቸውን የቻሉ ናቸው። የሚገኙትም በፀሀይ ነው። በጨረቃ ካሌንደር ውስጥ ወቅት የለም። ለምሳሌ ሙስሊሞች ረመዳንን ጾመው ነው ኢድ አል ፈጥርን የሚያከብሩት፣ በ33 ዓመት ኡደት ውስጥ 12ቱም ወር ይደርሰዋል። ምክንያቱም ጨረቃዋ በጋውም ላይ፣ ፀደይ ላይም ይሄዳል መጸው ላይ ይሄዳል፣ በክረምትም እንደዛው ይሄዳል።

አሁን ፋሲካ ከመጋቢት 26 በታች አይወርድም ከሚያዚያ 30 በላይ አይወጣም፤ ወቅቱ ደግሞ ጸደይ ነው አይለቅም። የፀሀይና ጨረቃ አቆጣጠር በሕዝብ አቆጣጠር ውስጥ የለም። ወደ ሃይማኖታዊ አቆጣጠር ስንገባ በእስልምናም በክርስትና እና በአይሁድ ሃይማኖቱን ተከትለው የሚመጡ በዓላት አሉ። ስለዚህ የፀሀይና ጨረቃ አቆጣጠር የምናስበው ከቤተክርስትያን አቆጣጠር ጋር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ስሌቱ እንዴት ነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** አንደኛው ከጥንተ ፍጥረት፤ ኢትዮጵያ ክርስትናን ከመቀበሏ በፊት የንጉስ ሰለሞንን

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# የኢትዮጵያን መለያ የሆነውን ...

ከገጽ 9 የዞረ

ግኑኝነት፣ ቀዳማዊ ምኒሊክን ተከትሎ የአይሁድ እምነት አለ። እምነቱ ካለ ደግሞ የዘመን አቆጣጠሩ እና በዓል አከባበር አለ።

ስለዚህ አንደኛው የዘመን አቆጣጠር የሚነሳው ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ ነው። የፍጥረት የዘመን አቆጣጠር የምንለው ከክርስቶስ ልደት በፊት 5501 ብሎ የሚነሳው ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ካለው ዘመን ይነሳል። ሁለተኛው ከክርስቶስ ልደት ዘመን ወዲህ ያለው ብለን የምንቆጥረው ነው።

የፈረንጆቹ የቀን አቆጣጠር የሚጀምረው ጥር የመጀመሪያው ወር ብሎ ይጀምርና ታህሳስ ላይ ይጠናቀቃል። የኢትዮጵያ ደግሞ መስከረም አንድ ብሎ ይጀምርና ጳጉሜ ላይ ያልቃል። ሌላው በየአራት ዓመቱ ሰግር የምንለው ጭማሪ አንድ ቀን አለች።

ስሌቱ ከጥንተ ፍጥረት ይነሳል፣ ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ ይነሳል። እያንዳንዱ ወር 30 ቀናት አሉት። ከዛን የወሩ ስያሜ ደግሞ ከእርሻ ጋር የተያያዘ ነው። ጳጉሜ ደግሞ 360 አብቅቶ ሌላኛውን 360 ለመረከብ እንደ አረካካቢ አድርገን ማየት እንችላለን። ሌላው አቆጣጠር ደግሞ የሃይማኖታዊ በዓላትን ለመለየት የምንጠቀምበት ነው። ስሌቱ የተመሰረተው በፀይና በጨረቃ ጥምር አቆጣጠር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሌሎች ዓለማት የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ልዩነቱ ምንድነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-**መሬት በራሷ ዛቢያ ስትዞር አንድ ቀንን ታስገኛላች። በፀሀይ ዛቢያ ስትዞር 365 ቀን ከስድስት ሰዓት ነው። እስከ 16 መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ምዕራቡ ሆነ ሁላችንም በዚሁ ሁኔታ ነበር ስንቆጥር የቆነው። ንጉስ ጊርጎር በተነሱበት ዓመት ሊቃውንቱ ተሰብስበው፤ መሬት ፀሀይን ምትዞርበት 365 ቀን ከስድስት ሰዓት ነው የሚለውን መረመሩ። 365 ቀን 5 ሰዓት ከ48 ደቂቃ ከ44 ሰከንድ ነው በሚለው ተማመኑ ።

ያለአግባብ ቀን ተጨምሯል በማለት የጁሊያን ካሌንደር እንከልሰው በማለት ከለሱት። ለቤተክርስትያን አቆጣጠር መሰረት የሆነው በ325 ዓ.ም ኒቂያ ላይ የተደረገው ጉባኤ ነው። ሊቃዉንቱ ከ325 እስከ 1582 ያሉት ዓመታት ላይ ያለአግባብ ተጨምሯል ያሉት 11 ደቂቃ ሲሰበሰብ 10 ቀን ወጣው።

ያለአግባብ ነው 10 ቀን የተጨመረው፤ ምን እናድርግ አሉ ። ከዛን ጥቅምት 4 በማግስቱ ጥቅምት 5 መሆን ሲገባው 10 ቀን ጨመሩና ጥቅምት 15 ብለው መቁጠር ጀመሩ። ይህን ውሳኔ ምስራቆቹ አልተቀበሉትም፤ ምዕራቦቹ ተቀበሉት። መስከረም አንድ 2017 በጁሊያን ካሌንደር ነሐሴ 29 ነው። በጊርጎሪያን ካሌንደር መስከረም 11 ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጳጉሜ አንዳንድ ግዜ ሰባት ቀን ትሆናለች የሚባል ነገር አለና፤ መቼ ነው የምትሆነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ጳጉሜ ሰባት ቀን ሆና አታውቅም። ምንድነው ጨረቃ ምድርን የምትዞርበት 354 ብቻ አይደለም ትርፍራፊ ሰዓት አላት ልክ ፀሀይ እንዳላት ሁሉ፤ እሱን ሰብስበው በ600 ዓመት አንድ ግዜ ጳጉሜ ሰባት ትሆናለች ይላሉ። ይሄ ደግሞ ስላልተመዘገበ አይሆንም። የፋሲካ ሰንጠረዥ አለ፤ በዚህ ላይ ጳጉሜ ከጥንት ጀምሮ አምስት እና ስድስት ብቻ ነው።

ለቀን አቆጣጠሩ የራሱ የሆነ ኡደት አለ። የሰባት ቀን፣ የ30 ቀን፣ የ365 ቀን፣ የአራት ዓመት፣ የዘጠኝ ዓመት፣ 28 ዓመት፣ የ76 ዓመት ኡደት ሲሆን ትልቁ ቀመር ደግሞ 532 ዓመት ወስጥ ነው የሚመላለሰው። ስድስተኛዋ ቀን ጳጉሜ መሪያ ትባላለች የምታዘዋውር ማለት ነው። ዓመቱ በዋለበት ቀን ተመልሶ እንዳይውል የምታደርግ ናት።

በ532 የሚዘዋወረው የዘመን ኡደት ውስጥ ጳጉሜ አምስት፣ አምስት፣ አምስት፣ ስድስት ነው የሚሆነው። ሰባት የሚል ሰንጠረዥ ውስጥ የለም። ጳጉሜን ስድስት እራሷን ችላ ቀን አይደለችም። ከ365 ቀን የምትተርፈው ስድስት ሰዓት ተደምራ ነው በአራት ዓመት አንዴ ስድስት የሚሆነው።

**አዲስ ዘመን፡-ጳጉሜ ስድስት ሲሆን ገና ታህሳስ 28 ነው የሚከበረው። ይሄ ከምን የመጣ ነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-**ጳጉሜ 5 እና የጌታ ልደት አንድ አይነት ናቸው። በቤተክርስትያን ስርዓት ጳጉሜ 5 ልደት ናቸው። ስለዚህ ሁልግዜ ጳጉሜ አምስትና ልደት ተመሳሳይ ቀን ነው የሚውሉት። 2016 ጳጉሜ 5 ማክሰኞ ነው የዋለው። ታህሳስ 29፣ 2017 ማክሰኞ ነው የሚውለው። አንድ ዓመት 52 ሳምንት ከአንድ ቀን ነው።

ስለዚህ ከ52 ውስጥ የሌለችው ልዩዋ ቀን ጌታ የተወለደባት ቀን ናት። ጳጉሜ ስድስት ሲሆን በ28 የሚውለው ከጳጉሜ አምስት ጋር ለማናበብ ነው። ለሎች ቱፊቶች ቢኖርቱም ዋና ቱውፊቱ ይሄ ነው። የፈረንጆቹ ታህሳስ 25 አይለቅም ምክንያቱም የእነሱ ጭማሪዋ ቀን እንደኛ በዓመቱ መጨረሻ ስላልሆነች።

**አዲስ ዘመን፡- የዘመን አቆጣጠሩን ስንረከብ የጳጉሜ ቀናት እንደ ኢትዮጵያ በዓመት መጨረሻ ላይ ነው። ወይስ እንደፈረንጆቹ በእያንዳንዱ ወር ላይ ተደምሮ እና ተቀንሶ ነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** አንድ ወር 30 ቀን አንድ ዓመት 12 ወር የሚለው ብሂል ጥንታዊ ነው። አንድ ወር 30 ቀን ማለት ከዚሁ ከአፍሪካ የበቀለ ነው። ከጥንት ከግብጻውያን ጋር እና እኛም ጋር ከአባይ ወንዝ ጋር ተከትሎ የመጣ ነው። ለሌላው የቀን አቆጣጠርም መነሻ የሆነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጳጉሜ አምስት ወይም ስድስት ቀን ናት፤ እንዴት 13 ወር ሊባል ቻለ?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ጳጉሜ ማለት የግሪክ ቃል ነው። የፀሀይ ኡደት 365 ቀን ነው። አንድ ወር በ30 ቀን መስከረም ጀምሮ ነሐሴ ላይ ያበቃል። የጨረቃ ደግሞ ነሐሴ 24 ያበቃል። ነሀሴ 25 በጨረቃ ስሌት መስከረም ወር ነው። ለፀሀይ ግን አምስት ቀን ትርፍ አላት።

ስለዚህ 13ኛዋን ተውሳክ፤ በመጨረሻ የግሪኩ ቃል ተስማማቸው ተውሳክ አሏት።ለነገሩ ንኡስ ወር ነው የምትባለው፤ በተጨማሪም ፍራንክ ስለሌላት ተጠዋሪቷ ባልቴትም ትባላለች። ሌሎቹን ወራት እንደ ቦላሌ ሱሪ ወስደን እሷ እንደቁምጣ ማየት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- እያንዳንዱ ዓመት ከአራቱ ወንጌላውያን በአንዱ ይመሰላልና ይሄስ ከምን የመጣ ነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** የቤተክርስትያን ቱውፊት ስንመለከት ዓመተ ምህረት ከክርስቶስ ልደት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው። ስለዚህ የክርስቶስን ታሪክ የጻፉ፣ የምስራቹን የተናገሩት አራቱ ወንጌላውያን ናቸው። የማቴዎስ ወንጌል፣ የማርቆስ ወንጌል፣ የሉቃስ እና የዮሐንስ ወንጌል ብለን አራቱ ወንጌል አለ።

አንዱም እኮ የሚለየን እሱ ቱውፊት ነው። ወንጌላውያን በተመለከተ በምስራቅም፣ በምዕራብም ያሉ ክርስትያኖች የሚያከብሩባቸው ቀን አላቸው። ነገር እያንዳንዱን ዓመት በእነሱ አይሰየሙም። ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስ፣ ዘመነ ዮሐንስ ብሎ በየአራት ዓመቱ ይመላለሳል። የጳጉሜን ቀናትንም ያስተሳስራል፤ ከዮሐንስ እስከ ማርቆስ አምስት ቀን ሆኖ፣ ሉቃስ ስድስት ቀን ይሆናል። ይህን ደግሞ የአዘቦት ዓመትና የሰግር ዓመት እንላለን።

**አዲስ ዘመን፡- ዓመቱ በየትኛው ወንጌላዊ እንደሚውል ለማወቅ፤ በምን መልኩ ነው የሚሰላው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** የአዲስ ኪዳን መጽሃፍ ሲከፈት በመጀመሪያ የማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ ወንጌሎች፤ ከአንድ እስከ አራት ባለው ቅድመ ተከተል ናቸው። ዓመተ ዓለም ሲደመር ዓመተ ምህረት ሲካፈል ለአራት ተብሎ፤ ቀሪው አንድ ከሆነ ማቴዎስ፣ ሁለት ከሆነ ማርቆስ፣ ሶስት ከሆነ ሉቃስ ሲሆን ምንም ቀሪ ከሌለው ዮሐንስ ይሆናል።

ዘንድሮ አዲስ አንድ ዓመት ብቻ ሳይሆን አዲስ የአራት ዓመት እና አዲስ የ28 ዓመት ኡደት የምንጀምርበት ልዩ ዓመት ነው። ቱውፊቱ ቢታወቅ የመንግስት ተቋማት ሆነ የሃይማኖት ተቋማት በእቅድ አወጣጥ ላይ ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ። ምድረ ቀደምት እንላለን፤ ነገር ግን ለኢትዮጵያ የግዜ አቆጣጠር ምን ያህል ጥልቅ እውቀት አለን የሚለው ጥያቄ ይፈጥራል።

አሁን ክረምት ሲያልፍ ብዙዎቹ ከአደይ አበባ ጋር ስለሚያያዝ ፀደይ ይላሉ። ፀደይ ግን መጋቢት ላይ ነው። ክረምት ቀጥሎ የሚመጣው መጸው ነው። ይህም አበባ ማለት ነው። ክረምት ላይ ሆነን «ሰመር» ወይም «ሰመር ኮርስ» ይባላል። ሰመር ማለት በጋ ማለት ስለዚህ ለአውሮፓውያን እንጂ ለኢትዮጵያ አይደለም። ለእኛ ክረምት ነው እንግሊዘኛውን ቃል እንጠቀም ከተባለም «ዊንተር» ነው።



**ጳጉሜ ማለት የግሪክ ቃል ነው። የፀሀይ ኡደት 365 ቀን ነው። አንድ ወር በ30 ቀን መስከረም ጀምሮ ነሐሴ ላይ ያበቃል። የጨረቃ ደግሞ ነሐሴ 24 ያበቃል። ነሀሴ 25 በጨረቃ ስሌት መስከረም ወር ነው። ለፀሀይ ግን አምስት ቀን ትርፍ አላት።**

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ጠብቀው ያቆዩት እነማናቸው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** የዘመን አቆጣጠሩ ሀገራዊም ነው። ክርስትና ዓለም አቀፍ እንደመሆኑ ከዓለም ከአይሁድ እና ከሌሎችም የተቀበልነው ልዩ ልዩ ሀሳቦች ስላሉ እከሌ ነው ማለት አንችልም። ነገር ግን በየዘመኑ ያስተማሩ ሊቃውንት አሉ። ስለዚህ የጥንት ሕብረተሰብ ነው። ክርስቲያናዊ፣ አይሁዳዊ እና እስላማዊ ሀሳቦች ደግሞ ከተመሰረቱበት አውድ ጋር ተያይዞ ይገለጣሉ።

የዘመን አቆጣጠሩ ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረገችው ቤተክርስትያን ናት። በቤተክርስትያን ባህረ ሃሳብ እንደ አንድ ሙያ ነው የሚሰጠው። ለቤተክርስትያን የዘመን አቆጣጠር መነሻው ብርሰቱ ደረጃ ቅዱስ ያሬድ ነው። በፊት ግን ከመጀመሪያ ዘመን ጀምረው ያሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ቅርስ እየተቀበሉ እያስማሙ ቀጥለዋል።

የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በዋናነት በሃይማኖት ሊቃውንት እና በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ሊቃውንት የተቀመረ ነው። በምስራቅም፣ በምዕራብም ያሉ። አውዲዮናሲዮስ፣ ዲሜጥሮስ ወደ እኛ ስንመጣ ደግሞ እንደነ እጨጌ አበሙ የመሳሰሉት አሉ።

ስለዚህ የኢትዮጳያ ሊቃውንት እና የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር አደራጀ። ከዛን ዓለም አቀፍ ከሆነው አቆጣጠር ጋር ተዛመደ።

**አዲስ ዘመን፡- በዘመን አቆጣጠር ከኢትዮጵያ ጋር የሚመሳሰል ሀገር አለ?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ አንድ ነው። መስከረም አንድን ቲቶ አንድ ነው የሚሉት፣ ሕዳርን ሀቱር፤ ጳጉሜን አልናሲ ይላሉ። በመንግስት ካሌንደር ደረጃ ኢትዮጵያ ብቸኛ ናት። 13 ወር በማለት ግን የግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ትመሳሰላለች።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚገልጹት ሀሳብ ካለ?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ኢትዮጵያ የራሷ ፊደል፣ ቁጥር፣ የራሷ ካሌንደር ያላት ብለን እናስተዋውቃለን። ነገር ግን በአግባቡ አናውቅም ፤በትምህርት ተቋማትም በአግባቡ አይገለጽም። አራቱን ወቅቶች እንኳን በቅጡ የማንገልጽ ነን። በደራሲዮች፤ በገጣሚዎች እና በዘፋኞች ፀደይን ለመስከረም የመስጠት ነገር አለ። ፀደይ በልግ ማለት ነው እንጂ ስፕሪንግ አይደለም። ቀጣይነት ያለውን የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር መጠበቅ ይገባል። ቀን ይሞሸራል ዓመት ይቀመራል። መልካም ዘመን እንዲሆንላቹ እመኛለው!

ልዩ ዕትም

# ከፖሊሲ ማሻሻያ እስከ ኢንቨስትመንት አማራጭ

በኢትዮጵያ የፋርማስቲካል ዘርፍ ብቻ በዓመት ከ1 ጥብ 5 ቢልዮን ዶላር በላይ ገበያ መኖሩን አለ

አስናቀ ፀጋዬ

በ2016 ዓ.ም በጤናው ዘርፍ በርካታ አበይት ተግባራት ተከናውነዋል። ከፖሊሲ ማሻሻያ ጀምሮ የጤናውን ዘርፍ ሊያዘምኑ የሚችሉ በርካታ አዳዲስ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ውጤቶች ተዋውቀዋል። በተለይ እያደገ ከመጣው የሕብረተሰቡ የጤና አገልግሎት ፍላጎትና ቀደም ሲል ያሉና አሁን ላይ ያሉ የበሽታዎችን ስርጭት ከግምት ውስት በማስገባት የፀደቀው አራተኛው የኢትዮጵያ ጤና ፖሊስ ባለፈው ዓመት በጤናው ዘርፍ ከተከናወኑ ተግባራት ውስጥ በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው።

አራተኛው የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ እስካሁን የተመዘገበውን ውጤት ይበልጥ ለማጠናከር፣ ለወቅታዊና ወደፊት ለሚከሰቱ ተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጤናና ጤና ነክ ፍላጎቶች ይበልጥ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስለመሆኑ ተነግሮለታል። እያደገ የመጣውን የሕዝብ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠትና ከወቅቱ ጋር የተናበበ የጤና ስርዓት ለመፍጠር ዓላማ ባደረገ መልኩ ፖሊሲው እንደተዘጋጀም ታውቋል።

ከጤና ፖሊሲ ማሻሻያው በዘለለ ባሳለፍነው ዓመት ሌሎችም በርከት ያሉ የጤናው ዘርፍ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን፣ የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታት «ጤናችን በምርታችን» በሚል መሪ ቃል የተካሄደው የመጀመሪያው የሀገር ውስጥ የሕክምና ግብዓት ምርትና ኢኖቬሽን የሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን በማሳደግ ረገድ ተስፋ ሰጥቶ አልፏል።

በሌላ በኩል ክትባት ያልጀመሩና ጀምረው ያቋረጡ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕፃናትን ተደራሽ የሚያደርግ የክትባት ዘመቻም በዚሁ ዓመት የተከናወነ ሲሆን ዘመቻው በተለይ በግጭትና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከክትባት ውጪ የሆኑ ሕፃናትን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ይፋ ተደርጎ የተጀመረው የፅዱ ኢትዮጵያ ፕሮጀክት አካል የሆነው የፅዱ ጤና ተቋም ንቅናቄም አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎች ሲሰራ የቆየው ባሳለፍነው ዓመት ነበር።

እነዚህ ስራዎች እንዳሉ ታዲያ የክረምት ወቅትን ተከትሎ የተከሰቱ የኮሌራና ወባና ወረርሽኞች ለኢትዮጵያ ስጋት ደቅነው የነበረ ቢሆንም በተከናወኑ ጠንካራ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች ወረርሽኞቹ የከፋ ጉዳት ሳይስከትሉ ለመቆጣጠር ተችሏል። በተመሳሳይ የዝንጀሮ ፈንጣጣ (Mpox) በሽታ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ በትኩረት በመሠራቱ እስካሁን ድረስ በሽታው በኢትዮጵያ እንዳልተከሰተ ተነግሯል። የዓለም ጤና ድርጅት ይህን በሽታ የዓለም አሳሳቢ የድንገተኛ የጤና አደጋ መሆኑን ካስታወቀ ጊዜ ጀምሮ የጤና ሚኒስቴር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በርካታ ስራዎችን በትኩረት እየሠራ መሆኑም ተገልጿል።

ከነዚህ የጤናው ዘርፍ አበይት ክንውኖች ባሻገር ግን ሌሎች በጤናው ዘርፍ ላይ አንድ እርምጃ የሚጨምሩ ስራዎችም በጤና ሚኒስቴርና በሌሎች አጋር አላት ተከናውዋል። ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ጉባኤዎች ተካሂደዋል። የልምድ ተሞክሮ ጉብኝቶች ተደርገዋል። አዳዲስ የጤና ፕሮጀክቶች ይፋ ሆነዋል። የጤና ተቋማትን ለመገንባት የሚያስችሉ ድጋፎችና ስምምነቶች ተደርገዋል። አዲስ የሆስፒታሎች ግንባታ ተከናውኗል። የክረምት የጤና በጎ ፍቃድ አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተካሂዷል።

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት መጨረሻ 27ኛው የዓለም የቲቢ ቀን እና 18ኛው ዓመታዊ የቲቢ ምርምር ጉባኤ ተካሂዷል። በዚህ ጉባኤ በኢትዮጵያ የቲቢን በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሰሩ ስራዎች ውጤት ያስመዘገቡ ቢሆንም በቲቢ የተያዙ ሰዎች አሁንም ድረስ መገለል እንደሚደርስባቸውና ይህን ችግር ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተጠቁሟል። ከዚሁ ጎን ለጎን አዲስ ሀገራዊ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስትራቴጂክ እቅድ የማስተዋወቂያ መድረክ ተከናውኗል። ሀገር አቀፍ የጤና ተቋማት የጥራት ደረጃ መረጃ የማሰባሰብ ስራም በዚሁ በጀት ዓመት ተጀምሯል።

በስዊዘርላንድ ጀኔቫ በተካሄደው 77ኛው የዓለም ጤና ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ ተሳትፋ በተለያዩ የጤና ጉዳዮች ላይ መግለጫ አቅርባለች። የጤና ሚኒስቴር ዶክተር መቅደስ ዳባ ለጉባኤተኞቹ ባደረጉት ንግግር የጤና አገልግሎት የዜጎች ሰብአዊ መብት መሆኑን ኢትዮጵያ በፅኑ ታምናለች ብለዋል። ዓለም አቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ስናረጋገጥ ማንንም ወደ ጎን መተው የለብንም፤ ምንም አይነት ልዩነትና ድምበር ሳይኖር ለዜጎቻችን ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠት ይገባል ብለዋል።

በተያያዘም የጤና ሚኒስቴር ዶክተር መቅደስ ዳባ ከዓለም ጤና ድርጅት ዶክተር ቴዎድሮስ አድሃኖም ጋር ተወያይተዋል። በውይይታቸውም የዓለም ጤና ድርጅት በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት፣ የጤና ፋይናንሲንግ፣ መደበኛ የክትባት ፕሮግራምን ለማጠናከር እንዲሁም ወባና ኮሌራ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር የሚወሰዱ እርምጃዎችን እንደሚደግፍ አስታውቋል።

የ2 ሺ የጤና ማእከላት ግንባታ የአራትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ባሳለፍነው በጀት ዓመት የተፈረመ ሲሆን የአራትዮሽ ስምምነቱ በጤና ሚኒስቴር፣ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ቦንጋ ዩኒቨርስቲና የሩሲያ ፓን አፍሪካ ዴቨሎፕመንት ሴንተር መካከል ተፈርሟል። ፕሮጀክቱ በ250 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የ2 ሺ ጤና ማእከላት ግንባታ ከተሟላ የሕክምና ቁሳቁስ ጋር በቀጣይ አምስት ዓመት እንደሚካሄድ ተጠቁሟል። በተመሳሳይ ለሰባተኛው ዙር የግሎባል ፈንድ መተግበሪያ 440 ሚሊዮን ዶላር ግራንት በጤና ሚኒስቴር፣ ግሎባል ፈንድና ሲ ሲ ኤም ኢትዮጵያ በኩል ተፈርሟል።

28 ሚሊዮን ዶላር በጀት የተያዘለት ወረዳን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ ጤና ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮጀክትም ይፋ የተደረገው ባሳለፍነው ዓመት ሲሆን ፕሮጀክቱ የሚከናወነው ከጤና ሚኒስቴር፣ አምሬፍ ኸልዝ አፍሪካ እና ቢል ኤንድ ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር በአምስት ክልሎች በተመረጡ በ50 ወረዳዎች መሆኑ ተነግሯል።

በሌላ በኩል ጤና ሚኒሰቴር ባለፈው በጀት ዓመት ከኢትዮጵያ ጤና ትምህርትና ፕሮሞሽን ባለሙያዎች ማህበር እንዲሁም ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ሶስተኛውን ሃገር አቀፍ የማህበራዊ እና ባህሪ ለውጥ ጉባዔ "የማህበራዊ እና ባህሪ ለውጥ ተግባራት ለዘላቂ የጤና ልማት" በሚል መሪ ቃል ከ13 ዓለም አቀፍ አገራት ከመጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ጨምሮ 400 በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት በአዲስ አባባ አካሂዷል።

በተያያዘም ከዩ ኤስ ኤ አይ ዲ (USAID) ጋር በመተባበር ከስርዓተ-ምግብ እና ጤና ጋር የተያያዙ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ባሳለፍነው ዓመት ተግባራዊ ሊደረጉ እንደሆነ ተገልጿል። ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ አዳዲስ ከስርዓተ-ምግብ ጋር የተያያዙ ፕሮጀክቶችን ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር መተግበር እንደሚፈልግ ከጤና ሚኒስትር ዶ/ር መቅደስ ዳባ ጋር ባደረጉት ውይይት ለማወቅ ተችሏል። ድርጅቱ ለሚተገብራቸው ፕሮጀክቶች ጤና ሚኒስቴር አስፈላጊውን ትብበር እንደሚያደርግም ተጠቁሟል። ፊድ ዘ ፊዩቸር በUSAID የሚተገበር የስርዓተ-ምግብ ፕሮግራም ሲሆን፤ ሴቶች፣ ታዳጊ እና ጨቅላ ሕጻናት የተሻለ ስርዓተ-ምግብ ተጠቃሚ ያደርጋል።

ባለፈው ዓመት ከተከናወኑ አዲስ ክስተቶች ውስጥ ሌላኛው ጤና ሚኒስቴር ከኮሪያው ሪፐብሊክ ዓለም አቀፍ የጤና እንክብካቤ ፋውንዴሽን (ኮፊ) ጋር በመተባበር የሕክምና አገልግሎት መስጫ መሳርያዎች ማደሻና ማሻሻያ ማዕከል ግንባታ መጀመር የሚያስችል የመሰረት ድንጋይ ማስቀመጡ ሲሆን ግንባታው ሲጠናቀቅ በኢትዮጵያ ታድሰው ዳግም አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በርካታ የሕክምና መሣሪያዎች ለብክነት እንዳይዳረጉ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ተጠቁሟል።

ሰላሳ ሁለት ሀገራት የተሳተፉበት የአፍሪካ መደበኛ ስፔሻላይዝድ የጤና፣ ስነ-ምግብ፣ ሕዝብ እና መድሀኒት ቁጥጥር ውይይት የተካሄደውም ባሳለፍነው የ2016 በጀት ዓመት ነበር። በአፍሪካ ሕብረት የስብሰባ አዳራሽ በተካሄደው በዚህ ውይይት "ጤናን ማዳበር በአፍሪካ፡ ሁለንተናዊ የጤና፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ የሕዝብ ቁጥር፣ የመድኃኒት ቁጥጥር፣ ወንጀል መከላከል እና ትምህርት የተነሱ አንኳር ጉዳዮች ነበሩ።

ከአፍሪካ የልማት አጀንዳ ጋር በማጣጣም ከጤና፣ ከሥነ-ምግብ፣ ከሕዝብ እና ከመድኃኒት ቁጥጥር ጋር የተያያዙ በርካታ የሥራ ሰነዶች ፀድቀዋል። በኮንፈረንሱ ከ32 አባላት የተውጣጡ ሚኒስትሮች እና ልዑካን ቡድኖች የተገኙ ሲሆን ከተለያዩ የአፍሪካ ሕብረት አካላት እና አጋር ድርጅቶች ተወካዮች የተውጣጡ ኃላፊዎችና ባለሙያዎችም ተሳትፈውበታል።

የመጀመሪያው ዙር ዓለም አቀፍ የክረምት ነጻ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ቡድን ወደ ሃገር ውስጥ መግባቱም የባለፈው ዓመት አብይ ክስተት ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የክረምት በጎ አድራጎት አካል የሆነው ነጻ የጤና ምርመራና ሕክምና አገልግሎት በሃገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም የጤና ተቋማት ተከናውኗል። ይህንኑ መልካም ተግባር ለማጠናከር ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የተለያዩ ሃገር ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የክረምት ነጻ የጤና አገልግሎት ሰጥተዋል።

ጤና ሚኒስቴርና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲሁም ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የአስገዳጅ የብሔራዊ የምግብ ማበልጸግ ፕሮግራምና የ5 ዓመት ስትራቴጂ እቅድ ማስተዋወቅ መርሃ ግብርም ባለፈው ዓመት ይፋ ተደርጓል። በኢትዮጵያ ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ ሕጻናት መካከል በተመጣጠነ ምግብ እጥረት 39 በመቶው የሚሆኑት የመቀንጨር ችግር እንደሚያጋጥማቸው በወቅቱ ተገልጿል። 11 በመቶው የሚሆኑት ሕፃናት የመቀጨጭ እንዲሁም 22 በመቶው የሚሆኑት ደግሞ የክብደት መቀነስ ችግር እንደሚያጋጥማቸው የተነገረ ሲሆን የአስገዳጅ የብሔራዊ የምግብ ማበልጸግ ፕሮግራም እና ስትራቴጂ ይህን ችግር ለመቅረፍ በእጅጉ እንደሚረዳ ተጠቁሟል።

ባለፈው ዓመት በኮንጎ ብራዛቪል የተካሄደው 74ኛው የአፍሪካ አህጉር የዓለም ጤና መድረክ የአፍሪካ አባል አገራት በተለይም ወረርሽኞችንና ድንገተኛ የጤና አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የአፍሪካ ተጨባጭ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ዝግጁነትና የቅድመ መከላከል ስራዎችን እንዲሁም ፈጣን ምላሽ ለመስጠት በትብብርና በቅንጅት ለመስራት፣ የአመራር ክህሎትና የጤና ባለሙያውን አቅም ለማሳደግ፣ የጤናውን ዘርፍ የፋይናንስ አቅምና ኢንቨስትመንት ለመደገፍ ከምንግዜውም በላይ በጋራ ለመስራት ቁርጠኝነት ታይቶበታል።

አምስተኛው የአፍላ ወጣቶች እና ወጣቶች ጤና ፎረም "ተደራሽነትና ጥራት፡ ምላሽ ሰጪ ስርዓት ለሁሉም የአፍላ ወጣቶች እና ወጣቶች!" በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም የተካሄደው በዚህ ዓመት መጨረሻ ነበር፡ በፎረሙ ጤና ሚኒስቴር የአፍላ ወጣቶችንና ወጣቶችን ሁለንተናዊ ጤና ለመጠበቅ በፖሊሲ የተደገፉ አቅጣጫዎችን ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር እየሰራ እንደሆነ ገልጿል።

በፎረሙ ከጤና ሚኒስቴር በተጨማሪ ሌሎች የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሚኒስትሮችና ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች መገኘታቸው የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና የጤናው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የሚመለከት መሆኑን ማሳያ መሆኑም ተጠቁሟል። ፎረሙ ጥራት ያለው የወጣቶች እና አፍላ ወጣቶች ጤናን ታሳቢ ያደረገ ስራ ለመስራት ከባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ ለመወያየት የተዘጋጀ መሆኑንም ተነግሯል።

በበጀት ዓመቱ መቋጫ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በቻይና ቤጂንግ እየተካሄደ በሚገኘው የኢትዮ-ቻይና ከፍተኛ የቢዝነስ ፎረም ላይ ተሳትፏል። ከዚሁ ጎን ለጎን በፎረሙ ላይ በመገኘት በጤናው ዘርፍ ያለውን ሁኔታ አስመልክቶ የጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በማብራሪያቸውም በኢትዮጵያ በጤናው ዘርፍ ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጭ መኖሩን ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ የፋርማስቲካል ዘርፍ ብቻ በዓመት ከ1 ጥብ 5 ቢልዮን ዶላር በላይ ገበያ መኖሩን ሚኒስትሯ አንስተው መንግስት በጤናው ዘርፍ ስድስት ዋና ዋና ዘርፎችን በመለየት አስፈላጊውን መሰረተ ልማት በማሟላት እየሰራበት መሆኑን ተናግረዋል። እነዚህም ሜዲካል ቱሪዝምን ማእከል ያደረገ የቴሪሸሪ ጤና አገልግሎት፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ የዲያግኖስቲክ አገልግሎት፣ የሕክምና ግብአቶች ማምረቻ፣ የጤናው ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት፣ የቅድመ ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት፣ የጤና ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን መሆኑን አብራርተዋል።

## ልዩ ዕትም



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ስራ አስኪያጅ ሊቀ ማዕምራን የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ፤



የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ስራ አስፈጻሚ አባል - ሼክ እድሪስ አሊ ሁሴን »



በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባዔ ጠቅላይ ጽህፈት ቤት የቤተሰብ የምእመናንና የወጣቶች ሃዋርያዊ አገልግሎት ዳይሬክተር አባ አብነት አበበ፤



በኢትዮጵያ ሕይወት ብርሃን ቤተክርስቲያን የቦርድ ሰብሳቢና የኢትዮጵያ ሃይማናት ተቋማት ጉባዔ መሥራችና የቀድሞ ዋና ጸሀፊ መጋቢ ዘሪሁን ደጉ፤

# አዲሱ ዓመት የኢትዮጵያ ሰላም የሚረጋገጥበት ዘመን እንዲሆን እንመኛለን

### የኃይማኖት አባቶች

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱን ዓመት ተቀብለናል። በዘመን ቆጠራ አዲስ የሚያሰኘው ማክሰኞ ከረቡዕ ተለይቶ ሳይሆን የሰው ልጅ የሚሠራቸው ሥራዎች ናቸው። በአዲስ ዓመት ዋዜማ እና በእለቱ መካከል ያለው ልዩነት በሰው ልጅ እቅድና እንቅስቀሴ የሚወሰን ነው። የሰው ልጅ እቅድና ተግባር ደግሞ ከራስ በዘለለ ለሌሎችና ለሀገር ሊጠቅም የሚገባ፤ ብሎም ሰላምን ያስቀደመ ሊሆን እንደሚገባ የሃይማኖት አባቶች ይናገራሉ።

በአዲሱ ዓመት ስለራሳችን እቅድ ስናወጣ ሀገራችንና በአካባቢችንም ሰላም እንዲሰፍን በማሰብ ሊሆን ይገባል። ዛሬ ላይ የተፈጠሩና እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች ሁላችንንም የሚነኩ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። በመሆኑም እቅዳችንም ተግባራችንም ሰላምን ያዘለ ሰላምን የተላበሰ እንዲሆን ይጠበቃል። ሰላም በመደፍረሱ በሰላም ከቦታ ወደቦታ መንቀሳቀስ የሚያዳግትበት ሁኔታ ሲፈጠር ችግሩ ሁሉንም የሚነካ ሆኗል። እንደ ሰው በማህበር እየኖርን ለብቻ ታስቦ ለብቻ ተሠርቶ የሚሳካ ነገር ባለመኖሩ ለሌሎችም ሰላም ልንጸልይ፤ ልንሠራ ስለ ሰላም ልንመክር ይገባል።

እንደ ሀገር ያለፉት ጥቂት ዓመታት ጥሩ አልነበሩም። በእነዚህ ዓመታት የነበሩ ስህተቶቻችንን ልንደግም አይገባም። ለዚህም አዲሱን ዓመት ስንቀበለው በአዲስ መንፈስ በየሃሳባችን ፤በየእቅዳችን ሁሉ ሰላምን አካተን ሊሆን ይገባል። እልህ በመጋባት ብዙ ጥፋት ደርሶ አይተናል፡፡ ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ህይወት እስከማለፍ የደረሱ አጋጣሚዎችን በቅርብ ጊዜያት በሀገራችን አስተናግደናል። አሁን መገንዘብ ያለብን ሁሉንም ነገር ከይቅርታ ውጪ ከሆነ አደጋው ለሁላችንም ነው፡፡ እልህ መጋባት አብሮ ያጠፋናል፡፡የራሳችን ሀሳብ አመለካካት እንዲከበር እንዲደመጥ እንደምንፈልግ ሁሉ የሌሎችንም ሀሳብ ማክበር ማድመጥ ይጠበቅብናል። ከእልህ አመለካከትና ተግባር መላቀቅ አለብን።

በተጨማሪ ለአዲሱ አመት እንደ ግለሰብም ሌሎች እንዲቀየሩ ሌሎች እንዲለወጡ ከማሰብ በፊት ራሳችንን ለመለወጥ ልንዘጋጅ ይገባል። ሌሎች ሰዎች እኛ የምንፈልገውን ላይሆኑ ይችላሉ በቁጥጥራችን ስር ባለመሆናቸውም ልንኮንናቸው አንችልም። እኛ ራሳችንን ግን ማረም ማስተካከል እንችላለን። ከሁሉም በፊት ራሳችንን ለማደስ ራሳችንን ለመቀየር ልንጥር ይገባል። አሁን አሁን በስፋት እንደምናስተውለው ብዙ ነገራችን ትላንት ለይ የቆመ ነው። በርግጥ ትናንትን የተሰሩ ነገሮች ጎጂም ጠቃሚም ቢሆኑ የራሳችን ታሪክ አካል ናቸው። እነዚህም በታሪክነታቸው ቢወጡና ብናውቃቸው ይጠቅሙናል እንጂ አይጎዱንም ። ነገር ግን ትናንትን እያነሳን ለጭቅጭቅ እና ለግጭት መነሻ መነሻ ልናገደርጋቸው አይገባም።

በሌላ በኩል ካለምክንያት ጎራ ለይቶ እርስ በእርስ ከመተቻቸት መውጣትም ይኖርብናል። ዛሬ ዛሬ የተለመደ አካሄድ አለ፡፡ ለምሳሌ ሰላሳና አርባ ኪሎ ሜትር መንገድ ተሠርቶ አንድ ቦታ ጎርፍ ሲገጥም ብዙዎቻችን ይቺን አጉልተን ሁሉም መንገድ እንደጠፋ አድርገን ስንገልጽ ይስተዋላል። ይሄ ለምን ሆነ ብለን ራሳችንን ልንፈትሽ ይገባል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከመናናቅ ወጥተን መከባበር መዋደድ አለብን ፡፡የሌላውን ባህል ፤ሃይማኖት፤ እምነት መናቅ ማንቋሸሽ የለብንም። ሰው ራሱን ሲሆን በተለያየ ማንነት ከመፈረጅ ወጥተን ሁላችንም ራሳችንን የምንመረምርበት የምንፈትሽበትና ለሰላምና ለፍቅር ቅድሚያ የምንሰጥበት ሊሆን ይገባል።

በአዲሱ አመት የሁሉም ሰው እቅድና ተግባር ከሀገር ሰላም ጋር የተገናኘ መሆን አለበት። ካለንበት ሁኔታ አንጻር ሰላም ለማስጠበቅ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ይጠበቃል። በእስልምና አስተምህሮ ሰው ከቤተሰቡ ጋር ሰላም ከሆነ፤ አካሉ ጤነኛ ከሆነ ዓለምን በእጁ አውሏል ይባላል። ለእያንዳንዳችን የአንድ ቀን ሰላም ብዙ ጥቅም አላት፡፡ ትናንት አልፏል፤ ነገ አይታወቅም የዛሬ የአንዷ ቀን ሰላም ግን በለሰው ልጅ ዘንድ ትልቅ ቦታ አላት። ስለዚህም ከሃይማኖት መሪዎች ጀምሮ በተለያዩ ሃላፊነት ቦታ ለይ ያሉ ግለሰቦችም እለት በእለት ስለ ሰላም ሊያስተምሩ የተግባር መምህርም ሊሆኑ ይገባል።

የውስጥ ሰላማችንን ከማስጠበቅ ባለፈ እንደ ሀገር ያንዣበበብንን ሰላም ለመመከትም መዘጋጀት አለብን። የውስጣችን ሰላም አስጠብቀን አንድነትና ህብረታችንን ማጠናከር ከቻልን ከውጪ የሚመጡ ጠላቶች የትም ሊደርሱ ምንምም ሊያመጡ አይችሉም። ካለፈው ታሪካችን እንደምናየው ብዙ ጊዜ የውጪ ጠላት ለእኛ አስቸጋሪ ሆኖብን አያውቅም። በጦርነትና በእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ያለፉ ሀገራት የደረሰባቸውን ችግር አይተናል። እንኳን ከጎረቤት ሀገራት ቀርቶ ከሶሪያ በግጭት የተፈናቀሉ ሀገራችን ድረስ መጥተው ሲንከራተቱና ለችግር ሲዳረጉ እየተመለከትን ነው። እኛ ከዚህ ብዙ ልንማር ይገባል። እኛ መሸሻ ሀገር ያለን ሕዝቦች አይደለንም ፡፡ ስለዚህ የሀገራችንን ሰላም ቅድሚያ ሰጥተን ልንጠብቅ ይገባል። በመሆኑም በአዲሱ አመት ማሰብም መሥራትም ያለብን ከችግር ወጥተን ወደ ልማት አንዴት እንደምንሸጋገር ነው።

ሌላው የአዲሱ ዓመት ዓላማችን ልናደርገው የሚገባው የመረዳዳት ጉዳይ ነው። በርካታ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ለከፋ ችግር ተዳርገዋል። ለእነዚህ መድረስ ከሁላችን ይጠበቃል። ይህ አብሮነታችንን መተሳሰባችንን የሚያጠናክር ነው። በቅርቡ በጎፋ ለደረሰው ችግር መጅሊሱ ርዳታ ይዞ በሄደበት ወቅት ይህንን በግልጽ አይተናል። የችግሩ ሰለባዎች ከተደረገላቸው የቁሳቁስ ድጋፍ ይልቅ የእናንተ መምጣት ወገን ደጋፊ አለሁ ባይ እንዳለን እንዲሰማን አድርጎናል ብለውናል። አሁን ባለው ሁኔታ የኑሮ ውድነት ሕዝቡን እያማረረው እንደሆነ ይታወቃል።’ በዚህ ረገድም ከንግዱ ማህበረሰብ ብዙ ይጠበቃል። ነጋዴ ለሕዝብ የቆመ ሊሆን ይገባል። መንግሥትም በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉና ለችግር የተዳረጉትን በየጊዜው ሊያስባቸው ይገባል።

ሌላው የዓመቱ ጉዳያችን መንግሥት የጀመራቸው የባህር በር ጉዳይና የዓባይ ግድብ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳይ ግብጽና ሌሎች ሀገራትም ጣታቸውን መቀሰር ከጀመሩ ውለው አድረዋል። እኛም ኢትዮጵያ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ገንብታ አጠናቃ ለልማት አስኪታውልና ለህልውና መሠረት የሆነውን የባህር በር ተጠቃሚነት አስኪታደርግ ድረስ ከመንግሥት ጎን ልንቆም ይገባል።

እያንዳንዱ ሰው ለአመቱ የሚያዘጋጀው እቅድ ሰላምን ያካተተ መሆን አለበት። ከቤተሰብ ጀምሮ እርስ በእርስ ያለንን ግንኙነት ልንፈትሽ ይገባል። ከቤተሰብ የሚጀምር ሰላም ለአካባቢም ለሀገርም የሚተርፍ ይሆናል። የአመቱ እቅዳችን የእኛን ዓላማ የእኛን ሃሳብ ብቻ የተሸከመ መሆን የለበትም። እንደ ሀገር ስለሰላም ማሰብ ብቻ ሳይሆን የሰላም አርአያ መሆንም ይጠበቅብናል። ያሰብነው ያለምነው ሊሳካና ከግብ ሊደርስ የሚችለው እኛ ብቻ ሳንሆን በአካባቢያችን ያሉትና መላው ሀገራችንም ሰላም ሲሆን ነው።

ሰላም ባለመኖሩ ብዙ ነገሮች አጥተናል። ዛሬ ለይ አንጻራዊ ሰላም ቢኖርም ሰላም በምንፈልገው መጠን ባለመሆኑ ብዙ ተግዳሮቶች ገጥመውናል። ይህንን ጉዳት ለማስቀረትና ሰላምን በዘላቂነት ለማስፈን ባጠቃለይ ለሀገርና ለሕዝብ ስንል የሰላም መሣሪያ ለመሆን፤ ከእኔ ምን ይጠበቃል ብለን ልናስብም ልንሠራም ይገባል። በካቶሊክ እምነት የሰላም ጸሎት የሚባል አለ። በእሱም ጥል ባለበት ፍቅር ፤ በደል ባለበት ይቅርታ ፤ ክርክር ባለበት ስምምነት፤ ጥርጣሬ ባለበት እምነት፤ ስህተት ባለበት እውነት፤ ተስፋ መቁረጥ ባለበት መጽናናት፤ ኀዘን ባለበት ደስታ ፤ ጨለማ ባለበት ብርሃን እንድናደርግ አብቃን እንላለን። በዚህ መሠረት ለይቅርታ፤ ለፍቅር ፤ ለመስማማት የምንተጋ ልንሆን ይገባል።

የተሰጠን ሶስት መቶ ስላሳ አምስት ቀን ፈጣሪ የሚደሰትበት ፤ ሁላችን የምንባረክበት ሊሆን ይገባል። አዲስ ዓመት አዲስ ስጦታ በመሆኑ ስላለፈው ዓመት የምናመሰግንበት ራሳችንን ገምግመን የምናስተካክለውን አስተካክለን አዲስ እቅድ የምንናስቀምጥበትና የምንተገብርበትም መሆን አለበት። ይህም ሆኖ አዲስ ዓመትን አዲስ የሚያሰኘው በሰዎች ዘንድ የሚኖረው ሰላም፤ ፍቅርና ደስታ ነው። ሰው መሆን መልካም መሆን ነው። ሌሎች ሰዎችን በመውደድ፤ ይቅርታ በመስጠት አዲስ ዓመትን ለመቀበል መዘጋጀት ይጠበቃል። አዲስ ዓመት የተሰጠንም ልንጠቀምብትም የሚገባው ለራሳችን ብቻ አይደለም፡፡ እኔ ከሚለው ተሻግረን ለቤተሰባችን በአካባቢያችን ላሉና ለሀገራችንም ጥሩ የምንሆንበት ደግ ደጉን የምንሠራበት ሊሆን ይገባል።

ሌሎች ሰዎችንም ስንቀበል ከነማንነታቸው፤ ከነባህላቸው፤ ከነሃይማኖታቸው በክብር ሊሆን ይገባል። በዚህ ሂደት የሃይማኖት አባቶች ሚና ትልቁን ድርሻ ይይዛል። ሁሉም ሳይታክቱ ስለፍቅር መስበክ አለባቸው። ዛሬ በአንዳንድ ቦታዎች የምናያቸው ጸብና ግጭቶች ትናንት ተዘርተው የነበሩ ናቸው። በተመሳሳይ ዛሬ የምንሰብከው ሰላምና ፍቅር ውጤቱን ፍሬውን የምናገኘው ነገ ነው። ስለዚህ የሃይማኖት አባቶች ከማስተማር ከማሳየት ከመምከር ባለፈ በጸሎት መትጋትና የቃል ብቻ ሳይሆን የተግባርም አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ሰላም ያሳጣን ችግር፤ አለመግባባትና ግጭት የጋራ ድምር ውጤት ቢሆንም ከግለሰብ የሚጀምር ነው። አሁን ያለንበት የሰላም እጦት የተፈጠረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በእርሱ እየተጣላ የጀመረው አይደለም። ችግሩን እዚህ ያደረሱት የተወሰኑ ፖለቲከኞች ቁጭ ብለው በመነጋገር ሊፈቱት የሚችሉትን መፍታት ባለመቻላቸው የተከሰተ ነው፡፡ በመሆኑም ሰው በቤቱ ፤ በአካባቢው ካለ ሰው ጋር የሚኖረው ጤናማ ግንኙነት ድምር ውጤት ኢትዮጵያን ሰላም ያደርጋታል። ሀገር የመንግሥትና የተወሰኑ ፖለቲከኞች ብቻ አይደለችም። ይልቁንም የህልውና አደጋ ሲገጥም የጥፋቱ ሰለባ የሚሆኑ የሃይማኖት ተቋማትና ተከታዮቻቸውም ናቸው። ጦርነትና ግጭት እንደተፈጥሮ አደጋ ሁሉ ማንነትን አይቶ የሚምር አይደለም። ስለ ሰላም የሚሠሩ ሥራዎች ለሌሎች ተብሎ ሳይሆን ለራስ ነው። በጥላቻ ንግግር መለያየትን መጠፋፋትን መስበክ ሀጢያት ነው። ይህንን በማህበራዊ ሚድያ የሚያስተላልፉትን መገሰጽም የሃይማኖት አባቶች ግዴታ ነው።

ሌላው በዓመቱ የሚጠበቀው ከሃይማኖት አባቶች ወጣቶችን በመቅረጽ ረገድ የሰላም መልእክተኛ መሆን ነው። ይህን የሚያደርጉት የሃይማኖት ተልእኮ ሰላም መስበክ በመሆኑና በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተሰሚነት ተቀባይነት መጠቀም ስለሚኖርባቸው ነው። ለሰላም የሚሠራ ሥራ በጊዜ መገደብ አይኖርበትም የሁል ጊዜ ሥራችን መሆን አለበት።

ዛሬ ሰላማችን ችግር የተጋረጠበትና ህብረታችንና አንድነታችን የተፈተነበት ወቅት ነው። በአዲሱ ዓመት አብሮነታችንን የሚያጠናክር ረዥም መንገድ የሚያስጉዘን የጋራ ሀገራዊ እቅድም ሊኖረን ይገባል። ለዚህም በሚያቀራርቡን ጉዳዮች ለይ እየመከርን እስከ ዛሬ በምንታወቅበት ኢትዮጵያዊ አንድነት ለይ ማተኮር አለብን። የውስጥ ችግሮቻችንን ለመፍታት ትኩረት ሰጥተን ልንሠራ ይገባል። አለመስማማትና ግጭት ተፈጥሯዊ በመሆናቸው መቼም ሊከሰቱ የሚችሉና የሚከሰቱም ነገሮች ናቸው። ችግሩ የተፈጠረው እነዚህ ነገሮች እንዴት እናስተናግዳቸው በሚለው ለይ ክፍተት በመኖሩ ነው። ለዚህ ደግሞ ንግግር ዘመኑ የሚጠይቀው ብቸኛው መንገድ ነው። በመሆኑም በራችንን ዘግተን አሉ በሚባሉ ችግሮቻችንን ለይ ራሳችን ሌሎችን ጣልቃ ሳናስገባ ልንመክር ይገባል። ለዚህ ደግሞ የምክክር ኮሚሽኑ ትልቅ እድል ይዞልን የመጣ ነው።

የምክክር ኮሚሽኑን በተመለከተ በሁለት ምክንያቶች እድሉን ከሰጠናቸውና አብረናቸው ከሠራን ውጤታማ ልንሆን እንችላለን። አንደኛው የተጀመረው ሀገራዊ ምክክር ትክክለኛው የችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ይህንን ነገር እንዲያደርጉ የተቀመጡት ሰዎች ከእድሜም ከልምድም ከሥነ ምግባርም አንጻር ብቁና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚመጥኑ መሆናቸው ነው ። በመሆኑም መላው ኢትዮጵያዊ፤ ነፍጥ ያነሱትንም ጨምሮ ቆም ብለው በማሰብ ከመንግሥትም ከሕዝብም ጋር ለመወያየት ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል።

## ልዩ ዕትም

# የመንግስት ቁርጠኛነት የታየበት የአረንጓዴ አሻራው ስኬት

**ማህሌት አብዱል**



ኢትዮጵያ በደን ሃብቷ ከአፍሪካ ሀገራት ግንባር ቀደም እንደነበረች ይታወቃል። ይሁንና ይህ ሀብት እየጨመረ በመጣው የሕዝብ ብዛት፣ ይህን ተከትሎ በተከሰተው የእርሻና የግጦሽ መሬት እጥረትና ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ደኑን ኃላፊነት በጎደለው መልኩ በመጨፍጨፋቸው ምክንያት ያ ግዙፍ የደን ሀብት ለመናመን ተዳርጓል።

እንደሚታወቀው ሃገሪቱ በተደጋጋሚ ለድርቅ አደጋ ስትጋለጥ ቆይታለች። ለእዚህ እና ለግብርና ምርታማነት በእጅጉ እየቀነሰ ለመጣበት ሁኔታም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል የደን ሀብት መመናመኑ ይገኝበታል።

በእርግጥ ሀገሪቷን በተለያዩ ዘመናት የመሩ መንግስታት የወደመውን የደን ሃብት መልሶ ለመተካትና ያለውንም ለመንከባከብ ጥረቶችን ማድረጋቸው አይካድም። ሆኖም ሙከራው ያዝ ለቀቅ ያለበትና የታሰበውን ውጤት ማሳካት ያልቻለ ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። የደን ሃብት ከሰብዓዊ ሕይወት ጋር ያለውን ቁርኝት ሁሉም ባይዘነጉትም የሰጡት ትኩረት የጉዳቱን መጠን ታሳቢ ያላደረገና አነስተኛ ስለመሆኑ ሌሎች መረጃዎችም ይጠቁማሉ።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት የማዕከላት ማስተባበሪያ ዳይሬክተርና የአፈር ሳይንስና የአግሮኖሚ ከፍተኛ ተመራማሪ እንዲሁም የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አስተባባሪ ዶክተር ገረመው ታዬ እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያ የደን ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ የመጣው ያለፉት መንግስታት መሪዎች የአረንጓዴ ልማት ስራን በባለቤትና በቁርጠኝነት መስራት ባለመቻላቸውና ሕዝቡንም በሚገባው ልክ ባለማስተባበራቸው ነው።

በዚህ ምክንያት የሃገሪቱ የደን ሃብት ከመጨመር ይልቅ ለመመናመን ተዳርጓል፤ የእርሻ ቦታ መስፋፋትንና ሕገ-ወጥ ስፍራዎችን ተከትሎ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ መጥቷል። ከዚህም ባሻገር ‹‹በተለያዩ መልኩ የተከላ መርሃግብር ቢካሄድም የተተከሉትን የመንከባከብ ባህሉ ባለመኖሩ ሽፋኑን ከፍ ማድረግ አልተቻለም›› የሚሉት ዶክተር ገረመው፤ በተለይ በቀድሞ መንግስታት ለጉዳዩ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ እንደነበር ያነሳሉ። እንደሃገርም ተግባራዊ የሆነው ፖሊሲም ማዳበሪያንና ምርጥ ዘርን በስፋት በመጠቀም መሬትን ምርታማ ማድረግ፤ በጥቅሉ የእርሻ መሬትን የማስፋፋት አካሄድ መሆኑ ለችግሩ መባባስ በምክንያትነት የሚጠቀስ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ይኸው የእርሻ ማስፋፋት ፖሊሲ ደግሞ ከደን ልማት ተቃራኒ በሆነ መንገድ ይፈፀም እንደነበር አስታውሰው፣ የደን ስፍራ የነበሩ መሬቶች እየተመነጠሩና እየተቃጠሉ ወደ እርሻ ቦታ በመቀየራቸው የደን መናመኑ ሂደት ተጠናክሮ የቀጠለበትን ሁኔታ እንደነበር ይገልጻሉ።

ይሁንና ባለፉት ስድስት ዓመታት ይህ ሁኔታ መቀየሩን አስታውቀዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን መምጣት ተከትሎ እንደ መንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር መከናወን ከጀመረ ወዲህ ከፍተኛ የሚባል ለውጥ መምጣቱን ያስረዳሉ።

‹‹በተለይ ከለውጡ መንግስት ወዲህ ማለትም በ2011 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርኃ-ግብር ሲጀመር በመጀመሪያው ዓመት አራት ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፤ ይህም ቁጥር በየዓመቱ እየጨመረ መጥቶ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን 23 ነጥብ 6 በመቶ ደርሷል›› ሲሉ ያብራራሉ።

የዚህ ጠቀሜታው በብዙ መልኩ እንደሚታይም ጠቅሰው፤ በአጭር ዓመታት ውስጥ እዚህ ደረጃ መድረሱ እሰየው የሚያሰኝና በዚሁ መጠንና ጥንካሬ ማስቀጠል ከተቻለ የሃገሪቱን የደን ሽፋን ሙሉ ለሙሉ መመለስ እንደሚቻል ያላቸውን እምነት አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሐምሌ 2011 ዓ.ም ያስጀመሩት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በአራት ዓመት ውስጥ 20 ቢሊዮን ችግኝ መትከልን ዓላማ አድርጎ የተጀመረ ሲሆን፣ በዚህም በመጀመሪያው ዓመት ብቻ 4 ነጥብ 7 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል እቅዱን ሙሉ በሙሉ ማሳካቱ አይዘነጋም። ይኸው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነትና መሪነትና በጠንካራ ክትትል እየተፈጸመ ይገኛል። የሚተከሉ ችግኞች ብዛትም በየዓመቱ አስገራሚ በሚባል ደረጃ እየጨመረ መጥቷል። ዘንድሮም በአንድ ጀንበር ብቻ ስድስት ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ ከ615 ሚሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። ይህ እንደ ሃገር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ የሚባል ከመሆኑም ባሻገር የሃገሪቱን የደን ሽፋን በከፍተኛ መጠን ያሳድጋል ተብሎ ይታመናል።

ዶክተር ገረመው እንደሚሉት፤ ችግኝ መትከል የደን ሽፋንን ከማሳደግ ባሻገር አፈርን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህም ሲባል በአፈር ውስጥ እየቀነሰ የመጣውን የካርቦን ክምችት ለማሳደግ፤ በአፈር ውስጥ ያለውን ብዝሃ-ሕይወት፣ ውሃና ጠቃሚ ንጥረ ነገር እንዲጨምር ለማድረግ ያስችላል። ይህ ሲሆንም የአፈር ለምነት የሚጎለብት በመሆኑ ምርታማነት በዚያው ልክ ከፍ ይላል።

‹‹በተለይ ተራራማ አካባቢዎች ላይ ዛፍ መትከል ዓመቱን ሙሉ በዘላቂነት የሚፈሱ ወንዞች እንዲኖሩ ያደርጋል›› የሚሉት ተመራማሪው፤ ይህም ሲባል ዛፎች በስሮቻቸው የሚፈሰውን ውሃ በመያዝ አፈር ውስጥ ሰርጎ እንዲገባ በማድረግ የጎርፍ መጠንና የአፈር መሸርሸርን ይቀንሳል፤ በተጓዳኝ የአፈር ጤናን ይጠብቃል ሲሉ ያስረዳሉ። ‹‹ይህ የችግኝ ተከላ በተጠና መልኩ ከቀጠለ የአፋርን ጤናና ምርታማነት ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ላይ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል›› ሲሉ ያስገነዝባሉ።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የዘንድሮውን የአንድ ጀምበር የአረንጓዴ አሻራ መጠናቀቅ አስመልከተው ባስተላለፉት መልዕክትም ‹‹የዛሬ ጀምበር ወጥታ እስከምትጠልቅ 600 ሚሊዮን ችግችን ልንከተል ኢትዮጵያውያን ሁሉ አቅደን ነበር፤ ያሰብነውን ሳናሳካ ጀምበር የሚጠልቅብን አይደለንምና በአንድ ጀምበር 615 ነጥብ 7 ሚሊዮን ችግኞችን መትከል ችለናል›› ሲሉ በመንግስት በኩል የተሰጠውን ልዩ ትኩረት መግለፃቸው ይታወሳል።

አያይዘውም ከችግኙ ጎን ለጎን ሕፃናት ተስፋቸውን መትከላቸውን፤ ወጣቶች ፅናታቸውን ማሳየታቸውን አረጋውያን ውርስ ያኖሩበት ድንቅ ክንውን መሆኑን ተናግረዋል። በጥቅሉ ኢትዮጵያውያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከቤታቸው ወጥተው የማይደበዝዝ አሻራ ማሳረፋቸውን፤ በማበራቸውና በመፅናታቸውም በዓለም ያልታየ አዲስ ስኬት ማስመዝገብ መቻላቸውን ነው ያመለከቱት።

ዶክተር ገረመው በበኩላቸው ‹‹ዘንድሮ በተለየ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶት በመሰራቱ ከታቀደውም በላይ ማሳካት ተችሏል፤ ለስኬቱ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ የመንግስት ቁርጠኝነት ነው›› ሲሉ ይገልፃሉ። በተለይም መንግስት ስሩ ብሎ የመተው ሳይሆን ከላይ ሆኖ ስራውን የራሱ አድርጎ መስራቱና ድጋፍ መስጠቱ እንደሆነም ያስረዳሉ። ከላይ መንግስት ድጋፍ ሲሰጥ ደግሞ በየደረጃው ያሉት የመንግስት አመራሮች ለስራው በዚያው ልክ ትኩረት መስጠት በመቻላቸው እንደሆነ ይገልፃሉ። ከዚህ ባሻገርም ሕዝቡ በሂደት የዛፍ ችግኝ መትከልን ጥቅም እየተረዳ በመምጣቱና ተሳታፊ በመሆኑ እንደሆነ ይናገራሉ።

‹‹አሁን ላይ ሕዝቡ ደን ማልማት ሃገርን ማፅናት እንደሆነ፤ አፈር መጠበቅ፤ ውሃ ማጎልበት እንደሆነ፤ ለትውልድ ምቹ ሃገርን የማስተላለፍ ሁኔታን መፍጠር እንደሆነ ተገንዝቧል›› ሲሉ ዶክተር ገረመው ያብራራሉ። አክለውም ‹‹ ከዚህ ቀደም አብዛኛው ሰው ችግኝ በገንዘቡ ገዝቶ ሊተከል ቀርቶ በነፃ ተሰጥቶት እንኳን ለመትከል ፍቃደኛ አልነበረም›› ሲሉ አስታውቀው፣ አሁን ግን በገንዘቡ ችግኝ ገዝቶ ይተክላል፤ በየቦታው የተደራጁ ወጣቶች ችግኝ እያፈሉ መሸጥን ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው አድርገውታል›› በማለትም ይናገራሉ።

በተመሳሳይ የእሳቸውን ተቋም ጨምሮ በአብዛኞቹ የምርምር ተቋማት ችግኝ አባዝቶ የመትከል ባህል እንዳልነበረ ይጠቅሳሉ። ‹‹በእኛ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቱ ከዚህ ቀደም ችግኝን በየማዕከሉ አባዝቶ የመትከል ሁኔታ አልነበረም፤ አሁን ማዕከላቱ አባዝተው ለራሳቸውም ይተክላሉ፤ በአካባቢያቸው ላሉ ተቋማትና ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ያከፋፍላሉ›› ይላሉ። ዘንድሮም ከአንድ ጀምበር መርሃ ግብሩ ቀደም ብሎ በየማዕከሉ በተለይ ለምግብ ዋስትና፤ ለመኖና መሰል ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ችግኞች በማባዛትና ለሕብረተሰቡና በተቋሙ አቅራቢያ ላሉ ተቋማት በማከፋፈል የበኩሉን ድርሻ መወጣቱን አስታውቀዋል።

ለዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ግን የመንግስት ቁርጠኝነት ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ስለመሆኑ መስመር አለበት የሚሉት ዶክተር ገረመው፣ ‹‹መንግስት በተለይ ዘንድሮ የችግኝ ተከላን ዋነኛ የልማት ምሶሶ ወይም ቁልፍ ስራ ብሎ መስራቱን ተናግረዋል። ይህም ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ሆና እንድትቀጥል ያየዘው አቅጣጫ ውጤታማ ስለመሆኑ ማሳያ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ‹‹ በአረንጓዴ አሻራው በጥቅሉ ችግኞችን ተከልን ማለት አፈር ጠበቅን ማለት ነው፤ አፈሩን የማይጠብቅ ሕዝብና መንግስት ደግሞ ለራሱ ለመጥፋት የተዘጋጀ ነው። ምክንያቱም ለመጪው ትውልድ የሚያበላው የሚያስረክበው የለውም›› በማለትም ያስገነዝባሉ።

እንደ ዶክተር ገረመው ማብራሪያ፤ ችግኝ መትከል ብቻውን ግብ አይደለም፤ ችግኝ ተተክሎ ካልፀደቀ፤ እንክብካቤ ካልተደረገለት ለሃገር ኪሳራ ነው። በመሆኑም መትከሉ ላይ የታየው ቁርጠኝነትና ተሳትፎ በማፅደቁና መንከባከቡ ላይም ሊደገም ይገባል። በተለይም ከተከላ በኋላ ውሃ ከስሩ እንዳይተኛና እንዳያበሰብሰው መጠንቀቅም ያስፈልጋል። ዛሬ ላይ በነቂስ ወጥቶ ዛፍ የተከለው ሰው ዓመቱን ሙሉ በተከለበት አካባቢ እየተመላለሰ ክረምቱም ውሃ እንዳይተኛበት፤ አረም እንዳይበላው፤ በበጋው ደግሞ ድርቅ እንዳይገለው መከታተልና መደገፍ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም በተተከለባቸው አካባቢዎች የሚሞቱ ችግኞች ሊኖሩ ስለሚችሉ በአዳዲስ የመተካት ስራ መስራትም ይገባል።

አሁን ያለውን ቁርጠኝነት ማስቀጠል ከታቻለም የተሻሻለ የግብርና አሰራር ማስፈን፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የውሃ ሃብትንና የብዝሃ ሕይወት ጥበቃን በማረጋገጥ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ያመጣል የሚል እምነት እንዳላቸው ተመራማሪው ተናግረዋል። ከሁሉም በላይ የተጀመረው መርሃ ግብር የጎረቤት ሀገራትን ትኩረት በመሳብ ለጋራ ተጠቃሚነት በጋራ እንዲሰሩ ከማነሳሳት ባለፈ በቀጠናው በግጦሽ መሬት፣ በውሃና በደን ሃብት እጥረት የሚፈጠረውን ግጭት በማስወገድ ስደትንና ከመኖሪያ ቀዬ መፈናቀልን ለማስቀረት ያስችላል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት 40 በመቶውን ይሸፍን ነበር። ይህ የደን ሀብት በተለያዩ ምክንያቶች እየተመናመነ መጥቶ ሶስት በመቶ ደርሶም ነበር። መንግስታት ይህን አደጋ ለመቀልበስ ባደረጉት የችግኝ ተከላ የደን ሽፋኑ 17 በመቶ ደርሶ እንደነበርም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ባለፉት አምስት ዓመታት ደግሞ የለውጡ መንግስት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በካናወነው ተግባር 32 ነጥብ አምስት ቢሊየን ማድረስ ተችሏል። በየዓመቱ የሚተከሉ ችግኞች ብዛት እየጨመረ ይገኛል። በአንድ ጀንበር የሚተከሉ ችግኞች ብዛትም እንዲሁ እየጨመረ መጥቷል።

የደን ሽፋኑንም ከ23 በመቶ በላይ ማድረስ መቻሉን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአረንጓዴ አሻራ የተተከሉ ችግኞች ብዛትም በ2016 ዓ.ም በተከናወነ ሰፊ ተግባር 40 ቢሊየን ማድረስ ተችሏል። ይህን አሀዝ 50 ቢሊየን ለማድረስም ታቅዷል።

## ልዩ ዕትም

# ለማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ ስኬታማነት

ወንድይራድ ሰይፈሚካኤል

የለውጡ መንግሥት ለሀገሪቱ መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ለመፈለግ ያስችላሉ ያላቸውን ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። በዚህም ኢኮኖሚው ወደ ተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲሸጋገር አዲስ ተስፋ የሰጡ የፖሊሲና የሕግጋት ማሻሻያዎች ተደርገዋል። ሕጋዊ ማዕቀፎቹን መሰረት በማድረግም ተግባራዊ እርምጃዎች ተወስደዋል።

መፍትሄዎቹን በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ አሰራር ለመተግበርም ከ2013 እስከ 2022 ዓ.ም የሚተገበረው የ10 ዓመት ብሔራዊ የልማት እቅድ ተዘጋጅቶ እየተተገበረ እንደሚገኝ ይታወቃል። ዕቅዱ የሀገሪቱን ርዕይ፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲን፣ ሀገራዊና የሴክተር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የባለፉትን አስር ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸም፣ ሀገሪቱ የተስማማችባቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ጉዳዮችን እና ዓለም አቀፍና ከባቢያዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን እንደ ዋና መነሻ በመውሰድ የተዘጋጀ ነው። የልማት ዕቅዱ ዓላማ የታለመውን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ሀገራዊ የረጅም ጊዜ የልማት ርዕይ ለማሳካት ጉልህ ሚና መጫወት ነው።

በ2011 የበጀት ዓመት ወደ ትግበራ የገባው የመጀመሪያው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ ብዙ የፖሊሲ ሀሳቦችን በውስጡ ያካተተ እና መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ዓላማዎችንና ግቦችን ያሳካ ነበር። ቀሪ ሥራዎች ቢኖሩም፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባትን ለማረም፣ የዕዳ ጫናን ለማቃለል፣ የሀገር ውስጥ የማምረት ዐቅምን ለማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮችን ለማስፋፋት፣ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እና መዋቅራዊ ማነቆዎችን ለማረም በተደረገው ጥረት ውጤቶች መገኘታቸውን መንግሥት ገልጿል። በቅርቡ የጸደቀው ሁለተኛው ምዕራፍ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀሪ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ግብዓት እንደሚሆን ታምኖበታል።

በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ በቅርቡ ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ትግበራ መግባቷ ይታወሳል። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ በአራት ምሦሦዎች ላይ የተገነባ ነው። እነዚህም ምሦሦዎች የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን እና ዘላቂነትን የሚደግፍ ዘመናዊ እና ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማእቀፍ መመሥረት፤ ፈጠራን የሚያበረታታ ምቹ የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ከባቢ እና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነት ዐቅምን ማጠናከር እና ጥራት ያለው አገልግሎትን በብቃት ለማቅረብ የመንግሥትን ዐቅም ማሳደግ ናቸው።

በመንግሥት ይፋ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ማብራሪያ እንደሚያሳየው፣ የፕሮግራሙ ዋና ዋና ቁልፍ ዓላማዎችና ግቦች የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከል እና የረጅም ጊዜ የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግሮችን መፍታት፤ የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን በማዘመን የዋጋ ንረትን መቀነስ፤ የዕዳ ተጋላጭነትን በመፍታት እና የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግ ሀገራዊ የልማት ፍላጎቶቻችንን በሀገር ውስጥ ዐቅም ለማሳካት ምቹ መደላድል መፍጠር፤ የፋይናንስ ዘርፉን አካታችነት፣ ተወዳዳሪነትና ጤናማነት ማጠናከር እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም እና የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ ጠንካራ፣ አካታች እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባት ናቸው።

ማሻሻያው ለጠንካራ፣ በግሉ ዘርፍ ለሚመራ፣ ሁሉን አቀፍ ለሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ መሠረት እንዲሆን ታቅዷል። ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ወቅት ከፍተኛ እና የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ባለ ነጠላ አሀዝ የዋጋ ግሽበት ይኖራል ተብሎ ግብ ተጥሏል።

**ሀገሪቱ ከፖሊሲ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ጋር ተያይዘው የሚመጡት አዳዲስ የልማት ፋይናንስ፣ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በአግባቡ እንድትጠቀም ማድረግ ይገባል። ለግሉ ዘርፍ የሚፈጠሩ መጠነ ሰፊ ዕድሎች እንዳይባክኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።**

ከዚህ በተጨማሪም የማሻሻያው ትግበራ የውጭ ምንዛሪ መዛባትን በማስተካከል፣ የፋይናንስ ዘርፉን ይበልጥ በማጠናከር፣ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፣ የታክስ ገቢን በማሳደግ፣ የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነት በማሻሻል፣ የባንክ ዘርፍን ተወዳዳሪነትና ጤናማነት በማጎልበት እና የንግድና ኢንቨስትመንት ከባቢን በማሻሻል በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የኢኮኖሚ ሥርዓት የመገንባትን ሀገራዊ ግብ ለማሳካት እንደሚያስችል ተገልጿል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋና ዋና የፖሊሲ እርምጃዎች በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት፣ የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያ፣ በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲ ሥርዓት፣ የልማት ፋይናንስ ዕድሎች እና የመንግሥት ዕዳ አስተዳደር ማሻሻያ ናቸው።

የማሻሻያ መርሃ ግብሩ በእነዚህ የፖሊሲ እርምጃዎች አማካኝነት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ታምኖበታል።

ለአብነት ያህልም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ ተደርጓል። ይህ አዲስ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ስርዓት፣ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል አንዱ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ እንደሆነ መንግሥት ገልጿል። አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ስርዓት የውጭ ምንዛሬ ግኝትንና ክምችትን ሊጨምሩ የሚችሉ ልዩ ልዩ አሰራሮችን አስተዋውቋል። ለውጭ ኢንቨስተሮች ማነቆ ሆኖ የቆየውን አሠራር ያስወግዳል። በዚህም የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል ይህ ማሻሻያ የገንዘብ ፖሊሲ ማእቀፉን በማዘመን ዝቅተኛ እና የተረጋጋ የዋጋ ንረት እንዲኖር ያስችላል። የመንግሥት ፋይናንስ ጫናዎችን እንዲቀንሱ ያደርጋል። የመንግሥት ገቢን ማሳደግ፤ የመንግሥት ወጪንና የድጎማ ሥርዓትን ውጤታማ ማድረግ፣ በጡረታ ፈንድ ሥርዓቶች ላይ መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን መተግበር፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማና ተወዳዳሪ ማድረግ እና የመንግሥት ብድር አስተዳደር ውጤታማና ዘላቂ እንዲሆን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያ እንዲኖር ያስችላል። እነዚህ እርምጃዎች የበጀት አስተዳደር ውጤታማነትን እና የመንግሥት ዕዳ ተጋላጭነትን በማሻሻል የልማት ፋይናንስ አማራጮች እንዲበራከቱ ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪም የፖሊሲ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ኢትዮጵያ አዳዲስ የልማት ፋይናንስ አቅርቦት በተለይም ከዓለም ባንክ፣ ከሌሎች የልማት ፋይናንስ አቅራቢ ባንኮች እና ከሁለትዮሽ አበዳሪ ድርጅቶች እንድታገኝ መንገድ ይከፍታል።

በዓለም የገንዘብ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚ ትንታኔ መሠረት በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ አማካኝነት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በስምንት በመቶ ያህል ያድጋል፤ የዋጋ ንረት ወደ 10 በመቶ የተጠጋ ይሆናል፤ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11 በመቶ ይደርሳል፣ የመንግሥት ዕዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ወደ 35 በመቶ ዝቅ ይላል፤ የወጪና የገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ያድጋል፤ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ከፍ ይላል፤ ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ (የ3.3 ወራት የገቢ ሸቀጦችን ወጪ ለመሸፈን የሚበቃ) ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድም ማሻሻያውን በተመለከተ «በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም የግሉ ዘርፍ በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማራ በር የሚከፍት ነው። የምንዛሬ ገበያው እንዲስተካከል እያደረገ እንዲሁም ብዙ ሕገ ወጥ ስራዎችን ወደ ሕጋዊነት እያመጣ ነው። በዶላርና በብር መካከል ያለውን ያልተገባ ዝምድና ለማረቅ የሚያግዝ ነው። ኤክስፖርት በማድረግ፣ ገቢን በማስገባትና በማስፋት፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንት በመሳብ፣ ከውጭ የሚላክ ገንዘብ (ሬሚታንስ) በሕጋዊ መንገድ እንዲመጣ በማድረግ ኢኮኖሚያችንን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያነቃቃ ይጠበቃል። በግሉ ዘርፍ ከፍተኛ መነቃቃት እየታየ ነው» በማለት ተናግረው ነበር።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ትልቅ እርምጃ ነው። «ይህ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ትርጉም ባለው መልኩ ወደተሻለ ደረጃ እንደሚያሻግረው የታመነበት እርምጃ ውጤታማ እንዲሆን መከናወን ያለባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?» የሚለው ጥያቄ ቁልፍ ጉዳይ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙን በብቃት እና በውጤታማነት ለመተግበር መንግሥት ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን ገልጿል። እነዚህ አቅጣጫዎች በላቀ አፈፃፀም እንዲተገበሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይገባል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ ውጤታማ እንዲሆን ከእያንዳንዱ ዜጋ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የግልና የመንግሥት ተቋማት ብርቱ ኃላፊነት አለባቸው። ይህ ዓይነቱ መርሃ ግብር በሙያና በሀገር ፍቅር የተቃኘ ከፍተኛ የማስፈፀም አቅም ይጠይቃል። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ጠንካራ የመፈፀም ብቃት ያላቸው ተቋማትን ይፈልጋል። እነዚህ ተቋማት ከሙስና የፀዱና በብቁ ሰው ኃይል የተደራጁ ሆነው እንዲሰሩ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል።

ከዚህ በተጨማሪም የኅብረተሰቡንና የባለሙያዎችን ሃሳብ ማዳመጥ እንዲሁም ማሻሻያው ስኬታማ እንዳይሆን ችግር በሚፈጥሩ ተቋማትና ግለሰቦች (ለምሳሌ ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ነጋዴዎችና ከነጋዴዎች ጋር የሚመሳጠሩ አስፈፃሚዎች) ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ሂደት ተከትሎ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊከሠት የሚችለውን የመልካም አስተዳደር ብልሹነት እና ሕገ ወጥነት ለመከላከል፣ መንግሥት የነቃ ቁጥጥር በማድረግ ርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል።

መገናኛ ብዙኃን ከቁልፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ተቋማት ጋር በመተባበር ስለማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው መረጃና ማብራሪያዎችን የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። ቁልፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ተቋማትም ለዚህ ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ ማሻሻያው ምን ዓይነት ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ማሳወቅ፣ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮና ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ ማሻሻያውን ለመተግበር ቀደም ሲል ዝግጅቶች ሲደረጉ እንደቆዩ ማስገንዘብ፣ ኅብረተሰቡ ማሻሻያው ውጤታማ እንዲሆን ኃላፊነቱን እንዲወጣ (ለአሉባልታዎች ጆሮ እንዳይሰጥ፣ ሕገ ወጥ ግለሰቦችንና ተቋማትን እንዲያጋልጥ…) ግንዛቤ መፍጠር ይኖርባቸዋል።

የሀገር ውስጥ ተቋማትን ማጠናከር እና ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ ማሻሻያ አተገባበሩ ላይ ማሳተፍ አስፈላጊ ተግባር ነው። ሀገሪቱ ከፖሊሲ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ጋር ተያይዘው የሚመጡት አዳዲስ የልማት ፋይናንስ፣ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በአግባቡ እንድትጠቀም ማድረግ ይገባል። ለግሉ ዘርፍ የሚፈጠሩ መጠነ ሰፊ ዕድሎች እንዳይባክኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ዋና ዋና የፖሊሲ ርምጃዎች ከአጠቃላይ ሀገራዊ የረጅምና የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች ጋር ተጣጥመው እንዲከወኑ እንዲሁም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ እና የዜጎችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲተገበሩ መንግሥት ጥብቅ የክትትልና የድጋፍ ማዕቀፎችን መዘርጋት ይኖርበታል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በማውጣት፣ በመተግበር እንዲሁም ተጽዕኗቸውን በመከታተልና በመገምገም ረገድ ወሳኝ ሚና ላላቸው ቁልፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ተቋማት (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የፕላንና ልማት ሚኒስቴር) ድጋፍ በማድረግ ተቋማዊ ዐቅምን ማጠናከርም አስፈላጊ ነው።

ከሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ጋር ግልጽነት ያለው ግንኙነት መፍጠር እና ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን (ለምሳሌ ለማኅበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እና ለዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ የመንግሥት ሠራተኞች ድጎማ ማድረግ፣ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን መደጎም…) ያስፈልጋል። መንግሥት በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ላይ ቀጣይነት ያለው ግምገማ ማድረግ አለበት። ለዚህም በወቅታዊ መረጃ ላይ በመመሥረት በፕሮግራሙ ላይ ወቅታዊ፣ አስፈላጊ እና ተገማች የፖሊሲ ማስተካከያዎችን ሊያደርግ ይገባል።

ሰላምን ማስፈን ለማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ስኬት ግንባር ቀደም ሚና እንዳለው ከማንም የተሰወረ አይደለም። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው አንፃራዊ ስኬት እንኳ ሊያስመዘግብ የሚችለው በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ አግኝተው ሕዝብና መንግሥት ዋና ትኩረታቸውን ወደ ኢኮኖሚ ሲያዞሩ እንደሆነ ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም።

ልዩ ዕትም

# ኢትዮጵያና የዘመን አቆጣጠሯ

**ክብረአብ በላቸው**

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በዓለም የስልጣኔ መድረክ የራሳቸውን አሻራ ማኖር ችለዋል። ከአክሱም እስከ ላሊበላ ያሉ ጥንታዊ ቅርሶች የኢትዮጵያውያንን ባለብዙ እውቀትና ማስተዋል የሚያሳዩ ሕያው እውነቶች ናቸው። አለት ፈልፍለው ቤት መሥራት፣ ድንጋይ ቀርፆ ሀውልት ማቆም ከዘመናት በፊት ኢትዮጵያውያን የተካኑት ጥበብ ነው።

ከዚህ ባሻገር ኢትዮጵያን ከሌሎች የዓለማችን ሀገራት ለየት የሚያደርጋት የራሷ የዘመን አቆጣጠር መከተሏ ነው። ለዚህ ጥበብ መነሻ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ተቋማት አሉ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አበርክቶ የላቀ ነው። ይህ የዘመን አቆጣጠር ስርዓትም ለዘመናት በጽሁፍ ተከትቦ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ ዛሬ ላይ ደርሷል።

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር አንድ ዓመት በውስጡ አስራ ሶስት ወራትን ሲይዝ በአራት ወቅቶች የተከፋፈለ ነው። እነዚህም ወቅቶች አራቱ ክፍላተ ዘመናት በመባል ሲታወቁ ዘመነ መፀው፣ ዘመነ ሐጋይ፣ ዘመነ ጸደይ፣ ዘመነ ክረምት ይባላሉ።

የዘመን አቆጣጠር ዓመታትን፣ ወራትን፣ ሳምንታትን፣ ዕለታትን፣ ደቂቃን እና ድቁቅ ሰዓታትን በየሥፍራቸው (በየመጠናቸው) የሚገልጽ፤ የሚተነትን፤ የሚለካ የቤተ ክርስቲያን የቁጥር ትምህርት ነው። እነዚህ ኹሉ ተመርምረው፣ ተመዝነው፣ ተቆጥረው ሲያበቁ ምድብና ቀመር ተሰጥቷቸው የሚገኙበትን ውሳኔና ድንጋጌ የሚያሳውቅ የዘመን አቆጣጠር – ‹ሐሳበ ዘመን› ይባላል።

ዓመታት፣ ወራት፣ ሳምንታት፣ ዕለታትና ሰዓታት የሚለኩት (የሚሠፈሩት፣ የሚቆጠሩት) በሰባቱ መሥፈሪያና በሰባቱ አዕዋዳት ነው። ሰባቱ መሥፈርታት የሚባሉትም፡- ሳድሲት፣ ኃምሲት፣ ራብዒት፣ ሣልሲት፣ ካልዒት፣ ኬክሮስ እና ዕለት ሲኾኑ ሰባቱ አዕዋዳት ደግሞ፡- ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኅ፣ ዐውደ ዓመት፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ አበቅቴ፣ ዐውደ ማኅተም እና ዐውደ ቀመር ናቸው።

የኢትዮጵያ እምነታዊ ባህል የሚወረሰው በሦስት ዐይነት ጠባይ ነው። አንዱ ሕገ ልቡና ይባላል። ከመጽሐፍ በፊት የነበረ ነው። ከአበው ቃል በቃል የተወረሰ ነው። ሁለተኛው በሕገ ኦሪት ከኦሪት የተቀዳ ነው። ሦስተኛው በሕገ ወንጌል ከወንጌል የተማርነው ነው። በዚህ ዐይነት ከወረስናቸው በዓላት ማለት በሦስቱም ጠባያት ከወረስናቸው በዓላት የየራሳቸው መልክ ያላቸው አሉ። የዘመን አቆጣጠር ስርአቱም እነዚህን ሁሉ የሚያካታት ሆኖ እናገኘዋለን።

የግብጽ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በሐሳበ ፀሓይ መሠረት (solar) የተቀመረና የዓመቱ እና የወራቶቹ እርዝማኔ እኩል ሲሆን በሁለቱ መሃል ያለው ልዩነት የወራትና ቀናት የቋንቋ ስያሜ እና የዓመቱ አቆጣጠር በስተቀር በዘመን መለወጫ ቀን፥ በወራትና ቀናት አቆጣጠር ተመሳሳይ ናቸው።

ለምሳሌም፡- የዓመቱ የመጀመሪያ ቀን በኢትዮጵያ መስከረም አንድ ሲሆን በግብጽም ይህንኑ ዕለት ቶውት አንድ (Tout 1) በማለት የዓመቱ የመጀመሪያ ቀናቸው ነው። በአጠቃላይ በሁለቱም የዘመን አቆጣጠር በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት 12 ባለ 30 እና 1 ባለ 5 ቀናት በድምሩ 365 ቀናት ሲኖሩ፤ አራተኛው ዓመት (በተውሳክ) 12 ባለ 30 ቀናትና 1 ባለ 6 ቀናት በድምሩ 366 ቀናት ያሏቸው ስለሆነ ምንም እንኳን በአውሮጳ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚገኙ ክርስቲያኖች ጋር ቢለያይም በሁለቱ አገሮች የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ በዓላትን በአንድ ቀን ያከብራሉ።

የግብጽ፥ የኤርትራ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አንድ ሲሆን፤ የቀኖችና ወሮች ስያሜና የዘመን ቁጥር በተመለከተ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ አንድ ሲሆን የሁሉም አቆጣጠር ከጌታ ልደት ጀምሮ አንድ ብሎ በመጀመር ዘመኑንም ዓመተ ምሕረት ይሉት የነበረውን ግብጻውያኑ በሮም ቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ በመሆኑ በ284 ዓ.ም.) ጀምረው የሮም ንጉሥ ስም ዓመተ ዲዮቅልጥያኖስ (Anno Diocletian) ብለው እንዲቀይሩ በመገደዳቸው ዘመኑ በስሙ ሲጠራ ነበር።

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከተለየች በኋላ መንግስት የግሪጎርያውያንን የዘመን አቆጣጠር ሲከተል የኤርትራ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ከኢትዮጵያ ሲኖዶስ ከተለየች በኋላ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠርን መጠቀሙን የቀጠለች ቢሆንም ስያሜውን ግን የግእዝ አቆጣጠር ብላ ሰይማዋለች።

| ሚያዝያ ፳፻፪ (2002) ዓ.ም. | | | | | | April – May 2010 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰንበት Sunday | ሰኑይ Monday | ሠሉስ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሐሙስ Thursday | ዓርቢ Friday | ቀዳም Saturday |
| | | | | | ፩ 9<br>1 | ፪ 10<br>2 |
| ፫ 11<br>3 | ፬ 12<br>4 | ፭ 13<br>5 | ፮ 14<br>6 | ፯ 15<br>7 | ፰ 16<br>8 | ፱ 17<br>9 |
| ፲ 18<br>10 | ፲፩ 19<br>11 | ፲፪ 20<br>12 | ፲፫ 21<br>13 | ፲፬ 22<br>14 | ፲፭ 23<br>15 | ፲፮ 24<br>16 |
| ፲፯ 25<br>17 | ፲፰ 26<br>18 | ፲፱ 27<br>19 | ፳ 28<br>20 | ፳፩ 29<br>21 | ፳፪ 30<br>22 | ፳፫ 1<br>23<br>ቅዱስ ጊዮርጊስ |
| ፳፬ 2<br>24 | ፳፭ 3<br>25 | ፳፮ 4<br>26 | ፳፯ 5<br>27 | ፳፰ 6<br>28 | ፳፱ 7<br>29 | ፴ 8<br>30 |

የጁሊያን፥ የባይዛንታይን (Byzantine calendar) እና የግሪጎሪያን አቆጠጠር ዓመት በቀናት ርዝማኔ ማለትም በመደበኞቹ ሦስት ዓመታት 365 ቀናት አራተኛው ዓመት (በተውሳክ) 366 ቀናት ያሉት በመሆኑ ከእኛና ከግብፅ ጋር እኩል ሲሆን፤ አንድ ዓመት 7 ባለ 31 ቀናት፥ 4 ባለ 30 ቀናትና 1 ባለ 28 ቀናት፥ በተውሳክ ባለ 29 ቀናት 12 ወራት አሉት።

የባይዛንታይን ዘመን አቆጣጠር (Byzantine calendar) የጁሊያን ዘመን አቆጣጠርን መሠረት ያደረገ ሲሆን ልዩነቱ የጁሊያን ኦገስት 31 የዓመቱ መጨረሻ ሲሆን በማግስቱ ሴፕቴምበር 1 የዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ነው።

በሌላም በኩል የጁሊያን ከ525 ጀምሮ የጌታ ዓመት (AD) ሲሉ ባይዛንታይን ደግሞ ዓመተ ዓለም Anno Mundi (in the year of the world) በማለት ይጠሩታል ለምሳሌ በጁሊያን ኦገስት 31 ቀን 2023 AD በባይዛንታይን ኦገስት 31ቀን 7531 AM ሲሆን በማግስቱ በጁሊያን ሴፕቴምበር 1 ቀን 2024 AD ሲባል በባይዛንታይን ደግሞ ሴፕቴምበር 1 ቀን 7532 AM (በኢትዮጵያ (2015) ዓ.ም ወይም (7513) ዓመተ ዓለም) በማለት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በመጠቀም ላይ ሲሆኑ ከመንግሥታዊ አገልግሎት ከራሺያ (የቀድሞው ሶቪየት ሕብረት) በ1917፥ ከግሪክ በ1926 ቦታውን ለግሪጎርያን አቆጣጠር ለቋል።

የሮማውያን ዘመን አቆጣጠር በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ እየተስተካከለ መጥቶ ከጌታ ልደት 46 ዓመት በፊት (708 AUC) በጁሊየስ ቄሳር ከሐሳበ ጨረቃ ወደ ሐሳበ ፀሐይ ሲቀየር እንደገና ከጌታ ልደት 8 ዓመት በፊት (746 AUC) አንዷት ቀንን ከሁለተኛው ወራቸው ቀንሰው ስምንተኛው ወራቸው ላይ ጨምረው ዘመኑንም AUC (Anno Urbis Conditae) በማለት የሮም ከተማን ከመሠረቱበት ከጌታ ልደት በፊት 753 ጀምሮ ከጌታ ልደት በኋላ እስከ 284 ዓ.ም.) ድረስ በዚህ ስያሜ ሲጠሩበት ኖረዋል። ከ284 ዓ.ም.) ጀምረው ዘመኑን AUC ማለትን በመተው ዓመቱንም እንደ አዲስ ከታች ጀምረው አንድ ብለው በመቁጠርና ዘመኑንም ዓመተ ዲዮቅልጥያኖስ (Anno Diocletian) በማለት ተኩት።

በመቀጠልም በ525 በአሁኑ ጊዜ አውሮፓውያን የሚጠቀሙበትን AD (Anno Domini) የጌታ ዓመት የተሰኘውን አቆጣጠር ዲዮኒሲዩስ ኤክሲጉስ የተሰኘ የሮማን ቤተ ክርስቲያን መነኩሴ (Dionysius Exiguus) ሐሳብ አመጣ፤ በዚሁም ሐሳብ መሠረት ከ247 Anno Diocletian ቀጥሎ ያለውን ዘመን 532 (Anno Domini) የጌታ ዓመት በማለት በነበረው ዘመን ላይ ሰባት ዓመት በመጨመራቸው በእኛና በአውሮፓውያን ዘመን መሃከል በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ላይ የሰባት ዓመት ልዩነት አመጣ።

የታሪክ ተመራማሪዎችም የሮማው መነኩሴ ዲዮኒሲዩስ (Dionysius Exiguus) ካሰላው ሰባት ዓመት በፊት (7BC) ኢየሱስ መወለዱንና ሄሮድስ የሞተውና አርኬላዎስ የነገሠው ከዚሁ ስሌት አራት ዓመት በፊት (4BC) መሆኑን አረጋግጠዋል። (World History- A chronological Dictionary of Dates; by Rodney Castleden London 1994 PARRAGON Book Service Ltd) ከዚህና ከመሳሰሉት የታሪክና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች አንጻር የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሰባት ዓመት ከድርጊት የቀደመ መሆኑን ራሳቸው አውሮፓውያን አምነዋል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ባሕረ ሐሳብ በሚለው መጽሀፋቸው እንዳስቀመጡት የዘመን አቆጣጠር መለያየትን መነሻ እንዲህ በማለት ያብራራሉ፤ «ክብ የሆነ ነገር ሲከብ ከየትኛውም ቦታ መጀመር ይቻላል፤ የዘመን አቆጣጠር /ዓውደ ዓመትም/ ይኸው ነው። ዋናው ነገር አንድ ታላቅ ታሪካዊ ድርጊት ፈልጎ እርሱን መነሻ ማድረግ ነው፤ የዘመን አቆጣጠሮቹም ልዩነት መንስኤው ይኸው ነው» ይላሉ።

ጌታቸው ኃይሌ፣ ገጽ.65/ ለምሳሌነትም ሮማውያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ጊዜ መነሻ ማድረጋቸውን/ በኋላም ታላቁ እስከንድር የነገሠበት ዘመን የዘመን ቆጠራ መነሻ ሆነው እንደ ነበር ይጠቅሳሉ። የነበዩ መሐመድና ተከታዮች ከመካ ወደ መዲና ያደረጉትን ስደት መነሻ የሚያደርገው ኢስላማዊ የዘመን አቆጣጠርም ሌላው ተጠቃሽ ነው።

የአይሁድን አቆጣጠር ትተን ከላይ ያየናቸው ሁለቱ የዘመን አቆጣጠሮች /የምዕራባውያኑ የጁልየስ ጎርጎርዮሳዊ አቆጣጠርና የኢትዮጵያና የግብጽ አቆጣጠር/ ሁለቱም ዘመንን የሚቆጥሩት የኢየሱስ ከክርስቶስ ልደት መነሻ አድርገው ነው። ይሁን እንጂ እኛ ዛሬ 2002 ዓ.ም ነው ስንል እነርሱ ደግሞ 2009 ዓ.ም ነው ይላሉ።

በዓለም ላይ የራሳቸው ፊደልና የዘመን አቆጣጠር ካሏቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት። የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር በሚገባ ማስተዋወቅ እንደሚገባ ብዙዎች ይናገራሉ፤ የዘመን ቀመሩን የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በማካተት ትውልዱ ከልጅነት ጀምሮ እየተማሩት እንዲያድጉ ሊደረግ እንደሚገባ ይታመናል።

የዘመን አቆጣጠሩን ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅና እንዲገለገሉበት ማድረግ የሚቻለው ኢትዮጵያ የራሷን ባህል፣ ትውፊት፣ ሥርዓት እና ማንነት መጠበቅ ስትችል ነው። አንዲት ሀገር ከራሷ የሚተርፈውን ማንኛውም ነገር ለሌሎች ሀገራት ማሳወቅ የምትችለው ከፍ ብላ መታየት ስትጀምር በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በመተጋገዝ የዘመን ቀመሩን ማሳወቅ ተገቢ ነው።

የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ባለመካተቱ ትውልዱ ከልጅነት ጀምሮ እየተማረ እንዳያድግ፣ ምሁራን ለሌሎች ሀገራት እንዳያሳውቁ እና ኢትዮጵያውያን የሌላ ሀገር ዘመን አቆጣጠር እንዲከተሉ ምክንያት ሆኗል ሲሉ ብዙዎች ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ቀመር ከጁሊያንም ሆነ ከጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር በስሌትና በቀመር የተለየ ስለመሆኑ ይገለጻል። የኢትዮጵያ ዘመን መቆጠር የጀመረው ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን፤ መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ እና ጥንተ ፍጥረት መነሻ ያደረገም ነው።

የጁሊያን ብሎም የጎርጎሮሳውያን የዘመን ቀመሮች መነሻቸው ዕምነትን ሳይሆን ታሪክን ታሳቢ ያደረገ ነው። የኢትዮጵያውያን ከሌሎች በተለየ አዲስ ዓመታቸውን በወርሃ መስከረም የሚጀምር ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የግሪጎሪያን የዘመን ቀመር ከሚጠቀሙ ሀገራት ጋር ከመስከረም እስከ ጥር ወራት በሰባት፤ እንዲሁም ከየካቲት እስከ ነሐሴ በስምንት ዓመት እንደሚለያይ ያብራራሉ ይለያየል።

ኢትዮጵያ የ13 ወር ባለቤት መሆኗ ልዩ ያደርጋታል። ከመስከረም እስከ ነሐሴ ያሉ ወራቶች በ30 ቀናት የተከፈሉና ኢትዮጵያዊ ስምና ስያሜ ያላቸው ናቸው። ጳጉሜን ወር ግን በየዓመቱ አምስት ቀናትን ስትይዝ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ስድስት ቀን እና በየ700 ዓመቱ ሰባት ቀን እንደምትሆን አስረድተው፤ የዘመን አቆጣጠሩን ጠብቆ ለማስቀጠል፣ ትውልዱን ለማሳወቅ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን እና ሌሎች ሀገራት እንዲገለገሉበት ለማድረግ በሙያው የሚያገለግሉ በርካታ መምህራንን ማፍራት ተገቢ መሆኑን ይገልጻሉ።

እኛም አዲሱን ዓመት መነሻ በማድረግ በዚህ ለሀገርና ሕዝባቸው የላቀ አበርክቶ ማኖር የቻሉ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት በሚመሰገኑበት የባለውለታዎቻችን አምድ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር መነሻ በማውሳት ይህ ጥበብ እስከዛሬ ተጠብቆ እንዲኖር ያደረጉ አካላትን አመሰገንን. ሰላም!

ጽሁፉን ለማዘጋጀት በመረጃ ምንጭነት የተለያየ ማህበራዊ ድረ ገጾችን ተጠቅመናል።

ልዩ ዕትም

# ጳጉሜን እና ኢትዮጵያዊነት

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)



ጳጉሜን ወደ ላቀ እውነት፣ ወደ በለጠ ማንነት መንደርደሪያችን ናት። ወደ ትንሳኤ፣ ወደ ከፍታ፣ ወደ አዲስ ዓመት፣ ወደ አዲስ ተስፋ፣ ወደ አዲስ ብስራት መሸጋገሪያ ናት። አሮጌውን አስተሳሰብና አሮጌውን ዓመት ትተን ወደ ከበረ ሰዋዊ እውነት የምንሳብበት ሃይላችንም ናት።

ጊዜ በተፈጥሮ አስገዳጅ ምህዋር ላይ እየተሽከረከረ ይሄዳል..ይመጣል። የሰው ልጅም በዚህ የጊዜ እሽክርክሪት ውስጥ መሪ ተዋናይ ሆኖ ከዘመን ወደዘመን ይመላለሳል። ከመስከረም እስከ ነሀሴ። እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ከዚህ ብዙሃነ እውነታ ተለይተን በራሳችን የዘመን አቆጣጠር ሡልጥነን በአስራ ሶስት ወር ጸጋ ያማርን ነን። ከሌላው የሰው ልጅ በተለየ መልኩ የምንረግጠው፣ የምንነካው፣ የምንደርስበት ሌላ የዘመን እውነት አለን..ጳጉሜ የሚባል።

ጳጉሜን ሲነሳ አብሮ የሚነሳ አንድ ታላቅ ስም ፤ ኢትዮጵያዊነት ነው። በዓለም ፊት በዚህ ስም የሚጠራ ሌላ ሀገረ መንግሥት የለም። በዚህ አንድ አይነት በሆነ ዓለም ውስጥ ለየት ብለን እንድንቆምና እንድንታይ ካደረጉን ሀገራዊ ትውፊቶቻችን መካከል ጳጉሜን ያቀፈ ባህረ ሃሳባችን ይጠቀሳል። የዘመን አቆጣጠር ስሌታችን ከታላላቅና ካስደናቂ የክብር ስሞቻችን መሃል አንዱን ሆኖ ከትውልድ ትውልድ የተመመ ነው። በባህረ ሃሳብ ቀመር መሠረት ጳጉሜ ኢትዮጵያዊነትን የተፈጠረበት የድንቅ እውነት ታዛ ነው። በዚህ ድንቅ እውነት ከዓለም ሁሉ ሌላ ነን። በዚህ ድንቅ እውነት ከዓለም ሁሉ ፊተኞች ነን። በዚህ ድንቅ እውነት ከሰው ልጅ ሁሉ ባለታሪክ ነን።

ይህ ድንቅ እውነት ዓይኖች ሁሉ ኢትዮጵያን እንዲያዩ፣ ጆሮዎች ሁሉ ኢትዮጵያን እንዲያደምጡ ለዘመናት ያስገደደ ታሪካዊ እሴት ነው። እኔና እናተ የዚህ እውነት፣ የዚህ ፍጹምና ነፍስና ስጋ ነን። በዚህ የጥበብ ፈር ላይ ከእኛ በቀር ማንም አልተራመደም። በዘመን ስሌት ውስጥ ዓለም ይሄን ያክል ታሪካዊ ክስተት የላትም። እኛም ብንሆን ጳጉሜ እንደሰጠን፣ ከጳጉሜ እንዳገኘነው አይነት የወራት ገጸ በረከት የለንም።

አብዛኞቹ በረከቶቻችን ከጳጉሜ ማህጸን ውስጥ የሚመዘዙ ናቸው። ነሀሴን ተሻግረው በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ የሚጀምሩ ናቸው። ዓለም እንኳን ሲጠየቅ ‹ኢትዮጵያ እንዴት ሆና ነው አስራ ሶስት የወራት ጸጋዎች ያሏት? በምን አይነት የዘመን አቆጣጠር ሕግ ነው አንድ ወር አምስትና ስድስት ቀን ብቻ ሊኖረው የሚችለው? ብሎ ነው። አዎ እውነት ነው ገና ዓለም ስለኢትዮጵያ የሚጠይቀው፣ የሚመራመረው ብዙ እውነት ይኖረዋል። ኢትዮጵያዊነት ያልተደረሰ፣ ያልተነገረ፣ ያልተደረሰበት ሩቅ ማንነት ስለሆነ።

በዘመን አቆጣጠር ሥርዓታችን ውስጥ እንደ ጳጉሜ አይነት ዘመነ አጭር ግን ደግሞ የታሪክ ሀብታም የለም። እንደ ሀገር ከከበርንባቸው እና እንድ ህዝብ ከተደነቅንባቸው ወራቶቻችን መካከል የዘመን አቆጣጠራችን ቀዳሚው ነው። ሌላ ሌላውን ትተን ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ፣ ጥንታዊው ትውልድ ምን ያክል ከዓለምና ከሥልጣኔ እንደቀደመ ጳጉሜን ማሰቡ ብቻ በቂ ነው። ዓለም ጊዜንና ዘመንን በአስራ ሁለት ወራት ሲከፍል ኢትዮጵያ አባቶቻችን በአስራ ሶስት ወራት የከፈሉበት ሚስጢር በራሱ ዓለም ያልተረዳው ምስጢር ነው።

ያለምንም ጥርጥር ጳጉሜን ውስጥ ኢትዮጵያዊነት አለ። ጳጉሜን ውስጥ ጥበብና እውቀት፣ ዘመናዊነትም ነፍስ ዘርተው አሉ። ጳጉሜን ውስጥ ድሮነት ከነወዙ ተቀምጧል። ጳጉሜን ውስጥ የጥቁር ሕዝቦች ትናንትናዊ አውድ፣ ትናንትናዊ እውቀትና ማስተዋል፣ ታሪክና ሥልጣኔ፣ ባህልና ቅርስ፣ ወግና ሥርዓት፣ ጀግንነትና አልሸነፍባይነት ሞልቶና ተትረፍርፎ አለ።

ጳጉሜን ውስጥ የአባቶቻችን ብልሀት ከዓለም ሁሉ በላይ ገኖ አለ። ለዚህም ነው ጳጉሜና ኢትዮጵያዊነት ስል የተነሳሁት። ለዚህም ነው የጳጉሜን መባቻ በሆነው የነሀሴ ወር ላይ ቆሜ አጭሯን ወር የማስቃኛችሁ። ይህ ወር ኢትዮጵያን ለዓለም ያስተዋወቀ፣ ብኩርናዋንም ቀድሞ የተናገረ ወራችን ነው። ጳጉሜና ኢትዮጵያዊነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ ዘውድና ጎፈር ናቸው።

ከታሪክ አብራክ የበቀሉ የእውነትና የጥበብ ግንድ። ከአባቶች የዘመን ፍሬ ውስጥ የጸደቁ የጥቁርነት ሰምና ወርቅ። ጳጉሜና ኢትዮጵያዊነት መለኮታዊ ሃይልን የዋጁ የአበው የሊቃውንት ድጓ ልሳን ናቸው። ከተንስአ የጣሙ፣ ከታሪክ የላሙ ጸዐዳ ቀለሞች። ከእውቀትና ከማይመረመው የጥበብ ኩሬ ውስጥ ዓለም ያልተረዳው፣ የሰው ልጅ ያልደረሰበትን የወራት ማለቂያ ፈልጎ ማግኘት አጀብ ብሎ ከማለፍ በቀር ምን ሊባል ይችላል?

ዓለም አንድ አይነት ነው። እኛን የሚያስንቅ ምንም የለውም። አስራ ሁለት ወራትን ሲያከብር እኛ ግን በራሳችን እውነት ተረማምደን አስራ ሶስት ወራትን እናከብራለን። ዓለም አስራ ሁለት ወራትን እንደ አንድ ዓመት ሲቆጥር እኛ ግን በራሳችን እውቀትና ጥበብ ተመርተን አስራ ሶስት ወራትን አንድ ዓመት እንላለን። ዓለም አንድን ወር ሃያ ስምንትና ሃያ ዘጠኝ ቀን ሰላሳም አድርጎ ሲቆጥር እኛ ግን በአባቶቻችን የጥበብ እውነት ልቀንና መጥቀን ጳጉሜን አምስትና ስድስት እንላለን ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ደግሞ ሰባት ብለን እናከብራለን። ታዲያ ልዩዎች አይደለን? ከዚህ በላይ ምን ጥበብ ምን ልቀት ይመጣል? በዘመን አቆጣጠራችን ዓለም ቢቀና ምን ይገርማል? ኢትዮጵያዊነት ያልተደረሰበት ጥበብ፣ ያልተደረሰበት ሚስጢር ነው ያልኳችሁ በምክንያት ነው።

በጣም የሚገርመው ደግሞ አሁን የምነግራችሁ ነው..አብዛኛው የዓለም ሀገራት ሕይወቱን፣ ዘመኑን የሚቆጥረው በሌላ ሀገር የዘመን መቁጠሪያ ነው። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ አዲስ ዓመቱን የሚያከብረው በተወራረሰና የራሳቸው ያልሆነን የዘመን መቁጠሪያ ካላንደር በመጠቀም ነው። ዓለም ላይ በራሷ የቀን መቁጠሪያ የምትተዳደር የፕላኔታችን ብቸኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ እንደሆነች ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ?

የራሱን የዘመን መቁጠሪያ ባህረ ሃሳብ የሚጠቀም ብቸኛው ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነስ ይሄንንስ ደርሳችሁበታል? በዚህ እውነት ውስጥ መኖር ደስ አይልም ትላላችሁ? እልልልል...ክብር ለአባቶቻችን ይሁን። እንግዲህ ይቺን ነው ኢትዮጵያ የምላችሁ። ክብር ለነዛ ገናና ማንነትን ለሰጡን ሻካራ እጆች..ጠያይም ክንዶች፣ ሻንቅላ ፊቶች። ክብር ይሁን ለነዛ..ፊተኛ ላደረጉን ኋለኞች፣ ያልተደረሰበትን ኢትዮጵያዊነት ላወረሱን አስተዋይ ነፍሶች።

ከወራት ባለፈ ጳጉሜን የብዙ ነገር መጀመሪያችን ናት። የብዙ ህልሞች፣ የብዙ ተስፋዎች ማቆጥቆጫ አጸዳችን ናት። ከሰኔ ጉሩምሩምታ ሽረን፣ ከሀምሌ ጭጋግ ወጥተን፣ ከነፍራቃው ከነሀሴ እዬዬ ወደ ብሩህና ለምለሙ መስከረም የምናዘግምበት የንሰሀ ጎዳናችን ናት። የአደይ አበባ መፈጠሪያ፣ በዓመት አንድ ጊዜ የምትወጣው የመስቀል ወፍ ቀጠሮዋ ጳጉሜን ታካ ነው።

ጳጉሜን ወደ ላቀ እውነት፣ ወደ በለጠ ማንነት መንደርደሪያችን ናት። ወደ ትንሳኤ፣ ወደ ከፍታ፣ ወደ አዲስ ዓመት፣ ወደ አዲስ ተስፋ፣ ወደ አዲስ ብስራት መሸጋገሪያ ናት። አሮጌውን አስተሳሰብና አሮጌውን ዓመት ትተን ወደ ከበረ ሰዋዊ እውነት የምንሳብበት ሃይላችንም ናት። ከፊታችን ላሉት አስራ ሁለት ወራቶች ሞገስ ሆናን የምትቆም፣ ኢትዮጵያዊነት በተነሳ ቁጥር ከፊት የምትመጣ የወራት ቅንጣቢ ግን ደግሞ የታሪክ ባለጸጋችን ናት።

ዘመን የራሱ የሆነ የታሪክ ገጽ አለው። እንደ ኢትዮጵያውያን ያሉ አንዳንድ ጠቢባኖች በዚህ የዘመን ገጽ ላይ ታሪክ የሚያወሳውን ታሪክ ጽፈዋል። አንዳንዶች ደግሞ ሌሎች በጻፉት ታሪክ ማጌጥን ምርጫ አድርገው ተቀብለዋል። ዓለም በታሪክ ገጹ ላይ ከጻፈው እውነትም ይሁን ጀብድ የሚልቀው የእኛ የኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ነው። ለዚህ ደግሞ አንድ ጊዜ አለምን ማሰብ በቂ ነው።

በአንድ አይነት ታሪክ፣ በአንድ አይነት እውነት፣ በአንድ አይነት አስተሳሰብ ውስጥ ናት። ወደእኛ ስንመጣ ግን ከዓለም ልዩ የሆነ በርካታ ነገሮችን ማየት እንችላለን። የምናነበው፣ የምንጽፈው፣ የምንማረው፣ ከዘመን ዘመን የምንሻገረው አባቶቻችን በዘመን ገጽ ላይ በከተቡት እውነት ነው። የምንቀምረው፣ የምናሰላው በራሳችን ፊደልና ቁጥር ነው።

ጳጉሜን ለሁላችንም የለውጥ ሀሁ ናት። ሁሉን ትተን ወደ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ የምናቀናበት የሰላማችን መዳረሻ ናት። ወደ አዲስ ተስፋ ፣ ወደ አዲስ ተፈጥሮ የምናዘግምበት የለውጥ ጅማሬ ናት። እንደ እድሜዋ የሆነ አጭር በረከት የላትም። በመስከረም መንደርደሪያ ጳጌሜን ላይ ቆመን ተስፋ የምንሰንቅ፣ መታደስ የሚጎበኘን፣ አሻግረን ነገን የምንመለከት ብዙ ነን። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፖለቲካና የማህበራዊ ተልዕኮዎች ማስፈጸሚያ እየሆነች የመጣችበት ሁኔታም እያየለ ነው።

መንግሥት እንኳን ጳጉሜን ዝም ብሎ ማለፍ የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የጳጉሜን ወር የመልካም ምኞት መሸጋገሪያ፣ የበጎ ተስፋና፣ የበጎ ህልም ጅማሬ በማድረግ እየተጠቀመበት ይገኛል። ከጳጉሜ አንድ ጀምሮ እስከ አምስትና ስድስተኛው ቀን ድረስ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ አንድነትን እየሰበክን መጥተናል። ይቅርታን፣ መቻቻልን፣ ኢትዮጵያዊነትን እየተናገርንበት መጥተናል። ዘንድሮም በአዲስ አስተሳሰብ ጳጉሜን ጳጉሜን 1 የመሻገር ቀን፣ ጳጉሜን 2 የሪፎርም ቀን፣ ጳጉሜ 3 የሉዓላዊነት ቀን፣ ጳጉሜን 4 የህብር ቀን፣ ጳጉሜን 5 ደግሞ የነገ ቀን በመሆን ተሰይመዋል።

ጳጉሜን ከወራት ባለፈ የአዲስ ነገር መጀመሪያችን ናት። ከጥበብ፣ ከታሪክ፣ ከሥልጣኔ ባለፈ ፍቅርና አንድነትን የምንመሰክርበት፣ ጥላቻና ክፉ ነገርን የምንጸየፍበት፣ ያለፈውን ትተን የኢትዮጵያዊነት ቃል ኪዳን የምናስርበት የወራት ጌጣችን ናት። ኢትዮጵያዊነት ከዘመን፣ ከሥልጣኔ፣ ከታሪክ፣ ከሥርዓት፣ ከሕገመንግሥት፣ ከሀገር ግንባታ፣ ከመንግሥት ምስረታ ከዓለም ቀደምት ማንነት ነው።

ጳጉሜን የሁላችን መልክ ናት። ኢትዮጵያዊነትን ተቀልማ ጥቁርነትን ተነቅሳ ዓለምን አጀብ የምታሰኝ የበረከት ወራችን ናት። ብዙዎቻችን እንደምንለው የሚወደድ፣ የሚናፈቅ የሆነ ውብ ገጽ አላት። ከደስታ የዘለለ፣ ከፍሰሃ የተለቀ ጸጋን በጉያዋ ሸጉጣለች። የአስራ ሁለት ወር ማብቂያ፣ የአስራ ሁለት ወራት መጀመሪያ ስለሆነች የራሷ የሆነ የትዝታ ቀለም አላት።

የብዙ ታሪኮች መጀመሪያ፣ የብዙ ትዝታዎች ፍጻሜ ስለሆነች በመምጣቷ ውስጥ እንኖራለን በመሄዷ ውስጥም እንተክዛለን። ጳጉሜን የትዝታችን መጀመሪያና ማብቂያ ወር ጭምር ናት። ኢትዮጵያዊነትን በአጭር ቁመት በጠባብ ወርድ ይዛ በእያንዳንዳችን ነፍስና ስጋ ውስጥ የበቀለች የትዝታችን ፈርጥ ናት ።

ልዩ ዕትም

# የዓመቱ ትልቁ ውሳኔ - የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አሮጌውን ዓመት ሸኝተን ዛሬ አዲሱን 2017 ዓመት ተቀብለናል። አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የፍቅርና የብልጽግና እንዲሆንልን እየተመኘን በዚህ የአዲስ ዓመት ልዩ እትማችን ኢትዮጵያ በተሰናባቹ ዓመት አቅዳ ካሳካቻቸው መካከል አንዱ በሆነው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ ሙሉ ትግበራ ውስጥ መግባት ላይ ያተኮረውን ስራችንን ይዘን ቀርበናል።

ኢትዮጵያ ከአንድ ወር በፊት ወደ ተሟላ ትግበራ ያስገባችው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አገሪቷ በተለያዩ መስኮች የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እንድታስመዘግብ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር በመንግስት በኩል በጽኑ ታምኖበታል። ማሻሻያው የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚን ለመፍጠር፣ የዘርፎችን ምርታማነት ለማሳደግ እንዲሁም የማክሮ ኢኮኖሚ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስለመሆኑም የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችም ይናገራሉ።

አካታችና ዘላቂ ዕድገት ያለው ኢኮኖሚን ለመገንባት፣ የመንግሥት ገቢን ለማሳደግ እና በሃገር ውስጥ ምርት ቀጣይነት ያለው ዕድገት ለማስመዝገብ የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ እንደሆነ የተነገረለት ይህ ማሻሻያ፣ ተግባራዊ መሆን በጀመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባለው ግምገማ መሰረት በታቀደለት አግባብ ተግባራዊ እየሆነ ስለመገኘቱ መረጃዎች ያመላክታሉ።

የውጭ ምንዛሬ ግብይቱ ከብሔራዊ ባንክ እጅ ወጥቶ በገበያ የሚመራበት ስርዓት ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል፤ ይህም በርካታ ፋይዳዎች እያስገኘ ስለመሆኑ እየተገለጸ ነው። ወደ ትግበራው ሲገባ ስጋት እንደሚሆን የተጠበቀውን የምርቶች ዋጋ መናር መንግስት ገበያውን ለማረጋጋትና አቅርቦት ላይ ለመስራት እርምጃ እንደሚወስድ በገባው ቃል መሰረት እንደ ዘይት ያሉትን ምርቶች በስፋት ወደ ገበያው በማስገባት፣ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ገበያው እንዲረጋጋ እያደረገ ነው።

መንግሥት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በስንዴ፣ ሩዝ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ያከናወናቸው ተግባሮች የማሻሻያው አካል ስለመሆናቸው እየተገለጸ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ወደ ሙሉ ትግበራ ገብቷል።

በማሻሻያው ትግበራ በተለይም የወጪ ምርቶችን የሚያመርቱ አርሶ አደሮች እና አምራች ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑም የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎችም አስታውቀዋል። በትግበራው ኢ-መደበኛ የሆነው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወደ መደበኛ የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚገባም ይታመናል። ከዚህ ባለፈም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ከአቅም በታች እያመረቱ ያሉ ኢንዱስትሪዎች በቂ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያገኙና በዚህም ምርትና ምርታማነት እንደሚጨምርና ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ እንደሚጠበቅም ታምኖበታል።

በዋናነት የንግዱን ዘርፍ እንደሚደግፍ የተነገረለት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው፣ በተለይም የወጪ ንግድን የሚያሳልጥና የተሻለ የሚያደርግ ይሆናል። በመሆኑም በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች የሚበረታቱበትና በርካታ የውጭ ባለሃብቶች ወደ አገር ውስጥ ገብተው በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጠር ይጠበቃል። የጅምላና ችርቻሮ ንግድን ለውጭ ባለሃብቶች የሚፈቅድ ሕግ እንደመውጣቱ ለእዚህ ትግበራ ማሻሻያው ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ተመላክቷል።

መንግሥት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያን ተግባራዊ ማድረጉ ይታወሳል። በዚህ ለውጦች ማስመዝገብ የተቻለ ሲሆን፣ የዚህን ለውጥ ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ሁለተኛ ምእራፍ መተግበር ተጀምሯል፤ ለዚህ ትግበራ ደግሞ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ ወሳኝ መሆኑ ታምኖበት ማሻሻያው ሙሉ ትግበራ ተገብቷል።

ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ እንድትገባ ካደረጓት ገፊ ምክንያቶች መካከል የዕዳ ጫና፣ የዋጋ ንረት፣ ሥራ አጥነት፣ አዝጋሚ የሆነ መዋቅራዊ ሽግግር፣ ዝቅተኛ ምርታማነት እንዲሁም ዝቅተኛ የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም በዋናነት ይጠቀሳሉ።

እነዚህንና መሰል ችግሮችን ለማቃለልና ኢኮኖሚያዊ



ዝንፈትን ለማስታረቅ ወደ ሙሉ ትግበራ የገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በመንግሥት ቁርጠኝነት የተወሰደ ትልቅ ውሳኔ እንደሆነና ዘላቂ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማስመዝገብ የሚያስችል ነው ሲሉ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎችም አስታውቀዋል።

«በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተወሰዱ እርምጃዎች ኢትዮጵያ በ50 ዓመት ታሪክ ውስጥ ያልደፈረችውና ያልሞከረችው ትልቅ ውሳኔ ነው» ያሉት የምጣኔ ሃብት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በርሀተስፋ (ዶክተር)፣ በተለይም ለግሉ ዘርፍ የሚኖረው አበርክቶ ዘርፈ ብዙ መሆኑን አመልክተዋል። ዘርፉ በተለይ የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ማግኘት ባለመቻሉ የተነሳ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ሳይችል መኖሩን ተናግረዋል። የግል ባለሃብቱ እንዲፈቱለት ሲያነሳቸው የነበሩ እነዚህን መሰል በርካታ ችግሮችን መቅረፍ እንደሚያስችልም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ገበያ መር ኢኮኖሚ የሚባሉ መሰረታዊ ምሶሶዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተግባራዊ አልተደረጉም። አሁን እየተገነቡ ካሉ ምሰሶዎች መካከል አንደኛው የካፒታል ገበያ ነው። ይህ ገበያ ከ50 ዓመት በኋላ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥም ተቋቁሟል። ደርግ ከወረሳቸው ኩባንያዎች አብዛኞቹ በካፒታል ገበያ የተቋቋሙ ነበሩ።

በገበያ መር ኢኮኖሚው አንዱና ትልቁ ምሰሶ ካፒታል ገበያ ሲሆን፣ የፋይናንስ ፖሊሲው ተሻሽሎ የውጭ ምንዛሪ በገበያ ዋጋ እንዲመራ መደረጉም ሌላው ለውጥ ነው። በብሔራዊ ባንክ ሲመራ የኖረው የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ስርዓት አሁን በገበያ እንዲመራ ተደርጓል።

የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ በስፋት እንዲገቡ እና የንግዱ ስርዓት ግዙፍ ለሆኑ የውጭ ኩባንያዎችም ጭምር መፈቀዱ ለኢኮኖሚው ያለው አበርክቶ ጉልህ ነው። ግዙፍ የውጭ ኩባንያዎች አገር ውስጥ ገብተው የአገር ውስጥ ምርቶችን ኤክስፖርት እንዲያደርጉ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ሲሆን፣ እነዚህ ኩባንያዎች ከውጭ ዕቃዎችን በራሳቸው የውጭ ምንዛሬ ለማምጣት ከፍተኛ አቅምና ብዙ ተደራሽነት ያላቸው ናቸው። በዚህ ይሰማራሉ ተብለው የሚታሰቡት እያንዳንዳቸው ኩባንያዎች በ70 እና 80 አገራት ውስጥ የሚሰሩና ሰፊ ገበያ ያላቸውም ናቸው ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ተናግረዋል።

ስለዚህ እነዚህ ምሰሶዎች ማለትም የካፒታል ገበያ መቋቋም፣ የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ መግባት፣ የውጭ ምንዛሬ ፖሊሲ መቀየር እንዲሁም የውጭ ኩባንያዎች በአገር ውስጥ ንግድ ሥራ መሰማራት መቻላቸው ኢኮኖሚው እንዲያድግ በከፍተኛ መጠን እንደሚያግዘው እምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል። ሀገሪቱ የንግድ ሚዛኗን ማስተካከል የምትችልበት መንገድ እንዲፈጠር የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰው፣ መሰረተልማቶችን በራሷ አቅም መስራት የምትችልበትን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ እንዲሁም የሕዝቧ ኑሮ እንዲሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ መጠን ያለው የውሃ ሃብት፣ የሚታረስ መሬት፣ ማዕድንና ሌሎች በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች እንዲሁም በርካታ ወጣት የሰው ኃይል አላት ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ አብዛኞቹ የአውሮፓ አገራትና የምስራቅ እስያ ሀገሮች /ቻይናን ጨምሮ/ ትልቁ ችግራቸው የሰራተኛ ችግር ነው ይላሉ። ምክንያቱም አብዛኛው ሕዝባቸው በጡረታ ውስጥ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ባላት የተፈጥሮ ሃብትና የሰው ኃይል ምክንያት ሰፋ ያለ ኢንቨስትመንት ወደ አገሪቱ ሊመጣ እንደሚችልም ጠቁመዋል። በዚህም ወጣቶች በኢንቨስትመንት መሰማራት የሚችሉበት ሰፊ ዕድል ሊፈጠር እንደሚችልም አመልክተዋል።

የግሉ ዘርፍ ያነሳቸው የነበሩ ችግሮችም በዚሁ ማሻሻያ አማካኝነት እንደሚቀረፉ የጠቀሱት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በተለይም የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲመራ መደረጉ በርካታ ችግሮችን ይቀርፋል ብለዋል። «የውጭ ምንዛሪ ችግር በራሳችን ያመጣነው ችግር ነው» በማለት፣ የእስካሁኑ ችግር የፖሊሲ ችግር እንደሆነም ያስረዳሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ላለፉት 50 ዓመታት የውጭ ባንኮች በአገር ውስጥ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም። እነዚህ የውጭ ባንኮች ባለመኖራቸው በተለይም የውጭ ኢንቨስተሮች የውጭ ምንዛሪ ሊያበድሯቸው የሚችል የውጭ ባንክ ባለመኖሩ የውጭ ኢንቨስትመንት ሊስፋፋ አልቻለም። በዚህ የተነሳም አጠቃላይ የገበያ ኢኮኖሚው እንዲሰራ አልተደረገም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት ምን ያህል ቀላል ነው የሚለውን አስመልክቶ የዓለም ባንክ ያወጣውን ሪፖርት ዋቢ አርገው ሲያብራሩም በዚህ በኩል ኢትዮጵያ ጥሩ ውጤት የላትም ሲሉ አስታውቀዋል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ፈቃድ ከማውጣት ጀምሮ መሬትና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት ነገሮች ከባድ የሆኑበትን ሁኔታ በአብነት ይጠቅሳሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ለመስራት በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ሪፖርቱን ዋቢ በማድረግ ገልጸዋል። መንግሥት ይህን ችግር ለመቅረፍ ኮሚቴ በማቋቋም መስራቱንም ተናግረው፣ ጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት እንደሚገባም አመላክተዋል።

ማሻሻያን ተከትሎ በሚቀጥሉት ዓመታት የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ማግኘት የሚቻልበት ዕድል ይፈጠራል ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ በተለይም በወጪ ንግድ ዘርፉ ላይ የውጭ ኩባንያዎች በሚሳፈተፉበት ጊዜ የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ማግኘት እንደሚችሉና ምርትና ምርታማነትም እንደሚጨምር ያላቸውን ዕምነት ገልጸዋል። የአገር ውስጥ ላኪዎች የሌላቸውን ገበያ የውጭ ኩባያዎች በብዛት ሊኖራቸው እንደሚችል ተናግረዋል።

ወደ ውጭ ከሚላከው የኢትዮጵያ ምርት 78 በመቶ የሚሆነው በጥሬው የሚላክ ነው ሲሉም ጠቅሰው፣ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ እሴት ጨምሮ የመላክ ዕድል ይፈጥራል ብለዋል። ለአብነትም አንድ ኪሎ ቡና በጥሬው ሲላክ ከሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ይልቅ እሴት ተጨምሮ ሲላክ የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሬ እንደሚበልጥ ተናግረዋል። ስለዚህ የአገር ውስጥ ምርቶችን በኢንዱስትሪ ፓርኮችና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች እሴት የመጨመር ሥራው ይዳብራል። በዚህም ልዩነቶች ጠበው አገሪቷ ተጠቃሚ የምትሆንበት ዕድል ይፈጠራል የሚል እምነት አላቸው።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ከእሴት ጭመራው ባለፈ ከዲያስፖራው የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ መጠቀም እንዲቻል ባንኮች አሁንም በጥቁር ገበያ በሚሸጠው መጠን ልክ መሸጥ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ማድረግ ከተቻለ አገሪቷ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ትችላለች።

ሀገሪቱ ከዲያስፖራው ብቻ በዓመት ከ12 እስከ 15 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ትችላለች። ያን ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ችግር ሙሉ በሙሉ ይቀረፋል። ምክንያቱም ከዳያስፖራ የሚገኘው ሃብት ትልቅ አቅም ያለው ነው። ለአብነትም የሕንድና የቻይና ዳያስፖራ ወደ አገሩ የሚልከው ካፒታል በአገሩ ዕድገት ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል ሲሉም ያብራራሉ።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የግሉ ዘርፍ ችግሮች የሚፈቱበትና የበለጠ የሚበረታቱበት ማሻሻያ እንደሆነ ያነሱት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ አቅም ያላቸው የአገሪቱ ነጋዴዎች ከአንድ በመቶ የማይበልጡ እንደሆኑ ጠቅሰው፣ እነዚህ ነጋዴዎች ሰፋ ማለት እንዲችሉ ማሻሻያው ትልቅ አቅም መሆን ይችላል። በተጨማሪም ከዩኒቨርሲቲ የሚወጡ ወጣቶችም እንዲሁ በሚፈጠረው የንግድ ዘርፍ መሳተፍ የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በዚህም ኑሯቸው የሚሻሻልበትና የአገሪቷ ኢኮኖሚ የሚጎለብትበት ዕድል እንዳለ ነው ያብራሩት።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር «የኢትዮጵያን ይግዙ» በሚል መሪ ሃሳብ ባካሄደው አገር አቀፍ የንግድ ሳምንትና ኤግዚብሽን ላይ ተገኝተው ማሻሻያው ለንግዱ ማኅበረሰብ ያለውን አበርክቶ ያስረዱት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊና የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፤ ማሻሻያው በተለይም የንግዱ ማኅበረሰብን የዘመናት ጥያቄ የመለሰ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለንግዱ ማህበረሰብ እየተፈጠሩ ካሉ ምቹ ሁኔታዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው። ማሻሻያው በተለይም የንግዱን ማኅበረሰብ ጥያቄዎች የመለሰ ሲሆን፤ የንግዱን ምህዳር ለንግድ ሥራ አመቺ እያደረገም ይገኛል። ስለሆነም የንግዱ ማኅበረሰብ ይህንን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም አገሩንና ራሱን ለመለወጥ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን በመስራት ተጠቃሚ እንደሚሆን አመላክተዋል።

ማሻሻያውን ተገን በማድረግ ሕገወጥ ተግባራትን በሚፈጽሙ ላይ መንግስት እየወሰደ ያለውን እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀው፣ በተመሳሳይ አቅርቦትን የማሳደግና የገበያ ትስስሩን የማስፋቱ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለንግዱ ማኅበረሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ስለመሆኑ በስፋት ተነግሮታል። በተለያዩ መድረኮች ሲነሳ የኖረውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ የአምራቾችን የዘመናት ጥያቄ መመለስ የቻለ ስለመሆኑም መረጃዎች ያመለክታሉ።

በተለይ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ የውጭ ባለሃብቶች ሲያነሷቸው ከነበሩ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት እንደነበር ይታመናል። በአሁኑ ወቅት የውጭ ምንዛሪ በገበያው እንዲመራ በመደረጉ በተለይም አምራች ኢንደስትሪዎች ጥሬ ዕቃ ወደ አገር ውስጥ በማስመጣት ኩባንያቸውን ማስፋትና ምርታማነትን መጨመር እንደሚያስችላቸው ታምኖበታል። ማሻሻያው ወደ ሙሉ ትግበራ መግባቱን ተከትሎ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች ስራቸውን ለማስፋትና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላቸው እንደሆነ ሲያነሱ ተደምጠዋል።

ልዩ ዕትም

# የትምህርቱ ዘርፍ ዐበይት ክንውኖች

ግርማ መንግሥቴ

ያለፈው ዓመት አንድ ራሱን የቻለ፤ ወይም ራሳቸውን የቻሉ ስራዎች የተሰሩበት ዓመት ሲሆን፣ ክንውኖቹም እንደየ ተቋማቱ ይለያያሉ። "ይለያያል" ወይም "ይለያያሉ" የሚለውን በጠባብ ትርጉሙ ካልወሰድነው በስተቀር እየሰፉ ይሄዳልና ልዩነቱን ከክንውን ብዛት አኳያ እንጂ ከጥራት፣ ብቃት ወዘተ እንዳልሆነ ይታወቅ።

ከለውጡ በኋላ ባፋጣኝ ስርዓቱን ወደ ማሻሻል ተግባር የተገባበት (ወይም የገባ) ተቋም ቢኖር ከትምህርት ሚኒስቴር ቀዳሚ ነው። ስብራቱ፣ ቅጭቱ፣ ውልቃቱ ሁሉ ብሶ የነበረው እዚህ ዘርፍ ውስጥ ስለ ነበረ ይመስላል በወቅቱ ሁሉም አይንና ጆሮውን ጥሎ ሲያይ እና ሲያዳምጥ የነበረው በዚሁ በትምህርትና አካባቢው ላይ ነበርና ተቋሙ "ሪፎርም" ተግባር በፍጥነት መግባቱ ተገቢና የሚጠበቅ ተግባር እና ኃላፊነት ነው።

በዚሁ ትምህርት ሚኒስቴር "ሪፎርም" በሚለው (የለውጥ አሰራር) አማካኝነት፤ ወይም "ወደ ሪፎርም ስራዎች ገብቻለሁ" ካለበት ጊዜ ጀምሮ ጥቂት ዓመታት (በተለይ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ መደረግ የጀመረውን የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲን መሰረት ያደረገ እንቅስቃሴ ማለት ይቻላል) የተቆጠሩ ሲሆን፣ በእርግጥም ከማንም በላይ በከፍተኛ ደረጃ በሪፎርም ስራ ውስጥ ራሱን ሙሉ ለሙሉ አስገብቶ የሰራ ተቋም ይጠራ ከተባለ በሙሉ ድምፅ "ትምህርት ሚኒስቴር" የማይል ይኖራል ብሎ ማሰብ በማይቻልበት ደረጃ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። በትምህርት ላይ ደርሶ የነበረው የከፋ ቅጭት፣ ስብራትና ውልቃት ከባድ ነበርና እንዲህ በቀላሉ ይወገዳል ብሎ ማሰብ ከባድ ስለሚሆን ሪፎርሙ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑ ላይ በመስማማት ተቋሙ በ2016 ዓ.ም ያከናወናቸውን ዐበይት ተግባራት ቀጥለን እንመልከት።

ከላይ እደጠቀስነው፣ በማእከል የተሰሩትን ስራዎች መነሻ አድርገው በየክልሎችና ከተማ መስተዳድር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የተሰሩት ስራዎች እንዳሉ ሆነው፣ እንደ አገር ትምህርት ሚኒስቴር የሰራቸውን ስራዎች ብቻ ብንመለከት በርካቶች ሆነው የምናገኛቸው ሲሆን፤ በትምህርት ሴክተሩ ላይ የደረሱ ስብራቶችን ለመጠገን ሁሉንም ካነቃቃው የፈተናው ዘርፍ ርምጃዎች በመጀመር ወደ ሌሎቹ እንዝለቅ።

በፈተናና ምዘና አካባቢ በርካታ የተሰሩ ስራዎች ያሉ ሲሆን፣ ዝቅ ብለንና ራሱን አስችለን ከምናየው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተናን ሳንጨምር፣ ሀገር አቀፍ የድኅረ ምረቃ ፕሮግራሞች የመግቢያ ፈተና (NGAT)፤ የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን የመውጫ ፈተና፣ ያሉበትን ሁኔታ ማወቂያ (የአስተሳሰብ) መለኪያ የሆነው "አፕቲቲዩድ ቴስት"፤ እንዲሁም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በራሳቸው በየደረጃው የሚሰጧቸው ፈተናዎች ሁሉ በዚሁ ባሳለፍነው ዓመትም በአግባቡ ተከናውነው አልፈዋል።

ሌላውና "ግዙፍ" የተባው የዓመቱ ተግባር ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በራስ-ገዝነት የማደራጀት ጉዳይ ሲሆን፣ ዩኒቨርሲቲዎች የላቀ ውጤት እንዲያስመዘገቡ እና ልዩ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን ተቀብለው በማስተማር ብቁ ምሁራንን እንዲያፈሩ ያደርጋቸዋል፤ በማንኛውም ነገር ራሳቸውን እንዲችሉ እድል ይፈጥርላቸዋል የተባለው ጉዳይ ነው። በዚሁ መሰረት የመጀመሪያው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ወደ ስራ መግባቱ በተደጋጋሚ የተገለፀ ጉዳይ ሲሆን፤ በዚሁ መሰረትም ለራስ-ገዝነት የሚያበቁትን ተግባራት በክፍል ከፋፍሎ እየሰራ የሚገኝና የመጀመሪያውን ዙርም አጠናቅቆ ወደ ተግባር ለመግባት የሚያስችለው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አሳውቋል።

ዩኒቨርሲቲው የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እና ልዩ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን አወዳድሮ በመቀበል ከአገርም ባለፈ ለዓለም የሚተርፉ ልሂቃንን ለማፍራት ነፃነት እንደሚያስፈልግ በዚሁ፣ ሰሞኑን በሰጠው ይፋዊ መግለጫው ያስረዳ ሲሆን፤ ይህንን ለማድረግ ይህንን ለማሳካት ደግሞ ተቋማዊ ነጻነት፤ አስተዳዳራዊ ነጻነት፤ የፋይናንስ ነጻነት እና አካዳሚክ ነጻነት ማግኘትን የግድ ይል ነበር።

**በመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ከእንባ ጠባቂ ተቋም የዋንጫ ተሸላሚ የሆነው የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የሰጠው ስልጠና ይህ ብቻ አይደለም።**

በተወካዮች ምክር ቤት ስለ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ ቁጥር 1294/2015፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 537/2016 ድንጋጌ መሰረት የመጀመሪያው (ሌሎች ዘጠኝ ዩኒቨርሲቲዎችም ይከተሉታል ተብሎ ይጠበቃል) የመንግሥት ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ እንዲደራጅ የተወሰነው አአዩ፤ ራስ ገዝ መሆኑ እነዚህን፣ ከላይ የጠቀስናቸውንና ሌሎች በርካታ (መምህራንንም ሆነ ተማሪዎችን መምረጥን ጨምሮ) መብቶችን (እና ግዴታዎችን?) ሁሉ እንዳጎናፀፈው ተነግሯል። በዚሁ መሰረትም በዚህ፣ በያዝነው 2017 ዓ/ም ወደ ተግባር እንደሚገባ በተጠባባቂ ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር ሳሙኤል ክፍሌ አማካኝነት ባለፈው ሳምንት ይፋ ሆኗል።

## ወደ ሌላው አፈፃፀም እንሂድ።

ሰሞኑን "ፍትሃዊ እና ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም!" በሚል መሪ ቃል የተካሄደው፣ 33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤ የዚሁ ያከናወንነው 2016 አፈፃፀም አካል ሲሆን፤ በጉባኤው ላይ "ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች የመላው ኢትዮጵያውያን እንጂ የተቋቋሙበት መንደር አይደሉም" ያሉት የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሀኑ ነጋ ፐ/ር በትምህርት ዘርፍ ላይ ያሉ አመራሮች የትምህርት ሥራን ከፖለቲካ መለየት ያለባቸው መሆኑን፤ ከዚህ በኋላ በምንም ዓይነት ሁኔታ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በአካባቢ የሚመደብበት ምንም አይነት ሁኔታ እንደማይኖር፤ የዩኒቨርሲቲ አመራሮች ምደባ በውድድር እና በብቃት ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆን የሚሰራ መሆኑ፤ ለሁሉም ጉዳዮች መመሪያዎች የተዘጋጁ መሆናቸው መነገሩ የ2017ን አፈፃፀም ከወዲሁ አውቀን እንድንከታተል እድል ሰጪ ስለሆነ እዚህ መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል።

ባሳለፍነው 2016 "አዲሱ ስርዓተ ትምህርት አንድ ተማሪ 3 ቋንቋዎችን እንዲናገር የሚያስችል" ሆኖ መቀረፁን ያስታወቀው ትምህርት ሚኒስቴር "ከትምህርት ሚኒስቴር ዓበይት የሪፎርም ትኩረቶች አንዱ የስርዓተ ትምህርት ሪፎርም ነው።" በሚል ቁርጥ ያለ አቋም "ተማሪዎች በቅድመ አንደኛ ደረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በአንደኛ ደረጃ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ማለትም እንግሊዝኛ ከዚያም ከ3ኛ ክፍል በኋላ ሌላ የአጎራባች ክልል ቋንቋ እንደሚማሩ" የተወሰነበት ዓመት ሆኖ አልፏል። ይህም እንደ አንድ የተቋሙ ከፍተኛ የሪፎርም አካል ሆኖ ተወስዶለታል። ውጤቱን ከ2017 ጀምሮ የምንመለከተው ሆኖ የውሳኔው መሰረት 2016 ሲሆን፤ "ስርዓተ ትምህርቱ በሀገር በቀል ምሁራን ጥናት ላይ ተመስርቶ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ" የተዘጋጀ መሆኑም ታውቋል።

ባሳለፍነው ዓመት፣ በርካታ የሕዝብ ጥያቄዎች የነበሩትን፤ ነገር ግን በማን አለብኙ ስርዓት የተነቀሉትን ነጥቦች ባገናዘበ መልኩ ትምህርትና ትምህርት ነክ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን፣ ስርአተ-ትምህርቱ የግብረገብ እና የተግባር ትምህርቶችን እንዲያካትት ተደርጓል፤ በሥርዓተ ትምህርቱ ችግሮች ዙሪያ ከመምህራን፣ ከወላጆች እና ከተማሪዎች የሚነሱ ሀሳቦችንም ለማካተት አስፈላጊው ሁሉ ተደርጓል፤ ወደ ፊትም ይደረጋል። የመማሪያ መጻሕፍ ስርጭትን በተመለከተም ያሉ የበጀት ችግሮችን በመቋቋም በአማካይ ያለውን ተደራሽነት ለመጨመር (በተለይ ቴክኖሎጂ ተኮር አሰራርን ለማበጀት) የሚሰራው ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገልፆል። ይህም የ2017ን የስራ አፈፃፀም ከወዲሁ አውቀን አስፈላጊውን ክትትል እንድናደርግ ያግዘናል።

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ከሚወሰዱት ርምጃዎች አንዱ የሆነውን፣ ኩረጃን ለማስቀረት በተወሰደው "ተማሪዎችን በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት" የመፈተኑ ርምጃ በ2016ም በመቀጠል ሶስተኛ ዙሩን ይዞ የነበረ ሲሆን፣ ይህም የፈተና ስርዓት በሰላም መጠናቀቁ በወቅቱ ተገልፆል። ውጤቱስ? ባለፈው ሰኞ እለት እንደ ተገለፀው:-

"የዘንድሮውን የ12ኛ ክፍል የመልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ ከተመዘገቡ 701ሺህ 749 ተማሪዎች መካከል 684ሺህ 205 ተማሪዎች ወይም 97.5 በመቶዎቹ ፈተናውን ወስደዋል" ያሉለት፤ ከትናንት በስቲያ፣ ሰኞ ጳጉሜን 4 ቀን 2016 ዓ.ም ይፋ የተደረገውን የተፈታኞች ውጤት በተመለከተም "በጥቅሉ የዘንድሮው ውጤት ካለፉት ሁለት ፈተናዎች የተሻለ ነው"፤ "አጠቃላይ ፈተናውን ያለፉ ተማሪዎች [36,409] 5.4 በመቶ ናቸው። አዲስ አበባ 10,690 (21.4 በመቶ) ተማሪዎችን በማሳለፍ ከፍተኛውን ስፍራ ይዟል።" (ትምህርት ሚኒስቴር)

ሌላው ባለፈው ዓመት በትምህርቱ ዘርፍ ከተከናወኑት ተግባራት መካከል ከተለያዩ አገራት፣ ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችሉ ስምምነቶች መከናወናቸው ሲሆን፤ ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ከደቡብ ኮሪያ (ከጠቅላይ ሚኒስትርና ትምህርት ሚኒስትሩ ጋር)፣ ከኳታር መንግስት፣ ከአሜሪካው የረትገር ዩኒቨርሲቲ ወዘተርፈ ጋር የተደረጉት ስምምነቶች፣ የተደረሰባቸው መግባባቶች በትምህርቱ ዘርፍ ደርሶ የነበረው ጉዳት መልሶ ለመጠገን ያግዛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## ሂደታችን ነካ ነካ ነውና አሁን ደግሞ ወደ ስልጠናዎች እንሂድ።

ትምህርት ሚኒስቴር ባሳለፍነው 2016 ካከናወናቸው በርካታ ተግባራት መካከል እንደ ስልጠና መስጠት ሲሆን፣ ከእነዚህ ስልጠናዎች መካከል ደግሞ በአይነቱም ሆነ ይዘቱ "ልዩ" የተባለው ይገኝበታል።

የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሀኑ ነጋ ፐ/ር የ2016 ዓ.ም የሁለተኛው ሩብ ዓመት የስራ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርትን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ባቀረቡበት እለት ስልጠናው የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን አቅም ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ገልፀው ነበር። በወቅቱ ከስልጠናዎችም ትኩረትን አግኝቶ የነበረው ደግሞ "ልዩ" የተባለው ስልጠና ነበር።

በዚሁ መሰረትም "ለተከታታይ 24 ቀናት ሲሰጥ የቆየው የመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮች ልዩ አቅም ግንባታ ስልጠና" ተጠናቀቀ። ስልጠናውም "መምህራን በሚያስተምሩበት የትምህርት አይነት፣ የማስተማር ስነ-ዘዴ እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ክህሎት ላይ ብቃታቸውን ለማሻሻል ታሳቢ ተደርጎ ለመምህራን የ120 ሰዓታት፣ ለትምህርት ቤት አመራሮች ለ60 ሰዓታት ተሰጥቷል።"

ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 16/2016 ዓ.ም የተካሄደው ልዩ የክረምት መርሀ-ግብር ስልጠና በ28 ዩኒቨርሲቲዎች ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፤ 49ሺህ 505 መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች፣ 2ሺህ 892 አሰልጣኞች፤ እንዲሁም 224 ዋና አሰልጣኞች ተሳትፈውበታል። በስልጠናው መሰረትም 2017 የተሻለ የመማር ማስተማር ውጤት ይመዘገብበታል ተብሎ ይጠበቃል።

በመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ከእንባ ጠባቂ ተቋም የዋንጫ ተሸላሚ የሆነው የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የሰጠው ስልጠና ይህ ብቻ አይደለም። ከዚህ ከ"ልዩ የክረምት መርሀ-ግብር ስልጠና" ባሻገር ሌሎች በርካታ ስልጠናዎች በተለያዩ እርከን ለሚገኙ አባላት የተሰጡ ሲሆን፣ በተለይ ለተማሪዎች የተሰጠና እየተሰጠ ያለው የስቴም (STEM) ስልጠና፣ በተለያዩ አገራት የተካሄዱ ስልጠናዎችን፣ የውጪ የትምህርት እድሎችን፣ ሌሎች ውድድሮችን (በቻይና፣ ሁዋዌ የተካሄደውን ጨምሮ) እና እዚህ ያልዘረዘርናቸው በርካታ የስራ ላይና ከስራ ውጪ ስልጠናዎች ተሰጥተው አቅም የማጎልበት ስራዎች መሰራታቸውም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተከታታይ የሚወጡ ሰነዶች ያስረዳሉ።

በወፍ በረር ያደረግነውንና በትምህርቱ ሴክተር በተጠናቀቀው ዓመት የታዩትን የዋና ዋና አፈፃፀሞች ምልከታ በዚሁ እናበቃለን።

## ልዩ ዕትም

# ጥበብ እንደምን ሰነበተች?

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



እንደምን ነሽ ዛሬ... እንዴት ነበርሽ ትናንት? ማለት ሊያስፈልገን ነው። ወደፊት በመገስገስ ውስጥ አንዳንዴም መለስ ቀለስ እያሉ ወደኋላ መመልከትን የመሰለ ነገር የለም። ብዙ ያወራ ሰው ኋላ ላይ ስለምን እያወራ እንደነበር መልሶ ለራሱ ቢሰማው ትምህርትም ትውስታም ጭምር ነው።

ዓመቱን ሙሉ ሁለትና ሦስት ምዕራፎችን እያጠና የተፈተነ ተማሪ በዓመቱ መጨረሻ ለማትሪክ ሙሉ መጽሐፉን፣ ሙሉውን ደብተሩን ያገላብጣል። የማያውቀውን አውቆ፣ የሚያውቀውንም ያስታውሳል። እኛም ለፈተናው ባይሆንም ለማወቅና ለማስታወሱ እንደምን ሰነበትሽ ትናንት ማለታችን ግድ ነው።

365 ቀናትን ይዛ ስትመጣ አዲስ ዓመት፣ አውዳመት ብለን የተቀበልናት 2016 ዓ.ም፤ የያዘቻቸውን ቀናት በሙሉ አንድ በአንድ ስትጥል... ስንቀበላት ከርማ አሁን የቀራት የለም። እኛም ዝምድናዋን ጨርሰን አሮጌ ስንል ወዲያ ግድም ልናስፈነጥራት ነው። የምንወዳትም ያልወደድናትም ሳንወድ በግድ ተለያይተን ከሌላ አዲስ ዓመት ጋር እፍ ጥብስ! ልንል ነው። 2016 ዓ.ም በይ ደህና ሰንብቺ! መንገዱን ጨርቅ ያድርግልሽ! እያልን ሌላ የ2017 ዓ.ም ወርቅ ግን እንጠብቃለን።

ይሁንና ከፋም ይሁን ደግ ትዝታ መልካም ነው። ትውስታም ስንቅ ነው። የሸኘነውን ሸኝተን የመጣውን ስንቀበል፤ ነገ የሚያጓጓን ያህል ትናንትም ሊናፍቀን ይገባል። ዛሬ ያለ ትናንት፣ ነገም ያለዛሬ አይገነባምና ሁሉንም ከትናንት መጀመር መልካም ነው።

ብዙ ትናንትናዎች ግዙፍ ኪነ ጥበብ ከዚህ 2016 ዓ.ም ጉበን ላይ በነጭና በጥቁር፣ በወርቃማና በግራጫ ቀለማት የተጻፉ፣ ተጽፈው የተነበቡ ጉዳዮች እልፍ ናቸው። እልፍ እያሉ ከእልፍኙ እልፍ ቢሉ ሳሎን ጓዳ፣ ደጅና ማጀቱ ሁሉ የሚነገር የሚዘከር የጥበብ ውበት አለ። ጋራ ሸንተረሩን አቋርጠው፣ ከአውድማው በጎን፣ ከማሳው ከመሃል ሰንጥቀው ቢያልፉ ከ2016 የጥበብ መንደር ላይ ያሸተ አዝመራ፣ የጎመራ ፍሬ ነው። የጎመራን ፍሬ እላይ ሆኖ ባይበሉትም ሲያዩት ምራቅን ያስውጣል። የአዝመራ እሸትም ታይቶ አይታለፍምና ቀንጠስ! ቆንጠር! እያደረጉ ለአምሮት ታህል መብላቱ የወግ ነው።

እንግዲህ ብዙ እያሸን ብዙ ለመብላቱ ባንችልም ከ2016 ዓ.ም የኪነ ጥበብ ማሳ ላይ እልፍ እያልን የበላነውን የጥበብ አዝመራ እየቀመሰን እናስታውሰው። በዚህ 2016 ዓመት ውስጥ ምን ተሠርቶ፣ እንደምን ታለፈ?

አስቀድመን ጠቅለል ካለው እየጠቀለልን እንሂድና በ2016 ዓ.ም በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ከተከናወኑ አበይቶች መካከል አንዱ ወደ ስነ ጥበብ ቤት ያመራናል። እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ በስነ ጥበቡ ዘርፍ ከዓለም ቀደምት ብትሆንም ዘርፉ እምብዛም ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቷል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ሚያዚያ 7 ቀን (አፕሪል 15) የሚከበር ቢሆንም በሀገራችን ግን ይህን ዕድል ሳያገኝም ከርሟል። በዘንድሮው ዓመት የሆነው አዲስ ነገር፤ በሀገራችን የመጀመሪያው የዓለም የሥነ ጥበብ ቀን እና የኢትዮጵያ ጃዝ ሙዚቃ ቀን መከበር መጀመሩ ነው።

ሌላው በወርሃ ህዳር ለኪነ ጥበብ አዲስ የሀይል ምንጭ የሆነ ጅማሮ ነበር። አንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል ለረዥም ዘመናት የቆየ የጥበብ አሻራ ባለቤት ነው። ባህል ማዕከሉ በተለይ ደግሞ ቀደም ባሉት ዘመናት ስመ ጥር ገናና ነበር። ከጊዜያት በኋላ ግን ከደበዘዙና መኖር አለመኖራቸውም ከማይታወቁት እስከመሆን ደርሷል። በ2016 ግን ከጣላቸው ነገሮች አንኳር የሆነውን አንደኛውን ነገር ቀስቅሶ ዳግም አስጀምሯል። ይታወቅበት የነበረውንና በመሃል የተወውን የኪነ ጥበብ ምሽቶችን መሰናዶ ዳግም በሕዳር ወር አስጀምሯል። ቀደም ሲል ከዚህ የተገኘው ፍሬ ብዙ እንደመሆኑ አሁንም ለ2017 ዓ.ም እና ቀጥሎ ብዙ ፍሬዎች ከዚሁ ይፈሩም ይሆናል።

ከዚሁ ጥቅልል ርዕሰ ጉዳይ ሳንወጣ...የሁል ጊዜም የኪነ የኪነ ጥበብ ጎጆ ጩኸት አንደኛው በመንግሥት ዘንድ የሚሰጠው ትኩረት በቂ አይደለም የሚል ነበር። ታዲያ ጩኸቱ ተደምጦ ጥያቄው ተመልሶ ይሆን? አሁንም በሚገባና በበቂ ሁኔታ ትኩረት አግኝቷል ለማለት ባይቻልም ከሌላው ጊዜ በተለየ ግን ጥሩ ጅምሮችን የተመለከትንበት ዓመት ነበር። ስለዚህ ጉዳይ ስናነሳ በመጀመሪያ የቀስቱ ጫፍ ወደ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ይጠቁመናል። ለኪነ ጥበቡ ከተደረጉ ከመልካም ግብሮች አንደኛው የ"ክብር ለጥበብ" ሽልማት ነበር። ሽልማቱ ለሦስተኛ ጊዜ ቢሆንም ብዙ አዳዲስ ነገሮችን አካቶ የመጣው ግን በዘንድሮው ላይ ነበር። ከዚህም አንዱ ሽልማቱ ሀገር አቀፍ በማድረግ የክልል ባለተሰጥኦዎችንም ያበረታታ ነበር።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ፊቱን ወደ ኪነ ጥበብና ለኪነ ጥበብ ማዞሩን ያሳየበት ሌላኛው አዲስ ጉዳይ ከሰኔ 13 እስከ ሰኔ 15 ለተከታታይ ሦስት ቀናት ያካሄደው ሀገር አቀፉ የኪነ ጥበብና ስነ ጥበብ ውድድር ነበር። ከዚህ ቀደም በነበሩ ልዩ ልዩ ውድድሮች ውስጥ ተወዳዳሪዎች ከየክልሉ በግል ፍላጎት እየመጡ ሲወዳደሩ ነበር። ይሁንና ክልሎች የባህል እሴቶቻቸውን የማሳየት ዕድል ያመቻቹ ውድድሮች ሲካሄዱ አይታይም ነበር። ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው በዚህ ውድድር ላይ እያንዳንዱ የውድድር ይዘት ባህል ተኮር መሆኑና ሁሉንም አሳታፊ በማድረጉ ባህል ላበቀለው የሀገራችን ኪነ ጥበብ የከፍታ ድልድይ ነው። የዛሬ ጅምር የስኬት ፍሬው ነገ ላይ ነውና ጅምሩ አድጎና ተመንድጎ ነገ ላይ እንመለከተው ይሆናል።

2016 ዓ.ም ካሉ ኪነ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብ ካሉም አንዱ ሙዚቃ ነው። ሙዚቃ...ሙዚቃ ምን አለ በሙዚቃ? ምን ጠፍቶ ምን የለም ይባልና...ስንት አጃኢብ! ያስባሉን ስንቱ አልበም አለ አይደል... መርጦ መስማቱን፣ ሰምቶ መሸለሙን ለናንተው ልተውና በዚህ ዓመት ከወጡ አልበሞች አንድ ወደፊት አንድ ወደኋላ እያልን አንድ ሁለት እንበል።

ለብዙ ጊዜያት በነጠላ ዜማዎቹ ልባችንን ሲደርስ የነበረው ወጣቱ ድምጻዊ መሳይ ተፈራ ካሳ "የልቤን" የተሰኘውን የመጀመሪያ አልበሙን እንካችሁ ያለን በወርሀ ሰኔ ላይ ነበር። እጅግ ጥንቅቅ ባለ ተወዳጅ የአልበም ሥራ እዚያ የጥር ወር ላይ ደርሶ አድምጠነዋል። እሱም የማርያም ቸርነት "የደጋ ሰው" የተሰኘው አልበም ነው። "አስቻለ" አስቻለው ፈጠነ (አርዲ) ለየት ባለ የባህል አዚያዚያም ስልቱ ሙሉውን አልበም ጀምሮ ጨርሶታል። ከዚያው የጥር ወር ሳንወጣ፤ በጥር 24/ 2016 ዓ.ም "ሕይወት" የተሰኘው የዳዊት ቸርነት አልበምም አለ። ካሳሁን እሸቱ ደግሞ በጥር 17/2016 ዓ.ም "ይሁን" ያለን ሌላኛው ባለ አልበም ነው።

ከታህሳስ ግርግር ቀደም ብሎ ሕዳር ሲታጠን ፍቅር የሺዋስ "ፍቅር" ነበር፤ ቅሉ ግማሽ አልበም ቢሆንም። "ልዑል" የሕዳር 28 የራሱ የልዑል ሲሳይ አልበም ነበር። ወርሃ የካቲት ላይ ሁለት አዳዲስ አልበሞች ተደምጠዋል። ሲደመጡም የዋዛ አልነበረም። በየካቲት 1 ቀን 2016 ዓ.ም የማስተዋል እያዩ "እንዚራ" እና በየካቲት 3 ደግሞ የሮፍናን ኑሪ "ሐራምቤና ኖር" ተከታትለው ገብተዋል።

በመጋቢት ወር ላይ በንጉሡ ፈረስ እሳት ለብሶ "እሳቱ ሰ" አልበም ከች ብሏል። የጀምበሩ ደመቀ የሆነው ይሄው አልበምም በመጋቢት 13 አድማጩን ተገናኝቷል። የአልበሙ ዥረት ማቆሚያም መቆሚያም አልነበረውም። በግንቦት 6 የእብነ ሐኪም "ብራና" እንዲሁም በግንቦት 9 ደግሞ የለምለም ኃ/ሚካኤል "ማያዬ"ን አይተናል። የእውነትም ፓፓፓ! የሚያስብል ነበር። ያለው ግን አብዱ ኪያር ነበር። ግሩም የሆነውን አልበም ሠርቶ ሐምሌ 21 ቀን "ፓፓፓ" ከሚል መጠሪያ ጋር አውጥቶታል።

አንጋፋዎቹ በ2016 ከፊትም ከኋላም፣ ከጅምር እስከ አጨራረሱ አልደከሙም። የራፕ ስልት አቀንቃኙ ልጅ ሚካኤል ዘንድሮም አለን! አለን! ብሏል። ካሳለፍናት የነሐሴ ወርም ምርጥ ምርጡን አሰምተውናል። በክረምቱ በነሐሴ ብርድና ቆፈን "አንድ ቃል" ደርሶ ሳይታደገን አይቀርም። ተወዳጁ ሚካኤል በላይነህ በነሐሴ 17 ጀባችሁ እንዳለን ነው። ሞትን ይረሳኝ! ያውም የትናንቷን እሷን እንደምን ይረሳ..."መጠሪያዬ" ነው ብላለችና ቬሮኒካ አዳነንም አንረሳም። ብዙዎች ያደነቁለትን የጉቱ አበራን "ጋፊ ጎ"ን እንመርቅና ቀሪውን ቤቱ ይቁጠረው።

2016 ከደራሲያን ዓለምም አልቦዘነችም። አንባቢው ሲመናመን ቢሄድም ደራሲያኑ ግን በጀ! ሳይሉ ለአመልም ቢሆን ከመጻፍ አንቆጠብም ብለው በታላላቅ ሥራዎቻቸው ስነ ጽሁፉን አሙቀውታል። ከእነዚህም የመጀመሪያው ታላቁ ደራሲ ፍቅረማርቆስ ደስታ ነው። ከሀመሮቹ መንደር ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ እየከተበ ሲያስነብበን ከነበረው ጣፋጭ ጦማር ድንገት ብድግ ብሎ ሰው ሀገር እንደገባ ለብዙ ጊዜያት ጠፍቶብን ከርሞ ነበር። ታዲያ እጅ ነስቶ ሲመለስ እጅ ስሞ ስጦታ አበረከተልን። እርሱም "የሚሳም ተራራ"ን ነበር። ከተራራው ላይ ከወጣበት አስወጥቶ፣ ከወረደበት እያስወረደን ድንቁን ግለታሪክ እንድንኮመኩም አድርጎናል። ነገርን ነገር ያነሳዋልና የፍቅረማርቆስና የሀመሮቹን ጉዳይ ሳስታውስ "ዶሳይስ" ትዝ አለኝ። መጽሐፉ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ሲሆን ጸሀፊዋ ደግሞ ኩሪ አየለ ናት።

ከአንድ ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ የሚፈልቁ የባህል እሴቶችን የሚያንጸባርቅ በመሆኑ ምናልባትም ትውስታው ለዚህ ይሆናል። በ2016 ዓ.ም ቆንጆ ሥራ ይዘው ብቅ ያሉ አዳዲስ ደራሲያንም ነበሩ። "አባት ዐልባ ሕልሞች" ዳጎስ ካሉ ገጾቹ ጋር ፈርጠም ብሎ የመጣ የደራሲ ማስረሻ ማሞ የበኩር መጽሐፉና ለስነ ጽሁፍ የሰጠው በኩራቱ ነበር። በወርሃ የካቲት እውነትና ትረካ፣ ትረካና ታሪክ በመጽሐፍ ተገናኝተዋል። ከዓመታት በፊት ብዙ ኢትዮጵያውያንን ያስነባው የቦይንግ አውሮፕላን መከስከስን ተከትሎ የወጣቱ አብራሪ ታምራት ሙሉ ሁኔታ ይባስ አንጀት ሲበላም ነበር። እናም እርሱን በዋና ገጸ ባህሪ ወንበር አስቀምጣ ታሪኩን ወደመጽሐፍነት የቀየረችው ደግሞ እህቱ ፋሲካ ሙሉ ነበረች። "ያልገሩትን ፈረስ" በሚል ርዕስ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተውን የልቦለድ ይዘት ያለውን መጽሐፏን በየካቲት 30 ቀን 2016ዓ.ም ለንባብ አብቅታም ነበር። "ጥላዬን ቀደምኩት" በጥላዬ ታደሰ፣ "አይሆንም ሰረዝኩት" (የግጥም መድብል) በገጣሚ አብርሃም አስቻለው እና ሌሎችም የመጽሐፍት ዓለም በረከቶች በ2016 ዓ.ም ተበርክተዋል።

ፊልምና የፊልም ጥበብ በዓመቱ ሞቅ ደመቅ ብሎ አልፏል ለማለት ይቻላል። ከዚህ ቀደም ስንከሳር የነበሩ ብዙ ጉዳዮች ለመመንገል የተደረጉ ጥረትና ጥበባዊ ተጋድሎዎች አይዘነጉም። ሰማይ በብሩህ ደመና፣ ምድር በአደይ አበባ በተንቆጠቆጡበት ወርሃ ጥቅምት ሁለት የሀገራችን ፊልሞች በአበባው እንዳሸበረቁ ወደ ባህር ማዶ ተሻግረዋል። የኢትዮጵያን ፊልሞች በአውሮፓና አሜሪካ ከተሞች ውስጥ በማሳየት የአምስት ዓመታት ያህል ልምድ ያለው ሀበሻ ቪው፤ በዘንድሮው ዓመትም ከ30 ዓመታት በፊት የተሠራውን "ጸጸት" የተሰኘውን ፊልም ጨምሮ ከቅርብ ደግሞ "ዝምታዬ"ን በማከል ቀጠሮውን በለንደን ከተማ ውስጥ አድርጎ ነበር። ፊልምና ቴክኖሎጂን ያዋደደውና የነገ ተስፋና ማሳያ የሆነው "አስተውሎት" የተሰኘውን ፊልም የተመለከትነውም በ2016 ዓ.ም ነበር። ፊልሙ ቀርቦ የነበረው በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ሲሆን ቴክኖሎጂ ሰራሽ ሮኅቦቶችን በመጠቀም የኢትዮጵያን የፊልም ኢንዱስትሪ በማዘመኑ ትልቁን ተስፋም ተጥሎበታል።

እጅግ ተወዳጅና ዓለም አቀፍ እይታን ያገኙ ፊልሞችን ከመመልከት አንጻር እንደ "ዶቃ" ያሉ ድንቅ ፊልሞችን የተመለከትንበት ዓመትም ጭምር ነው። እንዲያው ካለማውራት ማውራት ይሻላል በማለት እንዲሁ ለጨረፍታ እንጂ በፊልም ኢንዱስትሪ ውስጥ የተከናወነው እንኳን ብዙ ነበር።

ብዙ መልካም ነገሮች ሆኗዋል። እኛም ሰምተናል። ተመልክተናል። ግን ደግሞ ጥሩ ነገሮች ባሉበት መጥፎ ክስተቶችና አጋጣሚዎች እንዳፈጠጡ ነው። በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ደስታ ሁሌም ጣፋጭ ነገር ቢሆንም መርጦ መኖር ግን አይቻልም። በምንፈልገውና በምንመርጠው ልክ የማንመርጣቸውና የማንፈልጋቸው ነገሮች ይመጣሉ። ከእነዚህ አንዱ ሞት ነው። ሞትም ሆነ መወለድ ከሰው ልጆች ፍላጎትና ምርጫ ውጭ የሆኑ ነገሮች ናቸው። በዘንድሮው ዓመት ብዙ መልካም የኪነ ጥበብ ጣፋጮችን እንደበላን ሁሉ ድንገት መራራ የሆኑ ዜናዎች ከጆሯችን እየገቡም እንዲሁ አዝነን ልባችን ተሰብሯል።

ጥበብን ለኛ የሰጡ እነርሱ ግን ለሞት ተሰጥተዋል። ከእነዚህም መካከል አንጋፋውን ድምጻዊ ሙሉቀን መለሰን አንደኛው ነው። ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ ደግሞ ሌላኛው ነው። በ70 እና በ80 የዕድሜ እርከን ወደ ሞት ተጉዘዋል። ክረምት መጣሁ መጣሁ እያለ ሰማይ የጉም ጭጋግ ለብሶ ሲያስገመግም ከወረዱ መብረቆች አንዱ የጥበብን ቤት ያደባየ ይመስላል። በተለይ ከሦስት ወራት ወዲህ የሞት ክንድ አለት የሚሰብር መዶሻ ያህል ጠንከር ብሎ ነበር። በዚሁ ሰለባ ከሆኑትም ሰዓሊና ገጣሚ ነብይ መኮንን ይገኙበታል። በሰኔ ዶፍ አውሎንፋስ ቀላቅሎ በሞት ወሰደው። ደግሞ እንደገና ሁለት አንድ ዓይነት ድንገቴዎች ተከታትለው መጡ። ነሐሴ 18 እና ነሐሴ 19 እጅግ አስፈሪ ነበሩ። በቀን 18 ወጣቱ የ60 ፊልሞች ባለጸጋ ጌታቸው እጅጉ (ባቡጂ) አረፈ። ቀጥሎ ደግሞ በቀን 19 የቲያትር ፈርጥ የነበረው ከያኒ ኩራባቸው ደነቀ ላይመለስ ተከትሎ ሄደ።

እንግዲህ ያለፈው እንዲህ ባለመልኩ አልፎ ከ2016 ጋር ለመተላለፍ የቀረን የለም። ታዲያ እሱም ገጭቶን፣ እኛም ተሳድበን እንዳንተላለፍ ያሳለፍነው ጥሩም ቢሆን መጥፎ ኋላን በፍቅር ተምሮ ማለፍ ታላቅነት ነው። ለነገ ነገ ብቻውን በቂ አይደለምና ከዛሬ ቆርሰው የያዙት ስንቅ ለራስ ነው። እንደምን ሰነበተች እያልን ጥበብን በ2016 ዓ.ም ስንቃኛት ከባህር ላይ የጭልፋ ታህል ብትሆንም ለቀጣዩ ጥቂት ማስላሰያ ትሆናለች። የዛሬው ዳሰሳ ለነገው አዲስ አሰሳ መንገድ ነውና መንገዱን እንሳት።

ልዩ ዕትም

# መስከረም የወራት አውራ

ኃይለማርያም ወንድሙ



በኢትዮጵያውያን ዘንድ የመስከረም ወር የተለየ ስሜት ያለው በመሆኑ የወራት ጌታ ይባላል። አንዳንዶች የወራት እማወራ ሲሉት፤ ከፊሎች የወራት አባውራ ሌሎች ደግሞ የወራት አውራ በሚል ይገልፁታል። ይህ ስያሜው የሚያመላክተው ወሩ የዓመት መጀመሪያ በመሆኑ ክረምት አልፎ የመኸር ወቅት የሚመጣበት ስለሆነ ልዩ ፍቅር አላቸው። በዚህ ሳቢያም ከወራቶች ሁሉ ሰዎች ለመስከረም ያላቸውን ፍቅር ልዩ ያደርገዋል። መስከረም ወር ሊጠባ ሲል የልጃገረዶች፣ የልጆች፣ የኮረዶችና የኮበሌዎች ጨዋታ ይደራል። በንጉሡ ዘመን ተማሪዎች በመስከረም ወር

‹‹ መስከረም ለምለም
ከወራቱ ሁሉ እንዳንቺ የለም
መስከረም መስከረም የወራቱ ጌታ
አበቦች
ጀመሩ ካንቺ ጋር ጨዋታ። ›› እያሉ ይዘፍኑ ነበር።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ቡሄ የሚባለው የወንዶች ጭፈራ እና ዝማሬ የሚደራው በነሐሴ አጋማሽ መሆኑ ይታወቃል።ያው ‹‹ቡሄ ከዋለ የለም ሌሊት ዶሮ ከጮኸ የለ ክረምት›› እንደሚባለው ጭፈራው ሁሉ አዲሱን ዘመን በማስታከክ የሚካሔድ ነው። የኮበሌዎቹ ጭፈራ ሲደራ ኮረዶች ደግሞ በተራቸው ለአሸንዳ/አሸንድዬ ሻደይ ዐይኒ ዋሪ ጭፈራ ይዘጋጃሉ። ባህላዊውን የፀጉር አሠራር ይሠራሉ ። በባህላዊ አልባሳት ይለብሳሉ በጆሮና አንገት ጌጦችም ያጊያጊጣሉ፤ ይደምቃሉ። ተኳኩለው፤ ተቀነዳድበው፤ አምረውና ተውበው የሚጠብቁት የሚናፍቁት ጊዜው ሲደርስ ከበሯቸውን እየመቱ ባህላዊ የጭፈራ ዘፈናቸውን እየዘፈኑና እየጨፈሩ በየቤቱ ይዞራሉ።

ደስታ ተክለወልድ ዐደይ የሚለውን ቃል ሲፈቱት፤ በቁሙ ዐደይ ጥለት ማለት ነው። ዐደይ አበባ በመስከረም የሚፈነዳ የምድር ጌጧ ሽልማቷ ሲሆን፤ ዐደይ ለአበባ ቅጽል ወይም ዘርፍ ሲሉ አስታውቀዋል። ዐደየ የበጨጨ ቢጫ መሰለ፤ ነጣ፣ ነጭ ሆነ ፣በአፋን ኦሮሞ ነጭ ዐዲ፣ ፀሀይ ዐዱ የሚባለው ከዚህ የወጣ ነው ሲሉ ይገልጻሉ። በተጨማሪም ዐደይ የበጨጨ ቢጫ የሆነ አበባ የመስቀል ዕለት ልጃገረዶች አክሊል (ዐደይ አበባ ጎንጉነው ግንባራቸው ላይ አድርገው በራሳቸው ላይ የሚያጌጡበት) ነው። ወቅቱ እንኳን ሰው ጋራው ሸንተረሩና ኮረብቶች ሁሉ በአደይ አበባ ስለሚያጌጥና በለምለም ሣር የሚዋቡበት መሆኑ ወሩን በሰዎች ዘንድ ተወዳጅ እንዲሆን አድርጎታል።

ዐደይ በተለያዩ ቋንቋዎች የራሱ የሆነ ብያኔ አለው። ለአብነት በትግርኛ እማዬ ፤ በጉራጌ ‹አዶ› እናት ማለት ነው። በአፋን ኦሮሞም አዴ ወይዘሮ ወይም እናት የሚል ትርጉም ይሰጠዋል። በሲዳምኛም አዴ እናት ማለት ነው። ስሙን ስታዩት መመሳሰሉ ምናልባት ከዐደይ አበባ ጋር የሚያመሳስለን የሚያስተሳስረን ነገር እንዳለ ሆኖ፤ ኢትዮጵያውያን በቋንቋ ብንለያይም መስተጋብር እንዳለን አንዱ አመላካች መሆኑን ያሳያል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብዝሃ ሕይወት ትምህርት መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሰብስቤ ደምሰው ባንድ ወቅት በአሜሪካ ድምፅ ፤በአማርኛ አደይ አበባ ወይም የመስቀል አበባ፣ በኦሮምኛ 'ኬሎ'፣ በትግርኛ ደግሞ ገልገለ መስቀል ተብለው የሚጠሩት ዕፅዋት በሳይንስ መጠሪያው 'ባይደንስ' እንደሚባል በኢትዮጵያ ብቻ የሚበቅል እንደሆነ ገልፀው ነበር።

መስከረም አእዋፋት እንስሳት እጽዋት፣ ነፍሳት (ንብና ቢራቢሮ) በምድር ልምላሜ ተደስተው የሚፈነጩበት ሣር እየነጩ ውሃ እየተጎነጩ የሚደሰቱበት ወራት ነው። መስከረም ባለ ብዙ ስም ነው። ዘመን መለወጫ፣ እንቁጣጣሽ፣ አዲስ ዘመን፣ አዲስ ዓመት፣ ዐውደ ዓመት የመሳሰሉት ስያሜዎቹ ናቸው። መስከረም በስያሜም የከበረ በልምላሜም ያመረ ወር ነው። የመስከረም ወይም የአዲስ ዓመት ‹ብራንዱ› ትዕምርቱ፣ (ምልክቱ) ደግሞ አደይ አበባ በየቦታው መብቀሉ ነው። በመስከረም የሚከበረው የመስቀል ደመራና የእሬቻ ጭፈራ አንዱ ድምቀት የአደይ አበባ ውበትና ለምለም ሣር ነው።

አደይ አበባ ዓመቱን ጠብቆ በአዲስ ዓመት መባቻ በኢትዮጵያ ብቻ የሚበቅል የኢትዮጵያውያን መለያ ነው። ትዕምርቱ ያልነውም ለዚሁ ነው። አደይ አበባን በመስክ ላይ መብቀሉን መፍካቱን አይተው ቀን መለየት የማይችሉ ሰዎች አዲስ ዓመት እንደባተ ያውቃሉ።

መስከረም አእዋፋት በክረምቱ ወራት ተዘርቶ የደረሰ አዝዕርት ላይ እያረፉ እንደልባቸው እየተመገቡ ልዩ ዝማሬ የሚያሰሙበት ከቦታ ቦታ እንደልብ የሚበሩበት የሚደሰቱበት ወር ነው። በክረምቱ ወራት ላሞችና ኮርማዎች በለመለመው መስክ የሚፈረጥጡበት ወቅት ነው። ይህን ጽንሰ ሀሳብ ሰዐሊና ገጣሚ ነፍስ ሔር ገብረክርስቶስ ደስታ አንተነህ መስከረም በሚለው ግጥሙ

‹‹... አንተነህ መስከረም
የሐምሌን ጨለማ
የነሐሴን ዝናም
የሻርከው አንተ ነህ
በብርሃን ውበትህ ...
ዕንቁጣጣሽ አንተ ስጦታህ የበዛ
ለሰው መታሰቢያ ውበት የምትገዛ ።
በሽቱህ መዓዛህ ለውጠው ዓመቱን፣
ይታደስ ያረጀው ፍጥረት ሌላ ይሁን ።
ከምረው ዘመን ካው ባመት ባመት፣
በወሩ ደረጃ ፍጥረት ይጓዝበት።
ፍየሎች ይዝለሉ ቅጠል ይበጥሱ፣
ከተሰደዱበት ወፎች ይመለሱ።
ይልቀሙት እህሉን ይሥሩ ቤታቸውን
ይሥፈሩበት ዛፉን ።
የደስ ደስ ያሰሙ ንቦች ይራኮቱ፣
ይንጠራሩ አበቦች ይንቁ ይከፈቱ።
አንበሳና ግልገል በመስኩ ይፈንጩ፣
ከብቶች ሳሩን ይንጩ፣
ሕፃናት ይሳቁ ይሩጡ ይንጫጩ። ...›› ሲል ገጥሞት ነበር።

**አበባ የሚለው ዘፈን በሬዲዮ ሲለቀቅ ትዝታ የሚጭር ሐሴት የሚፈጥር ነው። እንግጫ ነቀላና በኮረዶች መስከረም ሲደርስ የተለመደ ነው። በአፋን ኦሮሞ ቡቃሳ ይባላል። ለአዲሱ ዓመት እንግጫ ነቅለው ኮረዶች ቡቂሳ ቡቂፈና እያሉ ይዘፍናሉ።**

ክረምት ለገበሬው የተስፋ ወራት ቢሆንም ለከተሜዎች የፈተና ወራት ነው። ገበሬው ክረምቱን ሳይሳቀቅ በረዶው ዶፉ እየወረደበት እርሻውን እያረሰ ዘሩን የሚዘራበትና የዘራውን የሚያርምበት ወቅት ነው። ዝናቡን በመሳቀቅ እርሻውን የማያርስ ከሆነ ለመጪው አዲስ ዓመት ለረሀብ ለስደት ይዳረጋል። ‹‹ መስከረም ሲጠባ እንኳን ሰው፤ ዘመዱን ይጠይቃል ባዳ ›› የተባለውም ዝናብ በማይዘንብበት ወንዝ ባልሞላበት ወቅት እንደልቡ መሄድ ዘመድ አዝማድ ወዳጅ ወላጅ መጠየቅ ስለሚቻል ነው።

መጽሐፉም "በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ" ይላል። ስለዚህ የተሻለ ነገር ለማግኘት ፈተናን መጋፈጥ ግድ ይላል። መስከረም የሁለት ቃላት ጥምር ነው። መስ አለፈ ሲም ከረም ደግሞ ክረምት ማለት ነው። ፍቺው ክረምት አለፈ ማለት ነው። በያዝነው ክረምት እንደሀገር ብዙ መከራዎች አጋጥመውናል። ብዙ ዜጎች ህይወታቸው አጥተዋል።

በተለይ የመሬት መደርመስና መንሸራተት ጎፋን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሰዎች ከመሞታቸውም በላይ ቤት ንብረታቸው የፈረሰባቸው ብዙ ዜጎች አይተናል። ህም ተልቅ የፈተና እና የመከራ ጊዜ ሆኖ አልፏል። በክረምት ሰዎች እርስ በርስ ለመጠያየቅ በተለይ በገጠር ዝናቡና የወንዝ ሙሌት ስለሚያስቸግር ከቦታ ቦታ እርስ በርስ እንደልብ ለመንቀሳቀስ ይቸገራሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ መዝሙረ ዳዊት 146፥8 ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና ወያስተዴሉ ክረምተ ለምድር ዘያበቊል ሣዕረ ውስተ አድባር ይላል።ትርጉሙ፡-ሰማዩን በደመና የሚሸፍን ለምድር ክረምትን የሚያዘጋጅ በተራሮች ላይ ሣርን የሚያበቅል ማለት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ቀልደኛ ገበሬ በሰኔ ይሞታል እያሉ ሲናገሩ በተደጋጋሚ ሰምቻለሁ። መቼም ሞት ድንገተኛ ጥሪ ነው እንጂ ሰዎች ተዘጋጅተው የሚመጣባቸው እንዳልሆነ ይታወቃል። ለማለት የፈለጉት እርሻ በጣም በሚፈልጉት ወሳኝ ሰዓት ተሰወረ ለማለት ነው።

‹‹ ዕንቁጣጣሽ እንኳን መጣሽ፣
በአበቦች መሀል እንምነሽነሽ። ››

አበባ የሚለው ዘፈን በሬዲዮ ሲለቀቅ ትዝታ የሚጭር ሐሴት የሚፈጥር ነው። እንግጫ ነቀላና በኮረዶች መስከረም ሲደርስ የተለመደ ነው። በአፋን ኦሮሞ ቡቃሳ ይባላል። ለአዲሱ ዓመት እንግጫ ነቅለው ኮረዶች ቡቂሳ ቡቂፈና እያሉ ይዘፍናሉ። ይህም ዐደይ አበባን ዐይተን ባህላችን መስተጋብርና ትስስር እንዳለው መረዳት እንችላለን። አደይ አበባም በየቦታው መብቀሉ ኢትዮጵያውያን በባህል በእምነትና ቋንቋ ቢለያዩም አንድ መሆናቸውን ማሳያ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው መስከረም ሲደርስ ትዝ የሚለን የኮሮዶች አበባየውሽ ጨዋታ ነው። አዲስ ዓመት ሲብት አደይ አበባ ሲፈነዳ አበባዮሽ ጭፈራ በኮረዶች በየቤቱ እየዞሩ ይጨፍራሉ፤ ስጦታ ይቀበላሉ። ከአበየውሽ ዘፈኖቻቸው የተወሰኑት ብናነሳና መልካም አዲስ ዓመት ብለን መሰናበት ደስ ይለናል። አዲስ ዓመት የሰላምና የብልፅግና ይሁንልና።

‹‹ .. አበባዮሽ ለምለም አበባዮሽ ለምለም
ባልንጀሮቼ ግቡ በተራ
እንጨት ሰብሬ ቤት እስክሠራ
እንኳን ቤትና የለኝም አጥር
እደጅ አድራለሁ ኮከብ ስጥቆር
ኮከብ ቆጥሬ ስገባ ቤቴ
ትቆጣኛለች የእንጀራ እናቴ
አደይ የብር ሙዳይ
ኮለለ በይ። ››

# ስፖርት ባለፈው የውድድር ዓመት

ብርሃን ፈይሳ

**ዓመቱ ኢትዮጵያ ዝናን ባተረፈችበት የአትሌቲክስ ስፖርት ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የተወከለችበትም ነበር። በየዓለም የጎዳና ላይ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የጀመረው 2016፤ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና፣ የአፍሪካ ቻምፒዮና፣ የአፍሪካ ጨዋታዎች፣ የዓለም ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና፣ ኦሊምፒክን እንዲሁም የዓለም ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና የተከናወኑበት ነበር።**

ትናንት የባተው 2016 ዓ.ም በስፖርቱ ዓለም በርካታ ጉዳዮች የታዩበትና የተስተናገዱበት ሆኖ አልፏል። የኢትዮጵያ ስፖርትም ከሃገር እስከ ዓለም አቀፍ መድረኮች በበርካታ ክስተቶች አልፏል። በውድድር ዓመቱ አንኳር የነበሩ ስፖርታዊ ጉዳዮችም እንደሚከተለው ይዳሰሳሉ።

## አትሌቲክስ

ከቡዳፔስት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ማግስት የተያዘው የ2016 ውድድር ዓመት ጅማሬውን ያደረገው በአትሌቲክስ ስፖርት በተለያዩ ርቀቶች በተሰበሩ ሦስት የዓለም ክብረወሰኖች ነበር። የአዲሱ ዓመት ገጸበረከት የተባለው የሴቶች የ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰን ለወራት ከኢትዮጵያውያን አትሌቶች እጅ ወጥቶ ከቆየ በኋላ በአትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ዳግም ወደ ሃገሩ ሊመለስ ችሏል። ጀግናዋ አትሌት በዓለም ቻምፒዮና የ10ሺ ሜትር ድልን በተጎናጸፈች የቀናት ልዩነት በዳይመንድ ሊጉ የመጨረሻ መዳረሻ ኦሪጎን ሰዓቱን በአምስት ሰከንዶች (14:00.21) ማሻሻል ችላለች።

ከቀናት በኋላ ደግሞ የዓለም ክብረወሰን በተደጋጋሚ በሚሰበርበትና በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ በተሰጠው የበርሊን ማራቶን አትሌት ትዕግስት አሰፋ የማራቶን የዓለም ክብረወሰንን ያሻሻለች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሆናለች። አትሌቷ በርቀቱ የዓለም ቀዳሚዋ አትሌት ለመሆን የቻለችውም ባስመዘገበችው 2:11:53 የሆነ ሰዓት ሲሆን፤ ከረጅም ጊዜ የሕክምና ክትትል በኋላ ዳግም ወደ ውድድር ተመልሳ ስኬታማ መሆኗ የጽናት ተምሳሌት ያደርጋታል። ከሳምንታት በኋላ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በሪጋ በተካሄደው የዓለም የጎዳና ላይ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሶስተኛው የዓለም ክብረወሰን በአትሌት ድርቤ ወልተጂ ሊሰበር ችሏል። በቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ያጠለቀችው ወጣቷ አትሌት በ1 ማይል የጎዳና ሩጫ 4:20.98 የሆነ ሰዓት በማስመዝገብ ታሪክ ሰርታለች።

ዓመቱ ኢትዮጵያ ዝናን ባተረፈችበት የአትሌቲክስ ስፖርት ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የተወከለችበትም ነበር። በየዓለም የጎዳና ላይ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የጀመረው 2016፤ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና፣ የአፍሪካ ቻምፒዮና፣ የአፍሪካ ጨዋታዎች፣ የዓለም ሃገር አቋራጭ ቻምፒዮና፣ ኦሊምፒክን እንዲሁም የዓለም ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና የተከናወኑበት ነበር። ኢትዮጵያን በነዚህ መድረኮች የወከሉ አትሌቶችም በርካታ ሜዳሊያዎች በማስመዝገብ ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ አኩርተዋል።

## ኦሊምፒክ

የዓመቱ ታላቁ ውድድር የ2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ ሲሆን ባልተጠበቀ ሁኔታ ኢትዮጵያ በተቀዛቀዘ ውጤት ነበር ያጠናቀቀችው። ኢትዮጵያ 1 የወርቅ እና 3 የብር በአጠቃላይ 4 ሜዳሊያዎችን በፓሪስ ኦሊምፒክ አስመዝግባ ከዓለም 47ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 4ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው። ይኸውም የስፖርት ቤተሰቡን በእጅጉ ያስቆጣ ውጤት ሊሆን ችሏል። ከዚሁ ኦሊምፒክ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ እሰጣ ገባ እንዲሁም አለመግባባት የተነሳው በተጠናቀቀው ዓመት ነበር። ከውጤት እጦትና የአትሌቶች ምርጫ ጋር በተያያዘ ብዙ ውዝግቦች ታይተዋል። በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ሕገወጥ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ እንዲሁም አሰራሮች ቀጥሎ በሃገር አቀፍ የስፖርት ማኅበራት ክስ ዓመቱ ሊጠናቀቅ ችሏል።

## ታሪክ ሰሪው የፓራሊምፒክ ቡድን

በፓሪስ 2024 ፓራሊምፒክ የኢትዮጵያ ቡድን በ4 ውድድሮች ላይ ተሳትፎ 2 ወርቅ፣ አንድ የብር ሜዳሊያ እና 1 ዲፕሎማ በማስመዝገብ ትልቅ ታሪክ በመስራት ከዓለም 27ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 2ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል። ይህም በኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ተሳትፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ትልቅ ውጤት የተመዘገበበትና




ታምራት ቶላ ከ24 ዓመት በኋላ በኦሊምፒክ ማራቶን ፓሪስ ላይ ሲያሸንፍ፣ ትዕግስት አሰፋ፣ በሪሁ አረጋዊና ፅጌ ዱጉማ የብር ሜዳሊያ ያጠለቁ ኢትዮጵያውያን ሆነዋል፣

ታሪክ የተሰራበት ያደርገዋል። አትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ በሴቶች 1500 ሜትር አይነስውራን ጭላንጭል የወርቅ ሜዳሊያ ስታስመዘግብ፣ በሴቶች 1500 ሜትር T11 ሙሉ በሙሉ ዐይነ ሥውራን አትሌት ያየሽ ጌቴ በራሷ የተያዘውን የዓለም ክብረወሠን በመስበር ጭምር የወርቅ ሜዳሊያ አሸንፋለች። በአይነስውራን ሙሉ በሙሉ (T 11) ምድብ 1500 ሜትር ደግሞ ይታያል ስለሺ የብር ሜዳሊያ አጥልቋል። በወንዶች T46 የእጅ ጉዳት የ1500 ውድድር አትሌት ገመቹ አመኑ 7ኛ በማጠናቀቅ የዲፕሎማ ባለቤት ሆኗል።

## እግር ኳስ

ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን (ዋሊያዎቹ) የአሰልጣኝ ውበቱ አባተን ስንብት ተከትሎ አሰልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ በድጋሚ የተሾሙበት ዓመትም ነበር 2016። የቀድሞው የዋሊያዎቹ አለቃ ስራቸውን የጀመሩትም እአአ በ2026ቱ ዓለም ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታ ነበር። ቡድኑ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሜሪካ ተጉዞ ከጉያና ብሄራዊ ቡድን እንዲሁም ከአትላንታ ሮቨርስ ጋር የወዳጅነት ጨዋታዎችን ማድረግም ችሏል። የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ተሳታፊዎቹ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ኢትዮጵያ ቡናም በተመሳሳይ የሸገር ደርቢ ጨዋታቸውን ከቀናት በፊት በዋሽንግተን ዲሲ አውዲ ፊልድ ስታዲየም አከናውነዋል።

የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ 2016 ዓ.ም የውድድር ዘመን በሁለቱም ጾታ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እግር ኳስ ክለብ አሸናፊነት ተጠናቋል። ይህንንም ተከትሎ በሴቶች

ወደ ገጽ 33 ዞሯል

ልዩ ዕትም



በፓሪስ ፓራሊምፒክ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ቡድን 2 ወርቅና 1 ብር በማስመዝገብ አዲስ ታሪክ ሰርቷል፣

# ስፖርት ባለፈው ...

ከገጽ 32 የዞረ

በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በተደረገው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ አገሮች (ሴካፋ) ቻምፒዮና ንግድ ባንክ አሸንፏል። በዚህም የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በሚዘጋጀው የካፍ ቻምፒዮንስ ሊግ ምስራቅ አፍሪካን እንደሚወክል አረጋግጧል።

የቀድሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተጫዋቿ ሎዛ አበራ ወደ ሰሜን አሜሪካ ማራውደርስ ቨርጂኒያ ክለብን መቀላቀሏ የሚታወስ ነው። የምንጊዜም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ከፍተኛ ጎል አስቆጣሪዋ አጥቂ ሎዛ ቀጣይ መዳረሻዋን ዲሲ ፖወር ክለብ ማድረጓም በዓመቱ ከተሰሙ የምስራቾች መካከል ነው።

## ቦክስ

በውድድር ዓመቱ የተሻለ እንቅስቃሴ ከነበራቸው የስፖርት ማህበራት መካከል አንዱ የሆነው የቦክስ ስፖርት ነው። በዓለም አቀፍ ውድድሮች የተሻለ ውጤት የተመዘገበ ሲሆን፤ በአፍሪካ የቦክስ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ባለቤቱ ፍቅረማርያም ያደሳ፤ ምንም እንኳን ተሳታፊ ሊሆን ባይችልም እስከ ፓሪስ ኦሊምፒክ የሚዘልቅበት ዕድል ተገኝቶ ነበር።

በዓመቱ በተካሄደው የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ እያሱ ወሰን አሸንፈው አህጉር አቀፍ ፕሬዚዳንት የሆኑትም በዚሁ ዓመት ነው። ይህንንም ተከትሎ የኮንፌዴሬሽኑ ጽህፈት ቤት መቀመጫውን አዲስ አበባ ላይ ሊያደርግ ችሏል። በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት ፕሮፌሽናል የቦክስ ውድድሮችም በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂደዋል። እነሱም ኢንተርናሽናል እና ሰሚ ፕሮፌሽናል ውድድር እንዲሁም በዓለም አቀፉ የቦክስ ማህበር የሚመራውና በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነው ፕሮፌሽናል የቦክስ ቻምፒዮና ምሽት ናቸው።

## ስፖርትና ቱሪዝም

ከዓለም ተወዳጅ የጎዳና ሩጫዎች መካከል አንዱ የሆነው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት ለ23ኛ ጊዜ 45ሺ ሯጮችን በማሳተፍ ተካሂዷል። ዓለም አቀፍ ይዘት ባለው በዚህ የ10 ኪሎ ሜትር ሩጫ በርካታ የውጪ ሃገራት ዜጎች ተሳታፊ ናቸው። ኑሯቸውን ከኢትዮጵያ ውጪ ያደረጉ ዜጎችም ተካፋይ እንዲሆኑ በኢንተርኔት የታገዘ «Virtual Run» ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህም 200 የሚጠጉ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባላት ተሳትፈዋል።

ዓመቱ ከምንጊዜውም በተሻለ በስፖርት ቱሪዝም በርካታ ስራዎች የተከናወኑበት ነበር። ከእነዚህም መካከል አንዱ በሃገር አቀፍ ደረጃ በተገነቡ የቱሪስት መስህቦች ስፖርታዊ ሁነቶችን ማዘጋጀት ሲሆን፤ በወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም የ10 ኪሎ ሜትር ሩጫ እንዲሁም የብስክሌት ውድድር ተካሂዷል። የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሚኒስትር በበኩሉ ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በመሆን፤ የአትሌቶች መፍለቂያ በሆነችው በቆጂ፣ በሃዋሳ ሃይቅ ዙርያ እንዲሁም በ40 ምንጭ ከተሞች ስፖርትና ቱሪዝምን መሰረት ያደረጉና በዘርፉ ንቅናቄ መፍጠር የሚችሉ የሩጫ ውድድሮችን አካሂዷል።

አህጉር አቀፍ የፋሽን፣ የቱሪዝም እና ስፖርት ፌስቲቫል በሆነው ሸነን አፍሪካ ፌስቲቫል ላይም ስፖርታዊ ክንውኖች ተካተዋል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) የተሳተፉበት የወዳጅነት ጨዋታ ከቀድሞ አፍሪካዊያን የእግር ኳስ ከዋክብት ጋር ተካሂዷል። በዚህም የናይጄሪያ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ኑዋንኮ ካኑ፣ ዳንኤል አሞካቺ፣ ታሪቦ ዌስት እንዲሁም በአውሮፓ ሊጎች የተጫወተው ሴኔጋላዊው ሄንሪ ካማራ መገኘታቸው የሚታወስ ነው።

## የብሔራዊ ስታዲየም

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን የማስተናገድ ህልሟን ታሳካበታለች ተብለው ከሚጠበቁ ማዘውተሪያ ስፍራዎች መካከል አንዱ የሆነው ብሔራዊ ስታዲየም ምዕራፍ ሁለት ሎት አንድ ግንባታም በ2016 ዓ.ም ነው የተጀመረው። እአአ የ2029ኙን የአፍሪካ ዋንጫ ለማስተናገድ ጥያቄ ማቅረቧ የሚታወስ ነው።

**ዓመቱ በኢትዮጵያ ስፖርት ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ሰዎች የታጡበትም ነበር። ከእነዚህ መካከል ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ፣ ጸሃፊ እና የቀድሞው የእግር ኳስ ተጫዋች ገነነ መኩሪያ ሊብሮ አንዱ ነው።**

## የስፖርት አበረታች ቅመሞች

የስፖርት አበረታች ቅመሞች በዓመቱ ለኢትዮጵያ ስፖርት አስጊ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ቢሆንም ከ2015 ዓ.ም አንጻር በ50 ከመቶ የቀነሰ ነበር። በተለይ ተጋላጭ የሆነው የአትሌቲክስ ስፖርት በመቶዎች የሚቆጠሩ አትሌቶች የደም እና የሽንት ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ 6 (4ቱ በቀጥታ ተጠቃሚ መሆናቸው የተረጋገጠ) አትሌቶች የሕግ ጥሰት መፈጸማቸው ተደርሶበታል። ከዚህ ባለፈ በኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን በተቋቋመው ግብረኃይል በተደረጉ 21 ኦፕሬሽኖች 7 ግለሰቦችና ተቋማት፣ 3 የሕክምና ባለሙያዎች (በቀጥታ)፣ 1 አሰልጣኝ፣ 2 የሕክምና ተቋማት እንዲሁም 1 የመድሃኒት መደብር የሕግ ጥሰቱ አካል በመሆናቸው አስተዳደራዊና ሕጋዊ ርምጃ ተወስዶባቸዋል።

## የስፖርት ዓለም ሰዎች ስንብት

ዓመቱ በኢትዮጵያ ስፖርት ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ሰዎች የታጡበትም ነበር። ከእነዚህ መካከል ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ፣ ጸሃፊ እና የቀድሞው የእግር ኳስ ተጫዋች ገነነ መኩሪያ «ሊብሮ» አንዱ ነው። ታሪክ አዋቂው በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ለስፖርት ቤተሰቡ መረጃ ከመስጠት ባለፈ ኢሃፓና ስፖርት (ከ1እስከ3)፣ ፍትሃዊ የጠጅ ክፍፍል፣ ሊብሮ ኢትዮጵያዊ ስልጠና፣ መኩሪያ፣... የተባሉ መጽሃፍትን ለአንባቢያን አበርክቷል። በዚህም «ተንቀሳቃሽ ቤተመጽሃፍት» የሚባል መጠሪያ ያገኘው ገነነ መኩሪያ ጥር 14/2016 የቀብር ስነ ስርዓቱ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል።

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ስፖርት ከፍተኛ ተስፋ ከተጣለባቸው ወጣት ተጫዋቾች መካከል አንዱ የሆነው አሰልጣኝ አዘነ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየውም ባለፈው ዓመት ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እንዲሁም የባህርዳር ከተማ ተጫዋቹ መጋቢት 17/2016 ዓ.ም ለስፖርት ቤተሰቡ ልብ ሰባሪ የሆነው ሕልፈቱ ተሰምቷል።

# የ2016 ዓ.ም የቱሪዝም ዘርፍ በረከቶች

**ዳግም ከበደ**

የ2016 ዓ.ም አጠናቅቀን አዲሱን የ2017 ዓ.ም ዛሬ ተቀብለናል። ኢትዮጵያውያን አዲሱን ዓመት በተስፋ፣ በአንድነትና በጋራ ለመልማት እቅድ በማውጣት ተቀብለውታል። አዲስ ዓመት ያለፈው የስራና የኑሮ ዘይቤ የሚገመገምበት፤ ጥሩውን ይዞ ክፍተት ያለበትን ደግሞ ለማረም በጥሩ መንፈስ እቅድ የሚወጣበትም ነው።

ዓመቱን በጥሩ ስኬት ለመጀመር እቅድ የግድ እንደሚል ሁሉ «ባለፈው ዓመትስ ምን መልካም ስራዎችን ፈፀምኩ» በማለት በስኬት መስፈርቶች ራስን ማየትንም ይጠይቃል። ይህንን መሰል ባህል በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ነው።

ከግለሰቦች ባሻገርም መንግስታት ከዓመት ወደ ዓመት ሽግግር ሲያደርጉ መሰል የአፈፃፀምና እቅድ ግምገማዎችን ያደርጋሉ። ይህ የአሰራር ስርዓት በጎውን ይዞ፤ አሉታዊ ጎንን ቀይሮ በቀጣይ ውጤታማ ለመሆን ይረዳል። ከዚህ መነሻ የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የአዲስ ዓመት ልዩ እትሙ የተጠናቀቀውን የ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ስኬቶችን ለመቃኘት ሞክሯል፤ ዛሬ በተቀበልነው የ2017 ዓ.ም በዘርፉ ትኩረት ቢሰጣቸው ያላቸውን ጉዳዮችንም ዳሷል።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ውስጥ ታላላቅ እቅዶችን በመንደፍ ተግባራዊ ስታደርግ ቆይታለች። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል በቱሪዝም ዘርፍ የተከናወኑት ይገኙበታል። በዘርፉ አዳዲስ የመዳረሻ ልማት ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ የአሰራር ስርዓቶችን ማሻሻል፣ የቱሪዝም ገበያ ልማትና ማስተዋወቅ ስራዎችን ማጠናከር፣ ቅርሶችን የሚጠብቁና የሚያለሙ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ በዘርፉ ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች መካከል ይገኙበታል።

በተለይ በተጠናቀቀው ዓመት ስኬታማ አፈፃፀም የታየባቸውና በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ሀሳብ አመንጪነት ወደ ተግባር የገቡት በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት የወንጪ፣ የጎርጎራ፣ የሀላላ ኬላ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ተመርቀዋል። በገበታ ለትውልድ ደግሞ ሌሎች በርካታ ፕሮጀክቶችን ወደ መገንባት ተገብቷል። እነዚህ ፕሮጀክቶች የዘርፉ ማርሽ ቀያሪዎች መሆናቸው ተረጋግጧል።

ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀው ወደ ተግባር ከገቡት ከእነዚህ መዳረሻ ልማቶች ባሻገር በ2016 ዓ.ም በቱሪዝም ዘርፍ ተስፋ ሰጪ አፈፃፀም መመዝገቡን መረጃዎች ያመለክታሉ። በዛሬው ዳሰሳችንም የቱሪዝም ዘርፍ ዋና ዋና ስኬቶች እና አፈፃፀሞች ምን እንደነበሩ እንደሚከተለው ለመቃኘት እንሞክራለን።

**በተጠናቀቀው 2016 ዓ.ም እንደ ሀገር የተመዘገቡ የቱሪዝም ዘርፍ ስኬቶች ከላይ ያነሳናቸው ብቻ አይደሉም። ከእነዚህ ውጤታማ የዘርፉ አፈፃፀሞች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በይፋ እውቅና አግኝተው በዩኔስኮ የተመዘገቡ የኢትዮጵያ የመስህብ ሀብቶች ይገኙበታል። ኢትዮጵያ በዓመቱ አራት የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን በዓለም ቅርስነት ማስመዝገብ ችላለች።**

## የጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝም ፣

የጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝም በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ውስጥ ከተያዙት የመዳረሻ ልማት ግንባታዎች በቀዳሚነት ሲጠቀስ ቆይቷል። ይህ ፕሮጀክት በ2016 ዓመት የቱሪዝም ልማቶች መካከል አንዱ ነው። በዓመቱ የጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅ መመረቁ ይታወቃል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ የተገነባው የጎራጎራ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት በዓመቱ ተመርቆ ስራውንም በይፋ ጀምሯል። የማስተዳደር ስራውንም የኢትዮጵያ አየር መንገድ መረከቡን መረጃዎች ጠቁመዋል።

የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ላለፉት ዓመታት በከፍተኛ ትኩረትና የጥራት ደረጃ ግንባታው ሲከናወን ቆይቶ ሐምሌ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ነበር የተመረቀው። ሪዞርቱ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ውስጥ ተካትተው ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ስራ ከገቡት ከወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ፣ ከሀላላ ኬላ እንዲሁም ከጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅ መዳረሻዎች ተርታም ተቀላቅሏል።

የጎርጎራ ፕሮጀክት የቱሪዝም ሆስፒታሊቲ ዘርፉን ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ እንደሚያሻሽለው የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። በተለይ የቱሪስት ፍሰትን በመጨመር፣ የጎብኚዎችን የእርካታ መጠን በማሻሻል ውጤት እንዲመዘገብ መሰረት የጣለ መሆኑ ይገለጻል። ከዚህ ቀደም ወደ ጎርጎራ እና በአማራ ክልል ወደሚገኙ ሌሎች አንዳንድ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና መሰል የመስህብ መዳረሻዎች ጎብኚዎች በሚያቀኑበት ወቅት ደረጃቸውን የጠበቁ የእንግዶች ማረፊያ፣ የሆቴልና የሬስቶራንት አገልግሎት መስጫ ሎጆችና ኢኮ ሪዞርቶች አለመኖራቸው ለዘርፉ እድገት እክል ፈጥሮ ነበር። የጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝም በይፋ ስራ መጀመር ይህንን ክፍተት እንደሞላ ተገልጿል።

የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አረጋ ከበደ የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ለግል ባለሀብቱ በቱሪዝም ልማት አቅም የሆኑ የኢንቨስትመንት ተግባራትን በማከናወን አካባቢውን ለማልማት የሚያስችል መነሳሳትን መፍጠሩን በምረቃ ስነስርዓቱ ወቅት መናገራቸው ይታወሳል። ፕሮጀክቱም በ2016 ዓ.ም ከተመዘገቡ የቱሪዝም ዘርፍ ስኬቶች መካከል አንዱ መሆን ችሏል።

## የሳፋሪ መኪኖች በሀገር ውስጥ መመረት

ሌላኛው የቱሪዝም ዘርፉ የ2016 ዓ.ም ስኬት ሆኖ የተመዘገበው ፕሮጀክት የቱሪስቶችን ጉብኝት የሚያቀላጥፉ የሳፋሪ መኪኖች በኢትዮጵያ ውስጥ መገጣጠም መጀመራቸውን የሚያበስረው ዜና ነው። ከዚህ መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው የእነዚህ ተሽከርካሪዎች በሀገር ውስጥ መገጣጠም መጀመር ለጎብኚዎች ፍላጎትና ምቾት ብቻ አይደለም ምላሽ የሚሰጠው። ዘርፉን አንደሚያሳድገውና ኢትዮጵያንም በቱሪስቶች ተመራጭ እንደሚያደርጋት ታምኖበታል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት ከታደሉ ጥቂት የዓለማችን አገራት ተርታ ትመደባለች። እነዚህን የተፈጥሮ መስህቦች ለመመልከት በሚል በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ቱሪስቶች የኢትዮጵያን ምድር ይረግጣሉ። ወደ አገር ወስጥ ሲገቡ የአፍሪካ ኩራት የኢትዮጵያን ሀብት የሆነው አየር መንገድ ቢኖርም በየብስ ትራንስፖርት ግን በቂ አቅርቦት (በሚፈለገው ልክ የጎብኚዎችን እርካታ የሚያረጋግጥ) ሳይኖር መቆየቱ ይነገራል። የዚህ ዋነኛው መነሻ ችግር በአገር ውስጥ ቱሪስትን መሰረት አድርገው የሚመረቱ የጉብኝት ትራንስፖርት ሰጪ መኪኖች አለመኖር ነው።

በዚህ መነሻ መንግስት የቱሪዝም ዘርፍን እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምሰሶ አድርጎ የፖሊሲ ማሻሻያ ሲያደርግ «ሊስተካከሉ ይገባቸዋል» ብሎ ካስቀመጣቸው ጉዳዮች መካከል የትራንስፖርት አገልግሎት ማሻሻልን ነው። በዚህም ባጠናቀቅነው የ2016 ዓ.ም አንድ ስኬታማ አፈፃፀም መመዝገቡን መረጃዎች ያመለክታሉ።

የጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ለመገናኛ ብዙሃን ይፋ ያደረገው መረጃ እንደሚያመልክተው፤ የተፈጥሮ ቱሪዝምንም ሆነ መሰል መስህቦችን ለመጎብኘት የሚያስችሉ በአገር ውስጥ የተመረቱ መኪኖችን የማምረት ተግባር በይፋ ተጀምሯል። ይህም መንግስት ባለሀብቶችን ለመደገፍ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት በ2016 ዓ.ም መሳካቱንና የመጀመሪያዎቹ ለሳፋሪ ጉብኝት የሚያገለግሉ መኪኖች ተመርተው ርክክብ መደረጉም ተገልጸል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት መረጃዎች እንዳስታወቁት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ /ዶክተር/ በየካቲት 2016 የሚኒስትሮች ምክር ቤት የ100 ቀናት ግምገማ ወቅት ለቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ የሳፋሪ ተሽከርካሪዎች እንዲመረቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሰጡትን አቅጣጫ ተከትሎ በሀገር ውስጥ ለሳፋሪ አገልግሎት ተሽከርካሪነት የተቀየሩ ባለ አንድ ጋቢና ፒክ አፕ መኪናዎችን በናሙናነት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስረክቧል። መኪናዎቹን ለሳፋሪ አገልግሎት እንዲመቹ አድርጎ በመለወጥ ሂደት ውስጥ አምራቾች በሀገር ውስጥ በስፋት የመለወጥ ልምድ እና አቅም ለማዳበር እንደቻሉም ተመልክቷል።

ለሳፋሪ አገልግሎት የሚውሉ መኪኖች በኢትዮጵያ ውስጥ መመረት የጎብኚዎችን ጥራት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመጓጓዣ ፍላጎት ከመመለስ አንፃር በጎ ጅምር እንደሆነ ይታመናል። ይህ እቅድ ተግባራዊ ተደርጎ መኪኖቹ መመረት የጀመሩበት ዓመትም የ2016 ዓመት ሆኖ ተመዝግቧል።

## የዓለም ቅርስ ምዝገባ

በተጠናቀቀው 2016 ዓ.ም እንደ ሀገር የተመዘገቡ የቱሪዝም ዘርፍ ስኬቶች ከላይ ያነሳናቸው ብቻ አይደሉም። ከእነዚህ ውጤታማ የዘርፉ አፈፃፀሞች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በይፋ እውቅና አግኝተው በዩኔስኮ የተመዘገቡ የኢትዮጵያ የመስህብ ሀብቶች ይገኙበታል። ኢትዮጵያ በዓመቱ አራት የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን በዓለም ቅርስነት ማስመዝገብ ችላለች። ከእነዚህ መካከል ሀይማኖታዊና ባህላዊ ይዘት ያለው የሐረሪ ብሔረሰብ የሸዋል ኢድ አንዱ ነው።

«ሸዋል ኢድ የታላቁን የረመዳን ወር መጠናቀቅን ተንተርሶ የሚከናወን እና በሐረር ሕዝብ የሚከበር ደማቅ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል» መሆኑን የክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም የቱሪዝም ሚኒስቴር መረጃዎች አመልክተዋል።

በመስከረም ወር ላይ ምዝገባው የተከናወነውን ባህላዊ ሀብት አስመልክቶ አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ፤ የረመዳን ወር መጠናቀቅን ተከትሎ የሚከበረው ሸዋል ኢድ የሐረር ከተማ ሞገስና ልዩ መለያ የሆነው የጀጎል ግንብ በክብረ-በዓሉ የሚያሸበርቅበት፣ ስሜትን የሚቆጣጠሩ ትዕይንቶች የሚከወኑበት፣ ሐረር ከወትሮው በተለየ መልኩ የምትፈካበት፣ የፍቅርና የእንግዳ ተቀባይነት ምልክት የሆነው የሐረር ሕዝብ በቱባ ባህሉ የሚደምቅበት መሆኑን መግለጻቸው ይታወሳል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ በመንፈሳዊ መዝሙሮችና ውዝዋዜዎች ተጀምሮ በቅዱሳን መፅሃፍት ንባብ ተዋጅቶ በምርቃትና መልካም ምኞቶች የሚቋጨው ሹዋልዒድ በውስጡ ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም ሕዝቦች ፋይዳ ያላቸው እሴቶችን የያዘ ነው። ይህ ሀብት ባጠናቀቅነው የ2016 ዓ.ም በመስከረም ወር ላይም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት እና የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ሃብት እንዲሆን ተመዝግቧል።

ከሸዋል ኢድ ባሻገር በ2016 ዓ.ም ስኬታማ የዓለም ቅርስነት እውቅናን ካገኙ ኢትዮጵያዊ መስህቦች መካከል የጌዴኦ ማኅበረሰብ እሴት የሆነው ባህላዊ መልከዓ ምድርና በውስጡ የሚገኙት የትክል ድንጋዮች (ሜጋሊቲክ ሀውልቶች) ይገኙበታል። የኢትዮጵያ መንግስት አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማልማት፣ ለማስተዋወቅ እና የቱሪስት መዳረሻዎች እንዲሆኑ ለመስራት ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ ባኅላዊና የአርኪዮሎጂካል ቅርሶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በዩኔስኮ እውቅና እንዲያገኙ ይሰራል።

በዚህ ጥረት በዓለም ቅርስነት በ2016 ዓ.ም ከተመዘገቡ መስህቦች ወስጥም የጌዴኦ መልከዓ ምድር አንዱ ነው። ይህ መስህብ የማኅበረሰቡን እሴቶች በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልተው እንዲታዩ ከማድረጉም ባሻገር ለጎብኚዎች አዲስ አማራጭ አንደሚሆን ይጠበቃል። የማኅበረሰቡን የቆየ አገር በቀል እውቀት ወደ ሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በማስፋትም በተለይ ለደን ልማትና ጥበቃ የሚውል ግብአት ማግኘት ይቻላል።

በዓለም ቅርስነት በ2016 ዓ.ም እውቅና ካገኙ የኢትዮጵያ መስህቦች ውስጥ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ እንዲሁም የመልካ ቁንጡሬ ባልጪት አርኪዮሎጂካል ስፍራ ይገኙበታል። የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በ45ኛው የዓለም ቅርስ ጉባኤ ላይ በዓለም ቅርስነት በቋሚነት የተመዘገበ ሲሆን፣ የመልካ ቁንጡሬ ደግሞ በ46ተኛው ጉባኤ ላይ በዓመቱ መጨረሻ ሊመዘገብ ችሏል።

እንደሚታወቀው ፓርኩ (ባሌ) በውስጡ የተለያዩ ስነ- ምህዳሮችን በአንድ ቦታ በማቀፉ «አንድ ፓርክ ብዙ ዓለም» የሚል ስያሜ ያገኘ ነው። በውስጡም የደጋ አጋዘን፣ ቀይ ቀበሮ፣ ድኩላና የባሌ ጦጣ መገኛ ነው። ይህ ፓርክ በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ ለቱሪዝም ልማት፣ ለቱሪስት ፍሰት አንዲሁም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚና ለአገር ገፅታ ገንባታ የላቀ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል።

ሌላውና የ2016 ዓ.ም የቱሪዝም በረከት ውስጥ የሚካተተው የመልካ ቁንጡሬ ባልጪት አርኪዮሎጂካል ስፍራ ነው። ይህ ጥንታዊ የሰው ልጅ የኑሮ ዘይቤን እና የሰው ዘር አመጣጥን የሚያሳየው ታሪካዊ ቦታ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስ የሚል እውቅናን ተችሮታል። ምዝገባውም በሐምሌ ወር ላይ ነበር በሕንድ ኒው ደሊህ በተካሄደው ጉባኤ ላይ ይፋ የተደረገው።

## እንደ መውጫ

የ2016 ዓ.ም የቱሪዝም ዘርፍ በርካታ ስኬቶች የተመዘገበበት መሆኑን ከላይ ያነሳናቸው ማስረጃዎች ያመለክታሉ። በእርግጥ ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ከፖሊሲ ማሻሻል፣ ሕግና ስርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ አንስቶ በርካታ ውጤቶች ታይተዋል። በዚህ ረገድ የታዩትን መዋቅራዊ ማሻሻያዎችና የሕግና ስርዓት ለውጦች የሚኒስቴር መስሪያቤቱን ዓመታዊ አፈፃፀም በምንዳስስበት ወቅት የምናነሳው ይሆናል። በጥቅሉ ግን በዓመቱ እንደ አገር በተያዙ ታላላቅ ፕሮጀክቶችና በዩኔስኮ በተመዘገቡ ቅርሶች የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ውጤታማነት ዓመት አንደነበር መረጃዎቹ ያስረዳሉ።